# ግልጽ የደብዳቤ ልውውጥ፤

## ቄስ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ፡
## ለአለቃ አያሌው ታምሩ በጻፉት ደብዳቤ መነሻነት፡
## የደረሱን እ-ጦማሮችና የተሰጣቸው መልስ።

---

**1. Email from Berhan:**

Dear Mr Ermias፡

I read with disgust the letter you wrote to His excellency Aleqa Ayalew Tamiru.

If the letter was written while Aleqa Ayalew was alive it would have been as fair and any normal person would have expected a response to your letter.

Now, after many years of services, Aleqa Ayalew has passed away and he is not in a position to respond to your sick letter. I only feel sorry for you.

He was undoutedly the greatest Ethiopain scholar ever lived. You and your kind of people would never ever even match him in millions of years.

Obviously, the letter is written by some one who do not have any decency and respect to out Ethiopian tradition.

---

**2. Email from Moule and Mikre Selassie፡**

Nibure-Id Qes Ermias!

I read your "letter" to the late Ethiopian scholar Aleqa Ayalew Tammerru. I was stunned with amazement when I finished the 21st page. With all due respect, sir, you must be a crazy person! Who would write a letter to a person who passed away, unless they are crazy or unless they were haunted by the strong character of that man!?

You have mentioned it well yourself on page 35 of your book "Ethiopia: Ye'Alemu Mefarejja!". You have also mentioned on page 16 of the letter that you do not have a proper education of the faith of the Ethiopian Orthodox Church. All you said is that as Protestants say you were educated from God! That's a lame excuse. And if you are not educated it's a pity that you try to single out the "errors" commited by Aleqa or other LIQAWUNT.

You have also mentioned in the letter and on other writings that you do not accept the Ethiopian Orthodox Church and you are not an Orthodox. So, that prevents you from commenting on the church's status or anything related to it. Everybody knows that you do not live by the rules of the church. You have created your own denomination like the Protestants do; you celebrate the mass and hold church services in your own house. That's way out of the teachings of the church.

The last thing I want to mention is your books. They are poison covered with honey. And the honey is stolen from Aleqa Ayalew Tameru's books. But it's no use because you have added poison in it. So, your books are simply crap and serve no purpose other than wasting your own time as well as the readers' time and taking up space in the bookshelf.

Let's come back to your "letter". It seems to me that you have a huge hatred towards Aleqa. Why? Let me guess? He refused to collaborate with you in printing those crap books of yours. Am I right? And besides, at that time you were fresh out of prison, delusional, and his refusal was like a death sentence to you. That's so sad. But what was he supposed to do as he were the chairman of the council of the Theologians of the church. Was he supposed to give you the green light? I suppose not. Because his sole job was to protect the faith and teachings of the church from false and fictitious craps like your books and the like. So he did the right thing? Don't you think so Nibure-Id? So, I think his strong belief and character still haunts you..till this day. I am sorry for you.

Let me finish my message by giving you a simple advice. It was the advice the great Liq gave you when he was alive. "Kezih kifu Alem raswon'na betesebwon yadnu."

---

**3. Email from Kerin Geremew፡**

Dear Nibure – ed Ermias Kebede!

May the peace and health of the Almighty God be with you!

I read the letter you wrote to the most respected scholar, man of God and prophet of our generation  Like – Likawent Aleka Ayalew Tamiru.

First of all, I haven't enough words to express my sadness and the shame I feel about what you did. Do you really believe in the values of Ethiopiawenet? I doubt! If you would have had a true belief in Ethiopiawenet what you did is just to the contrary of decency, Christianity and humanity. Pls. don't make your self a cause of insults to the name of the Almighty God and to our holy church. Whether you are bad or good you are the product of this church. In the other hand, I fill sorry for you; your letter clearly shows how much you suffer by complex in comparing your self with the great man Like-Likawent Aleka Ayalew Tamiru and how much you are haunted by his clean spirit. Poor guy!!

With a surprising coincidence I got a chance to see you in the office of the late Like-Likawent Aleka Ayalew in the then Yelekawent Gubae office right after you went out from the prison of Derg.

When I read this letter all my memory went back to that unique event where I saw you at that office. It is surprising to me. Let me draw back your memory to that date if you have a left over healthy memory.

You were fresh out of prison, hungry, delusional, bitter and pleading the great man Like-Likawent Aleka Ayalew Tamiru to give you the green light to get your books printed. Like-Likawent Aleka Ayalew decline to your request was like a death sentence to you. I remember how much you were frustrated and helpless in front of Aleka. At that time I was in hurry to go back to Europe in the same night and I didn't got time to discuss the matter concerning you and your book with Like- Likawent Aleka Ayalew.

Lately I heard that you left the country and still lives in confusion and bitterness in Maryland . Off course, I read the book your wrote and rejected by Lique Aleka Ayalew Tamiru in the land of your freedom and madness where you are living with your fantasy.

I can understand that you never dare to write a single line if Lique Aleka Ayalew was alive. You never did that during his life time. Because the satan who lived in you knows very well more than you how much that great person was holy and how his utter commitment as a greatest scholar was only to the truth and the purity of the teachings our religion .

Sorry! For you!!
Kerin Geremew

ከንቡረ እድ ኤርምያስ ክበደ ወልደ-ኢየሱስ፡
ለሦስቱም እ-ጦማሮች፡ የተሰጠ መልስ፡-

ይድረስ፡-

ለ... ብርሃን፣ ለ... ሙሌ፣ ለ... ምክረ ሥላሴና ለ... ቀሪን ገረመው።

(የአጠራር ማዕርጋችሁን ክፍት ያደረግሁት፡
ስሞቻችሁ፡ ጾታችሁን ለይተው ስለማያስታውቁ ነው።)

የመልእክታቸው ፍሬ ነገር፡ የኹሉም፡ ተመሳሳይና ቋንቋውም፡ በእንግሊዝኛ የኾነ፥ በተለይ፡ ፫ኛው፡ ቀኑና አድራሻው፥ ቃሉም አንድ፥ ነገር ግን፡ በኹለት የተለያዩ ስሞች ኾኖ፡ በማከታተል የጻፉችሁልኝ፡ ሦስቱም፡ እለቄጥሩ ጦማሮቻችሁ ደርሰውኛል፤ እግዚአብሔር ይስጥልኝ!

ኢትዮጵያኛውን ቋንቋ ልታነብቡና ሊገባችሁ እንደሚችል፡ ከየስማችሁ አጠራር ስለተረዳሁ፥ ከዚህ የተነሣም፡ መቼም፡ እጅግ ካልቸገረንና ካልተገደድን በቀር፥ በአጠቃላይ፡ ከባዕዳኑ ቋንቋ ይልቅ፥ "በራሳችን፡ በኢትዮጵያኛው መጠቀሙ ይሻላል!" ብዬ በማሰብ፥ ደግሞም፡ በቀላሉ ለማስረዳትና በበለጠ ለመግባባት ይቻለን፥ ያመቸንም ዘንድ፥ ይበልጡንም፡ ከእናንተ ይልቅ፡ ለሌላው፡ ማብራሪያና ትምህርት እንዲኾን፡ ይኸው በዚህ መልኩ፡ መልሴን አቅርቤላችኋለሁ።

ስለዚህ፡ ይህንኑ መልሴን፡ ቢቻላችሁ፡ በቅን ልቦና ጭምር፥ አለዚያ፡ በትኵረትና በማስተዋል እንድትመለከቱልኝ፡ እንደገና አሳስባችኋለሁ። "እንደገና" ያልሁት፡ ያለምክንያት አይደለም፤ እናንተ፡ አኹን፡ በመቈርቈርና በቊጭት፡ ለእኔ፡ መልስ እንድትጽፉልኝ ያደረጋችሁን፡ ያንን፡ ለአለቃ አያሌው ታምሩ የጻፍሁትን፡ የመጀመሪያውን ደብዳቤ፡ ቢያንስ ቢያንስ፡ በትኵረትና በማስተዋል ተመልክታችሁት ቢኾን ኖሮ፡ እናንተ እና እኔ፡ አኹን፡ እንደዚህ፡ በጽሑፍ መመላለስ ባላስፈለገን ነበር። የዚያን ደብዳቤ መልእክት፡ በትክክል ለመረዳት ደግሞ፡ ራሱ፡ ደብዳቤው: ራሱን፡ በሚበቃ የሚያስረዳ ስለኾነ፡ የሚያስፈልገው፡ በቅን ልቦና ላይ የተመሠረተ፡ የአንባቢ ፍላጎት ብቻ ነው። ይህ ችግር፡ በአብዛኛው፡ የዘመናችን ትውልድ አባል፥ በተለይም፡ ራሳችንን፡ "ኢትዮጵያዊ/ት ነኝ!" በምንለው ዘንድ፡ የጎላ ኾኖ ስለሚታይ፡ ሊታረም የሚገባው ጉድለት ይመስለኛል።

በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊው ጨዋነት፡ ለመግቢያ ያህል፡ ይህን አጭር ቃል ከሠነዘርሁ፡ በዚሁ፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊው ጨዋነት፡ የማብራሪያ መልሴን፡ እንደሚከተለው አቀርብላችኋለሁ፡-

፩ኛ. I read with disgust the letter you wrote to His excellency Aleqa Ayalew Tamiru. If the letter was written while Aleqa Ayalew was alive it would have been as fair and any normal person would have expected a respsone to your letter. Now, after many years of services Aleqa Ayalew has passed away and he is not in a position to respond to your sick letter. I only feel sorry for you. **ላላችሁት፡-**

**እንደእኛ፡ እንደቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያ ልጆች ሃይማኖት፡ እርሳቸው፡ በሕይወተ ነፍስም፡ ምንጊዜም፡ በህልውናቸው የቀጠሉ ከመኾናቸው በቀር፡ "ሞተዋል!" ብለን አናምንም፤ የእርሳቸው ህልውና፡ በዚህ ዓለም፡ በሕይውተ ሥጋ፡ አለመቀጠል፡ በሕያዉ የእግዚአብሔር ቃል ላይ የተመሠረተውን መልእክት በያዘው ደብዳቤዬ በኩል፡ የሚያስከትለው ምንም ዓይነት ለውጥ የለም። የደብዳቤዬን መግቢያ፡ በማስተዋል ስላልተመለከታችሁት እንጂ፡ ተመልክታችሁት ቢኾን ኖሮ፡ እውነተኞቹ የኢትዮጵያ ልጆች፡ ምንጊዜም ቢኾን፡ "ሕያዋን" እንጂ፡ "ሙታን" ተብለው የማይፈረጁ ስለመኾናቸው፡ በሚበቃ ተብራርቶ የተገለጠውን ሃይማኖታዊ ቁም ነገር ተረድታችሁ፡ ይህን የመሰለውን አስተሳሰብና አጻጻፍ ልታስቀሩት በቻላችሁ ነበር።**

**ዳግመኛም፡ የዚህ፡ የውዝግቡ መነሻ የኾነው፡ የአለቃ አያሌው ታምሩ መጽሓፋቸው፡ በሕይወተ ሥጋ ሣሉ፡ ደርሶኝ ቢኾን ኖሮ፡ ይህንኑ ደብዳቤ፡ በዚሁ መልኩ ጽፌ፡ ለእርሳቸው በቀጥታ መላኬ ስለማይቀር፡ ይኸው ውዝግብ ባልደረሰ ነበር። ይህን አባባሌንም፡ አኹን፡ በሞተ ሥጋ ከተለዩ በኋላ፡ በጻፍሁት፡ በዚሁ ደብዳቤዬ፡ ገጽ ፲ ላይ፡ "ከሃይማኖታችንና ከምግባራችን፥ ከሥርዓታችንም ጋር፡ ነክነት ስላለው፡ ስለሌላው ግብርዎማ፡ በሕይወተ ሥጋ እያሉ፡ ለራስዎ ባስነበቡትና በሰሙት፡ "ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፈረጃ!" በሚለው መጽሓፌ ውስጥ፡ (ገጽ ፩፻፳- ፩፻፳፯) በሚበቃ ስለገለጽሁ፡ እዚህ ላይ፡ በተነሣሁበት በዚሁ ርእስ፡ ከመወሰን በቀር፡ ሌላ የማክለው ነገር አይኖረኝም።" ብዬ የጠቀስሁት ቃል ያረጋግጠዋል።**

፪ኛ. …he was undoutdely the greatest Ethiopain scholar ever lived. You and your kind of people would never ever even match him in millions of years. … I read the letter you wrote to the most respected scholar, man of God and prophet of our generation Like – Likawent Aleka Ayalew Tamiru. **ላላችሁት፡-**

**ከመጥምቁ ዮሓንስና ከጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በኋላ፡ "ነቢይ" የሌለ መኾኑን እንድታውቁት ኾኖ፡ በደብዳቤዬ ውስጥ ተጠቅሶ የቀረበውንና የተተቸበትን፡ ያን፡ የድፍረትና የስድብ ቃል፡ በእግዚአብሔርና በቅድስት እናቱ ላይ፡ በመጽሓፍ መዝግበው ላለፉት፡ ለአለቃ አያሌው ታምሩ ሊቅነት፡ እናንተ የሰጣችሁትን፡ ይህን መመዘኛችሁን፡ ከጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስና ከተከታዮቹ ሓዋርያት ቃላት ጋራ ስናነጻጽረው፡ የተለያየ ኾኖ እናገኘዋለን።**

እኒህም፡ ጌታ፡ “እናንተስ፡ ‘መምህራን’ ተብላችሁ አትጠሩ! መምህራችሁ፡ አንድ ነውና። ሊቃችሁ፡ አንድ፥ እርሱም፡ ክርስቶስ ነውና፡ በምድር ላይ፡ ‘ሊቃውንት’ ተብላችሁ አትጠሩ! እናንተስ፡ ኹላችሁ፡ ወንድማማች ናችሁ።” እንዲያውም፡ “ከእናንተ የሚበልጠው፡ አገልጋይ ይኹናችሁ! ራሱን፡ ከፍ ከፍ የሚያደርግ ኹሉ፡ ይዋረዳልና፤ ራሱንም፡ ዝቅ የሚያደርግ ኹሉ ይከብራልና።” ብሎ የተናገራቸው ቃላት፡ ቀዳሚዎቹ ናቸው። (ማቴ. ፳፫፥ ፰-፲፪።)

ደግሞም፡ እናንተ፡ ለሊቃችሁ፡ ለአለቃ አያሌው ታምሩ ያቀዳጃችሁትን የመሰለው ሚዛን፡ በዘመኑ ትውልድ ዘንድ ተሰጥቷቸው ስለነበሩት፡ የአይሁድ “ሊቃውንትና ምሁራን”፡ የእኛ ሊቅና መምህር ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረውን፡ እስኪ ልጥቀስላችሁ! “እናንተ፡ በመጻሕፍት፡ የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ይመስላችኋልና፡ እነርሱን ትመረምራላችሁ፤ እነርሱም፡ ስለእኔ የሚመሰክሩ ናቸው። ነገር ግን፡ ሕይወት እንዲኾንላችሁ፡ ወደእኔ ልትመጡ አትወድዱም። ከሰው ክብርን አልቀበልም፤ ዳሩ ግን፡ የእግዚአብሔር ፍቅር፡ በራሳችሁ እንደሌላችሁ አውቃችኋለሁ። እኔ፡ በአባቴ ስም መጥቻለሁ፤ አልተቀበላችሁኝምም፤ ሌላው፡ በራሱ ስም ቢመጣ፡ እርሱን ትቀብሉታላችሁ። እናንተ፡ እርስ በርሳችሁ፡ ክብርን የምትቀባበሉ፡ ከአንዱ ከእግዚአብሔር ያለውንም ክብር የማትፈልጉ፡ እንዴት፡ ልታምኑ ትችላላችሁ?

“እኔ፡ በአብ ዘንድ፡ የምከስሳችሁ አይምሰላችሁ! የሚከስሳችሁ አለ፤ እርሱም፡ ተስፋ የምታደርጉት ሙሴ ነው። ሙሴንስ ብታምኑት፡ እኔን ባመናችሁ ነበር፤ እርሱ፡ ስለእኔ ጽፏልና። መጻሕፍትን ካላመናችሁ ግን፡ ቃሌን እንዴት ታምናላችሁ!?” (ዮሐ. ፭፥ ፴፱-፵፯።)

ከእነዚህ የሚቀጥሉት ደግሞ፡ ከሓዋርያት፡ አንዱ የኾነው፡ ቅዱስ ጳውሎስ፡ በመንፈስ ቅዱስ ተመልቶና ተመርቶ የጻፋቸው፡ እንዲህ የሚሉት ቃላት ናቸው፡- “[ሊቅ] ጥበበኛ ማን ነው? ጸሓፊስ ማን ነው? የዚች ዓለም መርማሪስ ማን ነው? እግዚአብሔር የዚችን ዓለም ጥበብ [ሊቅነት]፡ ሞኝነት እንዲኾን አላደረገምን? ...እግዚአብሔር፡ ጥበበኞችን [ሊቃውንትን] ሊያሳፍር፡ የዚህን ዓለም ሰነፎች መረጠ፤ ኃይለኞችንም ያሳፍር ዘንድ፡ እግዚአብሔር፡ የዚህን ዓለም ደካሞች መረጠ፤ ‘አለን!’ የሚሉትንም ያሳፍር ዘንድ፡ ዘመድ የሌላቸውንና የተናቁትን፥ ከቍጥርም ያልገቡትን፡ እግዚአብሔር መረጠ። ሰው ኹሉ፡ በእግዚአብሔር ፊት እንዳይመካ፤ ነገር ግን፡ የሚመካ፡ በእግዚአብሔር ይመካ!” (፩ቆሮ. ፩፥ ፳-፴።)

፫ኛ፡ You have mentioned it well yourself on page 35 of your book "Ethiopia: Ye'Alemu Mefarejja!". You have also mentioned on page 16 of the letter that you do not have a proper education of the faith of the Ethiopian Orthodox Church. All you said is that as Protestants say you were educated from God! That's a lame excuse. And if you are not educated it's a pity that you try to single out the "errors" commited by Aleqa or other LIQAWUNT. ላላችሁት፡-

በመጻሕፍቴና በሌሎቹ ድርሰቶቼ፡ እኔ ያመለከትሁት የእግዚአብሔር እውነታ፡ በመንፈሳዊዉም ኾነ በሥጋዊው ትምህርት፡ በሰዎች ዘንድና በሥርዓታቸው፡ “ሊቅ”፥ ወይም፡ “ምሁር” የሚያስሰኘው ትምህርት እንደሌለኝ፡ ራሴን በመቍጠር፡ የማምንበትና የምተማምንበት ትምህርቴና እውቀቴ፡ ከሰው ካገኘሁት ይልቅ፡ እንደመለኮታዊው የሃይማኖታችን ቃል፡ ከእግዚአብሔር የተለገሥሁት የሚበልጥብኝ መኾኑን፡ ለራሴ ብቻ ሳይኾን፡ ለሌሎችም ለማሳወቅና ለማስተማር ስል፡ በጽሒፈት መግለጤ ነው።

ለመኾኑ፡ እንደእናንተ አስተሳሰብና አገላለጽ፡ *“‘ሊቅ’፥ ወይም፥ ‘ምሁር’ ካልኾኑ በስተቀር፡ እግዚአብሔርን ማወቅ፥ ወይም፡ ስለእግዚአብሔር እውነት ለመናገር አይቻልም፥ ወይም አይገባም፥ ወይም አያስፈልግም!”* ማለታችሁ ነውን? እንዲያማ ከኾነ፡ ካህናቱ፥ ሊቃውንቱ፥ እናንተ፤ “ጳጳሳት፥ ሊቃነ ጳጳሳት፥ ፓትረያርክ” የምትሏቸው ሊቃነ ካህናቱ፡ እያሉ፡ እግዚአብሔር፡ እውነቱን የሚናገርለት ሰው ሲያጣና ሲቸግረው፡ እንኳንስ መጻፍ፡ ማንበብ የማይችሉትን፥ የመጽሓፍ ቃልንም እንኳ ሰምተው የማያውቁትን፡ ልበ ንጹሓን ገጠሬዎችንና ገዳማውያን ባሕታውያንን፡ ስለእርሱ እውነትና ስለመንግሥቱ፡ በግልጥ ይናገሩለት ዘንድ፡ በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ መልቷቸው፡ እናንተና እናንተን የመሰሉት ወደምታገለግሏቸው ወደዓለሙ ባለሥልጣኖች የሚልከው፡ ታዲያ ለምንድር ነው?

**“ልጆችሽም ኹሉ፡ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይኾናሉ፤ ልጆችሽም፡ በሰላም ይኖራሉ!”** ብለው፡ በመንፈስ ቅዱስ የተናገሩትን፡ የነቢያትን ቃል መሠረት በማድረግ፡ ራሱ፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ **“እንግዴህ አታንጕራጕሩ!…‘ኹሉም፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ፡ የተማሩ ይኾናሉ!’ ተብሎ፡ በነቢያት መጽሓፍ ተጽፏል፤ እንግዴህ፡ ከአባቴ የሰማ ኹሉ፡ ተምሮ፡ ወደእኔ ይመጣል!”** ሲል፡ ይህን ቃል የጠቀሰው፡ ለምንድር ነበር? ለማንስ ነበር? እርሱ ራሱ፡ ያልተማረና እንደእነርሱ “ሊቅ” የሚያሰኘውን ትምህርት አግኝቶ ያልተመረቀ በመኾኑ፡ ይንቁት ለነበሩት፡ ለተቃዋሚዎቹ የአይሁድ ሊቃውንት አልነበረምን? አዎን! ነበር።

እነርሱም፡ በእግዚአብሔርነቱ፡ የሚናገረውንና የሚያደርገውን ኹሉ፡ በዓይናቸው እያዩና በጆሮአቸው እየሰሙ፡ የእርሱን ማንነት፡ በሃይማኖት መቀበል ተስኗቸው፡ **“እኛ፡ አባቱንና እናቱን የምናውቃቸው፡ ይህ፡ የዮሴፍ ልጅ፡ ኢየሱስ አይደለምን? እንዴት ከሰማይ ወረድሁ ይለናል!?”** ደግሞም፡ **“እንግዴህ፡ ይህ ኹሉ ጥበብና ተአምር፡ ከየት ተሰጠው? ይህ የጠራቢው፡ የዮሴፍ ልጅ አይደለምን? የእናቱስ ስም፡ ማርያም አይደለምን?”** ያሉት እንደነበሩ እናውቃለን።

ይኸው፡ **“ኹሉም፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተማሩ ይኾናሉ!”** የሚለው፡ ጌታ የጠቀሰው የነቢያቱ ቃል የተነገረው፡ ስለራሱ ብቻ ሳይኾን፡ እርሱን ስለመሰሉትና ስለተከተሉት ኹሉ እንደኾነ ግልጽ ነው።

ይህም፡ እኒሁ አይሁድ፡ “ጴጥሮስና ዮሐንስ፡ በግልጥ እንደተናገሩ ባዩ ጊዜ፡ መጽሐፍን የማያውቁና ያልተማሩ እንደኾኑ አስተውለው፡ አደነቁ!” በሚለው አነጋገራቸው ይረጋግጣል። (ኢሳ. ፶፬፥ ፲፫። ዮሐ. ፮፥ ፵፩-፵፮። ማቴ. ፲፫፥ ፶፫-፶፯። የሐዋ. ፬፥ ፲፫።)

እኔም፡ በመንፈሳዊው ወገን፡ የቀደሙ ታላላቅ ሊቃውንትና የቀሳውስት ካህናት ወገኖች ከኾኑ ወላጆች፡ በአዲስ አበባ መናገሻ ከተማ፡ በመካነ ሰማዕት ቅዱስ ቂርቆስ ሰበካ የተወለድሁና ያደግሁ፥ ከሕፃንነት ጀምሬ፡ በቤተ ክህነት ትምህርት፡ በቤተሰቤና በእነየኔታ ሀብተ ሚካኤል እግርና ወንበር ሥር፡ እየተኮተኮትሁ ያደግሁ ነኝ፤ የኋላ ኋላም፡ በነአለቃ አያሌው ታምሩ ጊዜ ጭምር፡ የቤተ ክህነት የሊቃውንት ጉባኤ አባል ከነበሩት፡ ከአራት ዓይናው ሊቅ፡ ከመምህር ላዕሉ በፈቃዱ ጋር እስከዘመናቸው ፍጻሜ ድረስ፡ ዐብሬያቸው ውዬና በአጠገባቸው ተቀምጬ፡ ትምህርታዊ እውቀትን የቀሠምሁ ነኝ።

ለመኾኑ፡ ለዲቁናና ለቅስና፥ ከዚያም፡ ለተወለድሁበት፡ ለመካነ ሰማዕት ቅዱስ ቂርቆስ ደብር እልቅናና ለብዙ፡ የቤተ ክህነት ዋና ጽሕፈት ቤት፡ የአገልግሎት ዘርፎች ሥራ መሪነት፥ ለታዕካ ነገሥት ቅድስት በአታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያን ባለአደራ ለኾነው፡ ለዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ ድርጅት አስተዳዳሪነትና ለአኵሱም ጽዮን ርእሰ አድባራት ንቡረ እድነት፥ በመጨረሻም፡ ለኢትዮጵያ ቤተ ክህነት ጠቅላይ ሥራ አስኪያኻጅነት፡ ያውም፡ ስንቱ ዓይነት የ“ሊቃውንት” ብዛት በተትረፈረበትና በገነነበት፡ በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት፡ እየታጨሁ የተሾምሁትና በእነዚህ ሥልጣናት ያገለገልሁት፡ አስፈላጊውና ተገቢው የትምህርትና የእውቀት ደረጃ ሳይኖረኝ ኖርዋልን?

በሥጋዊዉም በኩል፡ የ፩ኛና የ፪ኛ ደረጃዎች ዘመናዊ ትምህርትን፡ በዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት አከናውኼ፥ ገና እዚያ እያለሁም፡ “ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት!”፥ “አዲስ ዘመን፡ ለወጣት ትውልድ!” በሚሉ የተለያዩ አርእስት፡ በተከታታይ እየታተሙ ይወጡ የነበሩ፡ የጦማረ ሕዝብ መልእክቶችን ከማቅረብ ጋር፡ “እየው ያን መከራ! የደስታ ጮራ!” የሚለውን ተውኔት ደርሼ፡ ራሴና በዚያን ጊዜ፡ በትምህርት ቤቱ፡ የመጀመሪያዋ፡ ልጃገረድ ተማሪ የነበረችው፥ እስከዛሬም ዐብራኝ ያለችው ባለቤቴ፡ ወይዘሮ ራሔል ዘካርያስ፡ ኹለታችንም፡ በባልና ሚስትነት፡ ተዋናዮች በኾንንበት፡ ይህንኑ ተውኔት፡ በት/ቤቱና በወወክማ አዳራሾች፡ ለሕዝብ ማሳየቴ፥ ወዲያውም፡ “ምናሴ” በሚል ዋና ርእስና “የመከራዬ ደስታ! ዓለምን ረታ!” በሚል ንዑስ አርእስት፡ በ፲፰ ዓመት ዕድሜዬ፡ አንድ መጽሓፍ ደርሼና አሳትሜ፡ ለሕዝባዊ ምንባብ ማብቃቴ፥ የመጀመሪያውን፡ የኢትዮጵያ ድርሰት ማኅበር በማቋቋምና በዋና ጸሓፊነት፡ ለብዙ ዓመታት ማገልገሌ፥ ከዚያም፡ በሰዎች ሕግ ደቀ መዝሙርነትና ባለሙያነት፡ ከ“ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መካነ አእምሮ”፡ የምስክሩንና የማዕርጉን ሰነዶች፡ ከአንድም ኹለት ጊዜያት፡ ከራሳቸው፡ ከአጼ ኃይለ ሥላሴ እጅ በመቀበል መመረቄ፡ በእናንተ ዘንድ፡ “እንደተማረ ሰው” እንኳ የሚያስቆጥረኝ አልኾነም ማለት ነው።

ኋላም፡ በአገር ቤት፥ ያውም፡ በደርግ እሥር ቤት እያለሁ፡ በዚሁ፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ላይ በተመሠረተ ጽንሰ ሓሳብ፥ "አዳም እና ሔዋን፡ በኢትዮጵያ!" በሚል፡ አጠቃላይ ርእስና "ኢትዮጵያዊው፡ በእውነት ፍለጋ!" "ኢትዮጵያዊው፡ በእውቀት ፍለጋ!" "ኢትዮጵያዊው፡ በጦብያ ፍለጋ!" በሚሉ፡ በሦስት ጥራዞች፡ ያዘጋጀሁት የጥናትና የምርምር ጽሑፍ፡ ያለትምህርታዊ እውቀት ተዘጋጅቶ፡ ለመጽሓፍነት መብቃት እንደማይችል፡ እንዴት፡ ይህን ቀላልና ግዙፍ እውነታ፡ ለእናንተ ማስተዋል አቃታችሁ?

አዎን! ለነገሩማ፡ ይህንኑ የጥናትና የምርምር ጽሑፌን፥ ሌሎቹንም፡ የእግዚአብሔርን መልእክት የያዙትን መጻሕፍቴን ኹሉ፡ ዛሬ፡ እናንተ፡ ወደኢትዮጵያኛ ልተረጉመው የሚሠቅቀኝን፡ crap የሚለውን የእንግሊዝኛ ጸያፍ የርኵሰት ቃል እስከማስቀጸል የደፈራችሁበት አይደለምን?

ይኸው የጥናትና የምርምር ጽሑፌስ፡ ያ፡ አለቃ አያሌው ታምሩ፡ በሊቀ መንበርነት ይመሩት የነበረው የቤተ ክህነት፡ የሊቃውንት ጉባኤ፡ ከጥንት ተመሥርቶ ሲሠራበት የኖረውንና የተለመደውን ሃይማኖታዊ የጉባኤ ሥርዓት፡ በማናለብኝነት ሥልጣኑ በማፍረስ፥ ምናልባትም፡ ለመጀመሪያ ጊዜ፡ ለእኔ ብቻ መብቴን በመንፈግ፡ አንድ ጊዜም እንኳ ጠርቶ ሳይጠይቀኝ፡ ከዘመኑ የቤተ ክህነት የደርግ ተሿሚ ባለሥልጣኖች ጋር በመመሣጠር፡ ያለአንዳች መግለጫ፡ የመለሰልኝ አይደለምን? "ነፍሳቸውን ይማርና!" አለቃ አያሌው ታምሩ፡ በቀንደኛነት የፈጸሙት፡ ይህ ድርጊትስ፡ እስከዛሬው ጊዜ ድረስ፡ ምን እንደኾነ፡ ሳላውቀው የቆየሁት ድብቅ ነገር አልነበረምን? እርሳቸው፡ ደርግን በመፍራት ይኹን፥ ወይም፡ ስለዘመናዊው የሥነ እውቀት (scientific) አቀራረብ ካለማወቃቸው የተነሣ፡ የጥናቱና የምርምሩ ጽሑፍ ሊገባቸው ስላልቻለ ይኹን፥ ወይም፡ በግል፡ የምቀኝነትና የጥላቻ ዓላማ ይኹን፥ ወይም፡ ለምን እንደኾነ ሳይገባኝ የኖርሁበት ምሥጢር አልነበረምን? እነሆ አኹን ግን፡ እየራሳችሁን፡ "ቀሪን ገረመው" በሚል ስያሜ ሠውራችሁ በማቅረብ፥ በዚያን ጊዜ፡ የአለቃ አያሌው፡ የምሥጢር ተካፋዮችና የሴራ ግብረ አበሮች መኾናችሁንም በማረጋገጥ፡ የዚህን ድብቅ ዱለታችሁን ምንነት፡ በግዳችሁ ገላለጻችሁት።

በባሕር ማዶው ወገን ደግሞ፡ በዩናይትድ ስቴትስ አሜሪካ፡ የሓዋርድና የቫንደርቢልት መካናተ አእምሮ ዘንድ፡ የኢትዮጵያንና የኢትዮጵያዊነትን ምንነትና ማንነት በሚመለከት፡ ያዘጋጀሁት፡ ይኸው የጥናትና የምርምር ዕቅድ፡ በታወቀውና በተለመደው፡ የባዕዳኑ ፀረ-ኢትዮጵያዊነት አቋም ምክንያት፡ ተቀባይነትን ባለማግኘቱ፡ ያ፡ በሰብአዊው ትምህርት አግጣጫ የተጀመረው እርምጃዬ፡ ቢታገድም፡ በመንፈስ ቅዱስ ጸጋና ኃይል የሚካኼደው የእግዚአብሔር ተልእኮ፡ በተጠናከረ መልክና ይዘት ቀጠለ እንጂ፡ ፈጽሞ አልተቋረጠም።

ይኸውም፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መኾኗን፥ ኢትዮጵያውያንም፡ የዚችው፡ በኢየሱስ ክርስቶስ የተገለጠችውና የምትመራው፡ የእግዚአብሔር መንግሥት የኾነችው፡ የኢትዮጵያ፤ እርሷም፡ በድንግል ማርያም የተገለጠችውና ሕያውት የኾነችው፡ የእርሷ ልጆችና ዜጎች፥ አገልጋዮችና ሕዝቦች መኾናቸውን በሚያረጋግጠው፡ በዚያ የጥናትና የምርምር ጽሑፌ ሃይማኖታዊ ጭንጫ ላይ ተመሥርተው የተጻፉት መጻሕፍቴ፡ ለኅትመትና ለሥርጭት በቅተው መገኘታቸው ነው። አዎን! እነዚሁ መጻሕፍት፡ ይኸው እንደሚታየው፡ ለእልፍ አእላፋት ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ በእውነተኛው ማንነታቸው፡ የታማኝነት ሕይወታቸውን ይኖሩ ዘንድ፡ መመሪያዎች በመኾን አገለገሉ፤ ጠቀሙ። ይህንኑ አገልግሎታቸውንና ጠቃሚነታቸውንም፡ እነሆ፡ እንደእናንተ ተቃራኒ ምኞትና ጥረት ሳይኾን፡ በመንፈስ ቅዱስ ባለቤትነትና መሪነት እንደቀጠሉበት ይታያል።

ታዲያ! ይህን የመሰለውን፡ መንፈስ ቅዱስ ያስገኘውን ዘለዓለማዊ ፍሬ ያበረከተ ትምህርታዊ እውቀት፡ ከእግዚአብሔር ካልኾነ በቀር፡ ከሌላ ከየት ሊመጣ ይችላል? ይህን ዓይነቱንስ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ፡ የሰው ትምህርት፥ ወይስ፡ የክፉት መንፈስ ሊያስገኘው ይቻለዋልን? ወይስ፡ ከእግዚአብሔር ከተገኘው ትምህርትና እውቀት ይልቅ፡ የሰውኛው፥ ወይም፡ ከክፉት መንፈስ የሚመነጨው "ይበልጣል!" ሊባል ይሞከር ይኾን? በእናንተ ዘንድ ግን፡ "እግዚአብሔራዊው የትምህርት እውቀት ያስገኛቸው ናቸው!" ተብለው የታመነባቸውን፡ ያን የጥናትና የምርምር ጽሑፍ፥ እርሱ ያስከተላቸውንም፡ እነዚያን መጻሕፍት፡ በዚያ ተቃራኒ መልክ ማየታችሁና ለዚያ አስነዋሪ ግምታችሁ መዳረጋችሁ፡ የእናንተኑ፡ የየራሳችሁን፡ ማንነትና ምንነት፥ ማለትም፤ የማን ወገኖች መኾናችሁን ገልጦና አረጋግጦ የሚያስታውቅ ከመኾኑ በስተቀር፡ ሌላ፡ አንዳችም ረብኅ የለውም።

በመጨረሻ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት በኾነችው፡ በኢትዮጵያ፡ በቤተ ክህነቷ ውስጥ ብቻ ሳይኾን፡ በቤተ ሕዝቧና በቤተ ምልክናዋም ውስጥ፡ የአዲስ አበባ ደቡብ ክፍልን ሕዝብ በመወከል፡ በመናገሻ ከተማዪቱ ምክር ቤትና በብሔራዊው የሕግ መምሪያ ምክር ቤት ውስጥ፡ በሕዝብ እንደራሴነት፥ በአኸስም አውራጃ አስተዳዳሪነትና በሕግ መወሰኛ ምክር ቤት፡ በአባልነት፥ እንዲሁም፡ ዋና መሥሪያ ቤቱ፡ በጄኔቫ ከተማ የኾነው፡ የዓለም የሕዝብ ምክር ቤቶች ኅብረት፡ የኢትዮጵያው አጠቃላይ ብሔራዊ ምክር ቤት ሊቀ መንበር (President) በመኾን ለማገልገል፡ በሕዝብ ምርጫና በመንግሥት ሹመት፡ ለእነዚህ የኃላፊትና የሥልጣን ወንበሮች በቅቻለሁ። ደግሞም፡ በተለያዩ ጊዜያት፡ እነዚህኑ፡ ቤተ ሕዝቡን፥ ቤተ ምልክናውንና ቤተ ክህነቱን በመወከል፡ በአያሌ፡ የዓለም-አቀፍ ጉባኤዎች ላይ ተካፋይ ኾኛለሁ።

ታዲያ! በእነዚህ የኃላፊነት ወንበሮች ላይ ተቀምጦ ለማገልገል የሚያስችለው፥ ለዚህ የአገልግሎት ምርጫና ሹመትም የሚያበቃው፡ ተገቢውና አስፈላጊው ትምህርታዊውና እውቀታዊው ሙያ፡ ለአንድ ሰው ካልኖረው በስተቀር፡ ይህ፡ የኃላፊነት ሥራና ሥልጣን፡ እንዴት ይሰሰጠዋል? አይሰጠውም።

ለእነዚያ አገልግሎቶች ያበቃኝ መንፈስ ቅዱስስ፡ ባሰማራኝ የተልእኮ ቦታዎች ኹሉ፡ በእኔ መሣሪያነት፡ ያስገኘቸውንና እስከዛሬ የቀጠሉትን ቋሚ የሥራ ፍሬዎች፡ እናንተና ሌላው ኹሉ የሚያውቀው አይደለምን? የዚህ መልሱ፡ በአዎንታ የሚደመደም ሲኾን፡ ምናልባት፡ እናንተ ብትክዱት፡ ሥራው፡ የእግዚአብሔር ስለኾነና ሰዎች ሊያፈርሱት የሚቻላቸው ስላልኾነ፡ እነሆ፡ እስከዛሬ፡ ራሱ፡ ቆሞ ይመሰክራል።

እንግዴህ፡ እኔ፡ ይህን ኹሉ ለማድረግ የቻልሁት፡ **"ኹሉም፡ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይኾናሉ!"** በሚለው፡ መምህራችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ስለራሱና ስለአማኞቹ በተናገረውና ቅዱሳት መጻሕፍት ባረጋገጡት መሠረት፡ በተፈጥሮም ኾነ በሃይማኖት፥ በምርጫም ኾነ በፍለጋ፡ ከሰው ሳይኾን፥ ወይም፡ ከዚያ ይልቅ፡ "ከእግዚአብሔር ባገኘሁት ትምህርትና እውቀት ነው!" ብዬ ማመንና መመስከር፡ የሚያስኬደኝ አይኾንምን? የእናንተ ሥጋዊ አእምሮ፡ ይህን መለኮታዊ እውነት፡ በሃይማኖት አውቆና ተረድቶ ለመቀበል፡ ዓቅም ቢያንሰውም እንኳ፡ በርግጥ እንደሚያስኬድ ታይቷል፤ ተመስክሩዋልም።

ያም፡ ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ፡ ከእግዚአብሔር ብቻ እየተማሩ፡ መለኮታዊዉን መልእክት፡ ለዓለም እንዳስተላለፉት፡ እንደቀደሙት ቅዱሳን ኢትዮጵያውያን ነቢያት፥ በመንፈስ ቅዱስም ተመልተውና ተመርተው፡ ምሥራቹን፡ ለፍጥረተ ዓለሙ እንዳደረሱት፡ እንደቀደሙት ቅዱሳን ኢትዮጵያውያን ሐዋርያት፡ እኛ የዛሬዎቹ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያትም፡ በኪዳነ ልቡናውና በኪዳነ ኦሪቱ ባሳለፍናቸው ዘመናት፥ ዛሬም በፍጻሜው ዘመን፡ በኪዳነ መንፈስ ቅዱስ፡ ይኸው እየኖርነው ባለነው የምሕረትና የትንሣኤ ሕይወት፡ <u>ከእግዚአብሔር ብቻ እየተማርን፥ በመንፈስ ቅዱስም እየተመራን፡</u> መልካሙን ህልውናችንን፡ እነሆ፡ በመቀጠል ላይ እንገኛለን።

ታዲያ! እናንተ፡ ቅዱሳት መጻሕፍት፡ **"ዓይን እያላቸው፡ የማያዩ! አእምሮ እያላቸው፡ የማያስተውሉ!"** እንደሚላቸው መኾናችሁ ነውን? ይህን ቀላልና ግልጽ እውነታ፡ በቅንነት ተመልክታችሁ፡ ለመረዳት እንዴት ተሣናችሁ?

የመመልከት ጒድለትና የማስተዋል ድክመት ያለባችሁ መኾናችሁን የሚያመለክት፡ ሌላ ድርጊታችሁ ደግሞ አለ፤ ይህም፡ የእኛ፡ የእውነተኞቹ የኢትዮጵያ ልጆች፡ የቅዱሱ ኪዳን ጥንታዊ ቅርሳችንና የጥበቃ ግዳጃችን የኾነውን፡ ይህን፡ **"ኹሉም፡ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይኾናሉ!"** የሚለውን፡ የእግዚአብሔርን ቃል፡ ከነሃይማኖታዊ ምግባሩ፡ ከእኛ፡ ከባለአደራዎቹ እጅ ነጥቃችሁ፡ በዋጋ እንደሚሸጥ ሸቀጥ፡ በቅርቡ ዘመን ለተፈጠሩት፡ ለባዕዳኑ Protestantቶች አሳልፋችሁ ለመስጠት መሞከራችሁ ነው።

ከፈጣሪያችንና ከቅድስት እናቱ፡ በታላቅ አደራ የተረከብነው፡ ይኸው ሃይማኖታዊና ምግባራዊ ይዞታችን፡ በቀደሙት ወገኖቻችን ነቢያትና ሓዋርያት ላይ እንደታየው ኹሉ፡ ዛሬ ባለነው የቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያ ልጆችም ሰውነት ላይ ጸንቶና ተጠብቆ፡ ለፍጥረተ ዓለሙ እያደረስነውና ለመጪው ትውልድም እያስተላለፍነው በምንገኝበት ጊዜ፡ እናንተ፡ "የለም! ይህ፡ 'ከእግዚአብሔር ነው የተማርኩት!' ማለትማ፡ ሰንካላ ምክንያት ስለኾነ አያስኬድም፤ እንዲያውም፡ ይህ ዘይቤ፡ የProtestantቶች እንጂ ነው!" እስከማለት መድረሳችሁ፡ በእርግጥ እጅግ ያስገርማል፤ ያስተዛዝባልም።

እርሱ፡ ራሱ፡ ባለቤቱ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ለራሱ ያደረገውን፥ በአማኞቹ ዘንድ የሚኾነውም፡ "ይኸው ነው!" ብሎ፡ በአምላካዊ ቃሉ ያጸናውን፥ ከዚህም ቃሉ፡ አንዲቱ ነቍጥ እንኳ ብትወድቅ ወይም ብትሻር፡ "ሰማይና ምድር ቢያልፉ ይቀላል!" የተባለለትን፡ ይህን፡ <u>'ከእግዚአብሔር የተማሩ ይኾናሉ!'</u> የሚለውን ቃሉን፡ እናንተ፡ እንዲህ በማስተሓቀር፡ ለማፍረስ መሞከራችሁ፡ ከድፍረታችሁ፡ በንስሓ በመመለስ ፋንታ፡ ያንኑ፡ የአለቃ አያሌው ታምሩን ፈለግ መከተላችሁ አይደለምን?

እዚህ ላይና ከዚህ ጋር በማያያዝ፡ በአንክሮና በተዘክሮ፡ ልናጤነው የሚገባን፡ አንድ ቍም ነገር አለ፤ ይኸውም፡ በእኔ ተጽፈው የቀረቡትና ለሕዝብ የተላለፉት፡ እነዚህ፡ የእግዚአብሔርን እውነት የያዙት መልእክታት፡ በመንፈስ ቅዱስ ከተቃኘ ትምህርትና እውቀት የተገኙ ካልኾኑ በስተቀር፡ እነአለቃ አያሌው ታምሩና እርሳቸውን የመሰሉት፡ አንዳንድ የቀደሙ ሊቃውንት፡ እግዚአብሔር ባደረገውና የኢትዮጵያ በኾነው ሥራው ላይ፡ በባዕዳን ተንኰልና በክፋት መናፍስት ተነቃቅተውና ተደግፈው የፈጸሟቸውን ስሕተቶችና ጥፋቶች፡ ፈልፍሎ ለማውጣትና ለማጋለጥ፥ ለማስተካከልና ለማጽዳትም፡ እንዴት ይቻል ነበር? በእርግጥ አይቻልም ነበር።

እኔስ፡ በእነዚሁ ሥጋውያንና መንፈሳውያን ሊቃውንት መንገድ ተምሬና ተመርቄ፡ ልክ እንደነርሱ ሊቅ መኾኑንና ሊቅ መባሉን ፈልጌውና ኾኜም ቢኾን ኖሮ፡ ዛሬ፡ እኔምኮ፡ "በሊቃውንቱ ጎራ" ውስጥ ገብቼ፡ እነርሱ የኾኑትንና ያደረጉትን፡ ያንኑ ኾኜ፡ አለቃ አያሌው ታምሩና እርሳቸውን የመሰሉት ኹሉ፡ ያደረጉትን ስሕተትና በደል እፈጽም ነበር እንጂ፡ እንዲህ፡ በዛሬው፡ ተልእኮዬ ጸንቼ፥ በሰውኛው ትምህርት ሳልመካና በእርሱ ሳልመራም፡ <u>"የተማርኩት በእግዚአብሔር፤ ከእግዚአብሔር፤ ለእግዚአብሔር ነው!"</u> ብዬ በማመን፡ እንዲህ በቁርጠኛነት፥ ያለፍርሃትና ያለይሉኝታ፡ ተጋድሎዬን እስከዚህ ለማድረስ ባልቻልኩም ነበር። ለዚህ ቸርነቱና ጸጋው፡ እግዚአብሔርን ምንጊዜም አመሰግነዋለሁ።

ደግሞስ፡ ከዚሁ፡ ከእግዚአብሔሩ ቃል ውጪ በኾነ አስተሳሰብና እርሱን በሚቃረን መንፈስ፡ ከሰዎች ተምሮና ተመርቆ፡ በእነርሱው፡ "ሊቅ"፥ ወይም፡ "ሊቀ ሊቃውንት"፥ "ምሁር"፥ ወይም፡ "ሊቀ ምሁራን"፥ እንደባዕዳኑም አጠራር፡ ባለ"Phd Doctor"፥ ወይም "Professor" መባሉ፡ ዓላማውና ጥቅሙ ምንድርነው?

ያን የሰዎች ትምህርት፥ ወይም ሙያ፡ ለራስ በሚበቃ አውቆ፡ ለሌሎች ለመትረፍ ካልኾነ በስተቀር፡ ከቶ፡ ለምን ይጠቅማል?! በእነዚህና እነዚህን በመሰሉት የሰዎች የትምህርት ማዕርጋት የተሰየሙትና የከበሩት ግለሰቦችስ፡ ይህን ማድረግ ከቻሉ፥ አድርገውም ከተገኙ፡ "መልካም አደረጋችሁ!" ተብለው ሊሞገሱ አይገባቸውምወይ? አዎን! በእርግጥ፡ ሊሞገሱ ይገባቸዋል። ነገር ግን፡ ይህን የመሰለውን የባለሙያነት ምግባር፡ እግዚአብሔር በሚያውቀውና በሚወድደው መልክና ይዘት ፈጽመውና የሥራ ፍሬን አበርክተው የተገኙ ስንት ናቸው? ከመቶዎቹ መካከል ስንት ይኾናሉ? አምሳ? ወይስ፡ ሠላሳ? ወይስ አሥር? ወይስ፡ ስንት? እየራሳችሁ ድረሱበት።

በዚህ ረገድ፡ በእነዚህ የሰዎች ትምህርት ማዕርጋት ውስጥ ከተፈረጁት ሊቃውንትና ምሁራን የሚጠበቀውን ምግባርና የሥራ ፍሬ፡ እኔ፡ አስገኝቼ ከተገኘሁ፡ የእኔ፡ በእነዚህ ማዕርጋት ተመርቄና ከብሬ መገኘት፥ ወይም፡ አለመገኘት፡ ምን ጥቅም አለው? የለውም። በእናንተና እናንተን በመሰሉ ዘንድ ግን፡ በእርግጥ ለውጥ፥ ወይም፡ ልዩነት አለው። ምክንያቱም፡ ይህን፡ **"ኹሉም፡ከእግዚአብሔር ዘንድ የተማሩ ይኾናሉ!"** የሚለውን የእግዚአብሔርን ቃል ስለማታምኑበትና ከዚህ ይልቅ፡ እናንተና እናንተን የመሰሉት ኹሉ፡ የምታምኑበትና የምታመልኩት፡ የሰዎችን ትምህርትና ማዕርግ፥ ሥራና ሥርዓት ስለኾነ ነው።(ዮሐ፤፮፥ ፵፭።)

እኔም፥ ራሴን፡ ባለ"Phd Doctor"፥ ወይም "Professor" አድርጌ፥ ወይም፡ "ነኝ!" ብዬ፡ ቀርቤ ቢኾን ኖሮ፡ እኔንና የምናገረውን ቃሌን፥ የምጽፈውንም አሳብ ኹሉ፡ በቀላሉ አምናችሁበት ልትቀበሉት በቻላችሁ ነበር፤ እናንተ እኮ፡ የእግዚአብሔር ከኾነው ይልቅ፡ የሰው ለኾነው፡ ቅድሚያንና ብልጫን፥ ክብርንና ዋጋን የምትሰጡ ናችሁ! ስለዚህም፡ <u>አንዳንዶች፡</u> ያን፡ የሰዎች ማዕርግ ያገኙት፡ በገንዘብና በሓሰት፥ በድጋፍና የቀደሙ መጻሕፍትን በመጠቃቀስ ብቻ፥ እንዲሁም፡ በአደንዛዥ ዕፅዋት ኃይልና በልዩ ልዩ ዘዴ መኾን ያለመኾኑን እንኳ ሳታጣሩ፡ "ባለPhd Doctor ነኝ!" ብሎ በድፍረት የሚቀርበውን ኹሉ፡ በጭፍን ትቀበላላችሁ፤ በዚሁ አስመሳይ ማዕርጋቸውም ምክንያት፡ በአላዋቂዎች ዘንድ፡ መከበርንና መመለክን የሚፈልጉ ግለሰቦችን በማወደስ፡ እኒህኑ ግለሰቦች የማክበር ብቻ ሳይኾን፡ የማምለክም ባዕድ መንፈስ የተጠናወተው ትውልድ አባሎች መኾናችሁን ታረጋግጣላችሁ።

ለነገሩ፡ ከሰው ባገኙትና በተመረቁበት ትምህርት፥ በእነዚህም፡ የሰዎች የትምህርት ማዕርጋት ኾኖ፡ እኔ አዘጋጅቼ ያቀረብኋቸውን የመሰሉ፥ በእግዚአብሔር እውነት ላይ ተመሥርተውና በእርሱ ቅዱሳት ቃላቱ ታጅበው የተላለፉ መለኮታውያን መልእክታትን የያዙ (እናንተ ግን፡ "crap" የሚለውን አስነዋሪ የርኵሰት ስም የሰጣችኋቸውን) መጻሕፍትን ለማበርከት፡ በመሠረቱ አይቻልም።

ለመኾኑ፡ ይህን እውነታ ታውቁታላችሁን?! "ከእግዚአብሔር ዘንድ የተማሩ ኹሉ"፥ ደግሞም፡ "ከእግዚአብሔር ዘንድ የተማርን ነን!" የሚሉ ኹሉ፥ በማናቸውም የእውቀት መስክ፡ ከምድራውያንና ከሥጋውያን፥ ከዓለማውያንና ከመናፍስታውያን ሊቃናተ ሊቃውንት ይልቅ፡ እጅግ የሚበልጡ መኾናቸውን፡ በእርግጥ ታውቃላችሁን?! አታውቁትም። አውቃችሁት ቢኾንማ ኖሮ፡ እኔ፡ ለአለቃ አያሌው ታምሩ በጻፍሁት፡ በዚያ ደብዳቤዬ ምክንያት፡ ያን ያህል፡ የቁጣና የብስጭት እሳት በላያችሁ ባልነደደ ነበር። በእኔም ላይ፡ ያን ያህል፡ የነቀፌታና የዘለፋ ናዳን፡ ባላወረዳችሁብኝ ነበር። አዎን! ይህን የመሰለው ተጻራሪ መንፈስ የታየባችሁ፡ ያን፡ የእግዚአብሔርን እውነታ ስላላወቃችሁ ነውና፡ እንግዴህ፡ እውነታው፡ ይህ መኾኑን፡ ከዛሬ ጀምሮ እወቁት!

"ከእግዚአብሔር ዘንድ የተማሩ ኹሉ"፥ ደግሞም፡ "ከእግዚአብሔር ዘንድ የተማርን ነን!" የሚሉ ኹሉ፥ በማናቸውም የእውቀት መስክ፡ ከምድራውያንና ከሥጋውያን፥ ከዓለማውያንና ከመናፍስታውያን ሊቃውንት ይልቅ፡ እጅግ የሚበልጡ መኾናቸውን አታውቁምን? ይህ እውነታ፥ ይህ እውቀት፡ ለእናንተ፡ ከእምነታችሁ ጉድለት የተነሣ፡ ሊከሠትላችሁ አይቻልም።

በንጽሓ ነፍስና በንጽሓ ሥጋ፥ በእውነትና በመንፈስ ቅዱስ የአምልኮ ሕይወትም ውስጥ ለሚገኙት፡ ለቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያ ልጆች ኹሉ ግን፡ ግልጽ ነው። ይህም የኾነው፡ እግዚአብሔር፡ ጥንቱኑ፡ በመልኩ የፈጠረውን፡ "አዳምን"፡ ማለትም፡ ወንድንና ሴትን አንድ አድርጎና አስተካክሎ የያዘውን ሰብኣዊ ፍጡሩን፡ "ከእኛ እንዳንዱ ኾነ!" በማለቱ፡ እኒሁ፡ የቅዱሱ ኪዳን፡ የኢትዮጵያ ልጆች፡ ንጽሓ ጠባያቸውን ጠብቀው ስለተገኙ ነው። ስለዚህ፡ እኒህ፡ የኢትዮጵያ ልጆች፡ እንደእግዚአብሔር ለማሰብ፥ ለመናገርና ለማድረግ፡ የሚችሉበት ጸጋና ኃይል፡ ከእግዚአብሔር፡ በተፈጥሮ የተሰጣቸው መኾኑን፡ ይህ እውነታ፥ ይህ እውቀት ያረጋግጣል።

ከዚያም በላይ፡ ወንዶቹ፡ በሥጋ በተወለዱ፡ በ፵፥ ሴቶቹም፡ በ፹ ቀናቸው፡ በምሥጢረ ጥምቀት፡ ከእግዚአብሔር በውኃና በመንፈስ ሲወለዱ፡ ከነፍሳቸውና ከሥጋቸው አካላትና ባሕርያት በተጨማሪ፡ የመንፈስ ቅዱስን አካልና ባሕርይ ስለለበሱ፡ በዚህ ጊዜና ከዚህ የማንነት ብቅዓታቸው የተነሣ፡ ትምህርታቸውና እውቀታቸው፡ የሰዎች ከኾነው አልፎና እጅግ መጥቆ፡ ከፍጹምነት ደርሷል።

"ከእግዚአብሔር ዘንድ ከተማሩት" እና "ከእግዚአብሔር ዘንድ የተማርን ነን!" ከሚሉትም መካከል፡ የዚህን ዓለም፡ ሥጋዊና ሰብኣዊ ትምህርት ተምረውና በሊቅነት፥ ወይም፡ በሊቀ ምሁርነት ተመርቀው፡ ማለትም፡ በባዕዳኑና በዛሬው ዓለም ዘንድ በሚያስከብረው አጠራር፡ ባለ"Phd Doctor"፥ ወይም "Professor" ተብለው፡ ነገር ግን፡ ያ እውነተኛው ውሳጣዊው ማንነታቸው፡ በእየራሳቸውና በመንፈስ ቅዱስ ዘንድ ብቻ በኅቡዕ ታውቆ፥ ለሌላው ሰብኣዊ ፍጡር ግን፡ በምግባራቸው ተገልጾ፡ በትሕትና እየሠሩ የሚኖሩ አሉ። እኒህም፡ እንዲህ የሚሉት ናቸው፦

“እኛ፡ ‘ኹሉም፡ከእግዚአብሔር ዘንድ የተማሩ ይኾናሉ!’ በሚለው የእግዚአብሔር ቃል አምነን፡ ከፈጣሪያችን ያገኘነውን፡ ይህንኑ ትምህርትና እውቀት፡ የህልውናችንና የሕይወታችን፥ የአገልግሎታችንና የሙያችን መሠረትና መመሪያ፥ ዓላማና ግብም አድርገን የምንኖር ነን! ከምድራውያኑና ከሥጋውያኑ፥ ከዓለማውያኑና ከመናፍስታውያኑ ተምረን፡ በባለሙያነት የተመረቅንበትን ባለማዕርግ ትምህርት ያገኘነው፡ ለዘመኑ ሰብኣዊና ዓለማዊ፥ ሥጋዊና ምድራዊ አገልግሎት፡ የሰላ መሣሪያ እንዲኾነን፥ ለበለጠ ፍሬያማ ተግባርም እናውለው ዘንድ ከመኾኑ በቀር፡ ሌላ፡ ከዚህ ያለፈ ጠቀሜታ የለውም!”

አትመለከቱምን? የቤተ ክህነቱ ተጠሪ የኾነው እጨጌው፥ ወይም፡ ርእሰ ሊቃነ ካህናቱ እንኳ፡ “ትምህርቱና እውቀቱ ባይኖረውም፡ ያን፡ ወደፊት ያገኘዋልና፥ በጸሎቱ፡ ለሕዝቡና ለአገሩ፡ የበለጠ ስለሚጠቅም፡ በሃይማኖቱና በምግባሩ፥ በመንፈሳዊነቱም፡ የበቃ ኾኖ የተገኘው ደግ ሰው” እንዲሾም የሚፈቅደውን፥ እናንተ በምታምኑበት፡ በግብፆቹ ፍትሐ ነገሥት ውስጥ ያለውን አንቀጽ አታስታውሱትም? አታስተውሉትምን?

ከዚህ በላይ፡ ባጭር በተሰጠው ሓተታ እንደተብራራው፡ በአንደኛው መደብ፡ ይህ፡ የእግዚአብሔር እውነታ፡ ማለትም፡ “ኹሉም፡ከእግዚአብሔር ዘንድ የተማሩ ይኾናሉ!” የሚለው የእግዚአብሔር ቃል ምንነትና ከሰው የእውቀት ሊቅነት ይልቅ፡ የእግዚአብሔር ሞኝነት የሚበልጥ ስለመኾኑ የሚናገረው ይገኛል፤ በኹለተኛው መደብ ደግሞ፡ የእኒህ ኹሉ የእግዚአብሔር ታማኞች ወገኖች፡ ማለትም፡ “ከእግዚአብሔር ዘንድ የተማሩት” እና “ከእግዚአብሔር ዘንድ የተማርን ነን!” የሚሉት ማንነት፥ በአጠቃላይም፡ የእነርሱ የመንፈስ ቅዱስ እውቀት፡ ከሰዎችና ከመናፍስታውያኑ ሊቃውንትነት ይልቅ፡ በእጅጉ የሚበልጥ ስለመኾኑ የሚያስረዳው ይገኛል። ይህ ቍም ነገር፡ እንዲህ በሚለው፡ በሓዋርያው ቃል ተካትቶ ተገልጧል፡-

“ይህ ትምህርታችን፡ ከሰው የተገኘ ትምህርት አይደለም፤ የአነጋገር ጥበብም አይደለም፤ መንፈስ ቅዱስ የገለጸው ትምህርት ነው እንጂ። መንፈሳዊ ጥበብም፡ ከመንፈስ ቅዱስ የሚኾነውን፡ መርምረው ለሚያውቁ፡ ለመንፈሳውያን ነው።

“ለሥጋዊ ሰው ግን፡ የእግዚአብሔር መንፈስ ነገር፡ ሞኝነት ይመስለዋልና፡ አይቀበለውም፤ በመንፈስ የሚመረመርም ስለኾነ፡ ሊያውቀው አይችልም። መንፈስ ቅዱስ ያደረበት ሰው ግን፡ ኹሉን ይመረምራል፤ እርሱን ግን፡ የሚመረምረው የለም። የእግዚአብሔርን አሳብ፡ ማን ያውቃል? መካሩስ፡ ማን ነው? እኛ ግን፡ ክርስቶስ የሚገልጠው እውቀት አለን።” (፩ቆሮ. ፪፥ ፲፫-፲፮።)

ይህ ኹሉ እውነታ፡ አስቀድሞ፡ በእግዚአብሔር ቃል ተገልጾ የተነገረ ሲኾን፡ ነገር ግን፡ ይኸው የመለኮት ቃል፡ በእናንተ ዘንድ፡ አንዳችም ተደማጭነትና ተቀባይነት፥ ተአማኒነትና ተፈጻሚነት ሳያገኝ መኖሩ፡ ከቶ አያስደንቅም።

ምክንያቱም፡ እናንተ፡ የምትከተሉትና ምርጫችሁ፡ ለየራሳችሁ ሥጋዊ ፍላጎትና ዓላማ የሚስማማችሁንና የሚጠቅማችሁን፡ ሰብኣዊ የኾነውን ኹሉ እንጂ፡ የእግዚአብሔር የኾነውን፡ በጭራሽ ስለማትፈልጉት፥ እንዲያውም፡ ስለምትጠሉትና ስለምትቃወሙት መኾኑ፡ ይኸው፡ የየራሳችሁ፡ ኢ-ጦማር መሰከረባችሁ።

የእግዚአብሔርም ቃል፡ ይህንኑ ፀረ ክርስቶስነታችሁንና ፀረ ኢትዮጵያነታችሁን፡ እንዲህ ሲል አረጋገጠባችሁ፤ እርሱም፡- **"ስለወጋችሁ፡ የእግዚአብሔርን ቃል የምትሽሩ እናንተ ግብዞች! 'ይህ ሕዝብ፡ በከንፈራቸው ያከብሩኛል፤ በልባቸው ግን፡ ከእኔ እጅግ ይርቃሉ!' ሲል፡ ኢሳይያስ፡ በእናንተ ላይ መልካም ተናገረ!"** የሚለው መለኮታዊ ቃሉ ነው። (ማቴ. ፲፭፥ ፯-፱።)

**፬ኛ.** You have also mentioned in the letter and on other writings that you do not accept the Ethiopian Orthodox Church and you are not an Orthodox. So that prevents you from commenting on the church's status or anything related to it. Everybody knows that you do not live by the rules of the church. You have created your own denomination like the Protestants do, you celebrate the mass and hold church services in your own house. That's way out of the teachings of the church. **ላላችሁት፡-**

እውነተኞቹ፡ የቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያ ልጆች፡ የምናምንባትና የምንኖርባት፥ የምናገለግላትና የምንጋደልላት እኮ፡ <u>ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት</u> ናት። እርሷም፡ በእግዚአብሔር መልክ ተፈጥሮ፡ በነፍስ፥ በሥጋና በመንፈስ ሦስት ባሕርያቱና አካላቱ፡ እንደእግዚአብሔር፡ በአንድነትና በሕያውነት ለመኖር የመቻል ኃይልና ብቅዓት በተሰጠው፡ በፍጹሙ ሰው ምሳሌነት፡ በተዋሕዶ ምሥጢር፡ አንድ የኾኑ፡ ቤተ ሕዝብ፥ ቤተ ክህነትና ቤተ ምልክና የተባሉት የአገልግሎት ዘርፎች ያሏት ናት።

በዚህ አቋማችንና ሥርዓታችን መሠረት፡ እኛ፡ "የኢትዮጵያ፡ ቤተ ክርስቲያን" የምንላት፡ ይህችኑ፡ የ፯ሺ፭፻፪ ዓመታት ዕድሜ ያላትንና የኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ አንዷ ቅርንጫፍ አካል የኾነችውን፡ ቤተ ክህነትን ነው እንጂ፡ ከክርስቶስ ልደት በኋላ፡ በ፬ኛው ምዕት ዓመት ግድም፡ ግብፃውያን፡ "በኢትዮጵያ መሥርተን አቋቋምናት!" ብለው የሚናገሩላትን፥ የእነእርሱ ተገዢ መኾኗንም ለማረጋገጥ፡ "Orthodox" የሚለውን ስም ሰጥተው፡ የሚመሩዋትን፥ እናንተና እናንተን የመሰሉትም፡ ይህንኑ ሓሰት አጽንታችሁ፡ በሕግም አውጃችሁ የተቀበሏችኋትን፡ በ፩ሺ፮፻ ዓመታት ዕድሜ የተወሰነችውን አይደለም።

እናንተ፡ በተገዢነት ተከትላችሁና አምናችሁበት፡ የምትኖሩበትና የምትሠሩበት፡ ዘመን አመጣሹና ጊዜ የወለደው፡ የባዕዳኑ ሰብኣዊ ፍልስፍና፡ በእኛ ዘንድ፡ ፈጽሞ ተቀባይነት የሌለው መኾኑን፡ እስካኹን አላወቃችሁት እንደኾነ፡ እንግዴህ ወዲህ እንድታውቁት ይኹን! ይህም፡"ሃይማኖትና ዓለማዊው ፈሊጥ"፤ "ሥጋዊውና መንፈሳዊው"፥ "ቤተ ክርስቲያንና መንግሥት" ፈጽመው የተለያዩ፡ ኹለት አካላት እንጂ፡ በተዋሕዶ፡ አንድ አካል አይደሉም!" የሚለው፡ የሰዎች የአገዛዝ ዘዴ ነው።

ከዚህ እውነታ የተነሣ፡ <u>እውነተኞቹ ተዋሕዶዎች፡</u> <u>በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥትነት</u> የምናምነው፡ እኛ፡ የቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያ ልጆች እንጂ፡ እናንተ፡ "የግብፅ Orthodoxሳዊነት"ን፥ ከቀዳሚነቱና ከበላይነቱ ጋር፡ በተገዢነት የተቀበላችሁት፡ እናንተ አይደላችሁም።

ይህ ዓቢይ ቁም ነገር፡ የኢትዮጵያዊነት አቋማችን መሠረታዊ ጉዳይ፥ እናንተም፡ በትክክል ልትገነዘቡት የሚገባችሁ ስለኾነ፡ እዚህ ላይ፡ በበለጠ ላብራራላችሁ፡ የሚያስፈልገኝ ኾኗል፤ ይህም፡-

-ለኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግሥት አቋም፡ ግንድ ከኾነው፡ ከቤተ ሕዝቡ፡ ከሠረፁት፡ ከኹለቱ ዓበይት ቅርንጫፍ አካሎች መካከል፡ ኹለተኛው፡ ሥጋዊዉን አገልግሎት፡ ለቤተ ሕዝቡ የሚሰጠው፡ ቤተ ምልክናው ሲኾን፡ አንደኛዋ ደግሞ፡ መንፈሳዊዉን አገልግሎት፡ ለቤተ ሕዝቡ የምታበረክተው፡ ቤተ ክህነት መኾኗን፥

-ዛሬ ያለችው፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን፡ ይህችው ቤተ ክህነት መኾኗን፥

-እርሷም፡ ከጠራውና ከቀናው፡ ከፍጹሙ የተዋሕዶ ሃይማኖቷና ምግባርዋ ጋር፡ በቋንቋዋና በሥነ ጽሕፈቷ፥ በዜማዋና በኪነ ጥበቧ፡ በሥርዓቷና በቀን አቆጣጠርዋ፥ በጥንታዊነቷና በሌሎቹ ባህሎቿ ኹሉ፡ እየራሳቸውን "Orthodox" እያሉ ከሚጠሩት፡ የውጭ አብያተ ክርስቲያናት ጋር ምንም ዓይነት መመሳሰል የሌላት ኾና፡ በራሷ ማንነት፡ ታውቃ የኖረች መኾኗን፥

-እንዲህ እንደመኾኗም፡ የእናንተ ሳትኾን፡ ከዚህ ኹሉ ሕያዋን ቅርሶቿና ሀብቶቿ ጋር "የእኛ ናት!" የሚለውን ሃይማኖታዊ እውነታ፡ እንደገና ማመልከት ነው።

ታዲያ፡ እንዲያ ካልኾነ፡ እኛ፡ ይኸው፡ መስቀሉን ተሸክመን፡ ዛሬ፡ እንዲህ፡ በገድል ጽናት የምንቃተልላት፡ ለምንድር ነው? እርሷን፡ እናንተን ከመሰሉ፡ የውስጥ የክፋት ኃይላትና ከውጭዎቹ ባዕዳን ተጻራሪዎቿ፡ የግዞት ቀንበር፡ ነጻ ልናወጣት አይደለምን? ለዚህ መኾኑንማ፡ ኹሉም ሊያውቀው የሚገባ ነው።

በመምህርነቱና በአርአያነቱ፡ በታማኝነት የምንከተለው፡ መለኮታዊው መሪያችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በዚህ ረገድ፡ ራሱ ፈጽሞት፥ እኛንም እንድናደርግ የሰጠንን መመሪያ፡ አውቀነው፡ ይኸው፡ እየሠራንበት እንገኛለን። እርሱ እኮ፡ በዘመኑ የነበረችውን፡ ራሷን፡ የአይሁድን ቤተ ክህነት (ቤተ መቅደስ)፡ **"'ቤቴ፡ የጸሎት ቤት ይኾናል!' ተብሎ ተጽፏል፤ እናንተ ግን፡ የወንበዴዎች ዋሻ አደረጋችሁት!"** ብሎ፡ በርኵሰት የማሰነ ኹለንተናዋን፡ በግዘፍ ጠራርጎ፡ በንጽሕና ሽለማት፥ በመጨረሻም፡ በሕማማተ መስቀሉና በፈሰሰው ደሙ ዋጅቶ፡ በቅድስና አስጌጣት እንጂ፡ ያችን ትቶ፡ ሌላ ቤተ ክህነት፥ ሌላ ቤተ መቅደስ እኮ አላቋቋመም። (ሉቃ. ፲፱፡ ፵፮።)

የዛሬዪቱ፡ የእኛዋ ቤተ ክህነትም እኮ ያቺው ናት! ቀድሞ፡ በዘመነ ብሉይ፡ በኪዳነ ልቦና፡ በኢየሩሳሌም፡ በእነመልከ ጼዴቅ ተመሥርታና በመካከሉ፡ በኪዳነ ኦሪት፡ በእነሰሎሞን ታንፃ፡ በእውነተኞች ታማኞች ካህናቷ ስትገለገል የቆየችው እኮ ናት፡ የእኛዋ ቤተ ክህነት!

ከዚያም፡ በየትውልዱና በየዘመናቱ በሚነሡ፡ በእነዚያ አንገተ ደንዳኖች አይሁድ ዐመፅ፥ ክህደትና የአምልኮ አመንዝራነት ኃጢአት ጠንቅ እየማሰነች፡ የኋላ ኋላ፡ በባቢሎናውያን የቅጣት ሠይፍ ፈርሳ ከመደምሰሷ በፊት፡ ታቦተ ጽዮን፡ በእግዚአብሔር ጥበባዊ ዕቅድ፡ ኢትዮጵያዊቷ ንግሥት ማክዳ፡ ከባለቃል ኪዳኑ እስራኤላዊ ንጉሥ፡ ከዳዊት ልጅ፡ ከሰሎሞን በወለደችው፡ በቀዳማዊ ምኒልክ ምክንያት፡ ወደኢትዮጵያ ተመልሳ የመጣችው እኮ ናት፡ የእኛዋ ቤተ ክህነት!

በመጨረሻ፡ በዘመነ ሓዲስ፡ በኢትዮጵያዊቷ፡ ቅድስት ድንግል ማርያምና በኢትዮጵያዊው ልጇ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ እስከተከሠተው ኪዳነ መንፈስ ቅዱስ ድረስ፡ በመጀመሪያዪቱና በጥንታዊቷ ኢትዮጵያዊት ቤተ መቅደስ የኖረችው እኮ ናት፡ የእኛዋ ቤተ ክህነት!

የቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያ ልጆችም፡ **"ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በአበው ልቦና በመሠረታት፥ በነቢያት ቃል ባጸናትና በሓዋርያት ጉባዔ በፈጸማት፥ የእርሱ ሥጋና ደም፡ ለመሥዋዕትነት በሚቀርብባትና የመንፈስ ቅዱስ ጸጋዎች በሚሰጡባት፡ በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እናምናለን፡፡"** እያልን በዘወትሩ፡ የሃይማኖት ጸሎታችን የምናወድሳት፥ "ቤተ መቅደስ"፥ ወይም፡ "ቤተ ክርስቲያን" እየተባለች፡ በተለያየ ስም የምትጠራው፥ በፍጥረት ልደትና ዛሬ፥ ወደፊትና ለዘለዓለምም፡ ሕያውት ኾና የምትቀጥለው፡ ያችው፡ አንዲቱ ቤተ ክህነት ናት እኮ፡ ይህች፡ የእኛዪቱ ቤተ ክህነት።

እኛ፡ ከጥንት የተመሠረትነውና የምንመራው፡ በፍጥረት መጀመሪያ፡ በአዳምና ሔዋን የተከሠተችው፡ ቀዳማዊቷና ጥንታዊቷ ኢትዮጵያ፡ በእግዚአብሔር መንግሥትነቷ፡ በቀጥታና በሰባቱ ቅዱሳት ኪዳናት አማካይነት፡ ከፈጣሪዋ በተረከበቻቸው፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖትና ምግባር፥ አምልኮና ሥርዓት እንጂ፡ በግብፅ Orthodox ቤተ ክርስቲያን ተፅዕኖ፡ ወደኢትዮጵያ ሠርገው በገቡብን፡ የግብፅ፥ ወይም፡ የግሪክ Orthodox ሃይማኖትና ምግባር፥ አምልኮና ሥርዓት አይደለም።

እንዲህ ከኾነ፡ ሃይማኖትንና ምግባርን፥ አምልኮንና ሥርዓትን በሚመለከት፡ እውነተኞች የኾንን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ኹሉ፡ አንድ ኾነን፡ ልንፈጽመው የሚገባን ታላቅ ግዳጅ አለ! ይኸውም፦

በቅድሚያ፡ እናታችን ኢትዮጵያና እኛ ልጆቿ፡ ንጹሕ መስቀሉን በመሸከም፡ በቀጥታ፡ ከእግዚአብሔር ካገኘነው፥ ከጠራውና ፍጹም ኢትዮጵያዊ ከኾነው፡ ከቅዱሱ ኪዳን የተዋሕዶ ሃይማኖትና ምግባር፥ አምልኮና ሥርዓት ጫንቃችን ላይ፡ የእኛ ሳይኾን የጨመርነውን፡ የእነርሱ የኾነውንና ሠርጎ የገባውን፡ ማናቸውንም ዓይነት፡ ባዕድ የኾነ፡ የትምህርትና የአስተሳሰብ፥ የባህልና የወግ ክፉ ቀንበር፡ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል፡ አሽቀንጥረን ማስወገድ ነው።

ቀጥሎ፡ ለሰፊ ዘመናት፡ በባዕዳኑ ስም ስትጠራ የኖረችውን፡ ይህችኑ፡ የእኛዪቱን ቤተ ክህነት፡ ጥንቱኑ፡ ከመሠረቱ፡ የኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ አንዲቱ ቅርንጫፍ አካል ኾና ለኖረችበት፡ ለፍጹሟ ኢትዮጵያዊት ቤተ ክህነትነቷ የምትበቃ ኾና እንድትገኝ ማድረግ ነው።

ስለዚህ፡ ፈቃደኞች ከኾናችሁ፡ እናንተ እና እናንተን የመሰሉት ኹሉ፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ንስሓ፡ እየራሳችሁን በማጥዳትና በማስተካከል ተመልሳችሁ፡ የእኛ በኾነችው፡ በዚችው፡ በእውነተኛዪቱ የኢትዮጵያ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እንድትታቀፉ መኾን፥ አለዚያ፡ "አይኾንልንም!" ካላችሁ ግን፡ የኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ አንዲቷ ቅርንጫፍ አካል ከኾነችው፡ ከዚችው፡ ቤተ ክርስቲያናችን፡ "Orthodox" ከሚለው ባዕድ ስያሜያችሁ ጋር፡ እየራሳችሁን በማግለል፡ እንድትለዩ ትጠየቃላችሁ። ዋናው ግንዳቸው፡ በውጭው አገራቸው ኾኖ፡ ቅርንጫፋቸውን፡ በተለያየ ስም፡ በኢትዮጵያ አቋቁመው እንደሚሠሩት፡ እንደሌሎቹ፡ ባዕዳን አብያተ ክርስቲያናት፡ "በኢትዮጵያ፡ የግብፅ Orthodox ቤተ ክርስቲያን" ተብላችሁ፡ በህልውናችሁ መቀጠል ትችላላችሁ።

እኛ፡ የኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አባሎችና አገልጋዮች፡ አስፈላጊውንና ተገቢውን አገልግሎት እንድናበረክት ስንጠየቅ፡ ያን፡ ግዳጅ፡ ለተገልጋዩ ጠያቂ፡ በተቻለን መጠን፡ ከመፈጸም በስተቀር፡ በዚችው፡ ግብፃዊት በኾነችው ቤተ ክርስቲያናችሁ ጉዳይ ውስጥ፡ ባለፈው፡ የገባንበት፥ ዛሬም ገብተን እያደረግን ያለነው፥ ወደፊትም፡ የሚያገባን ኹኔታና ምክንያት፡ ከቶ የለም።

ያን፡ ለአለቃ አያሌው ታምሩ የላክሁትን ደብዳቤም ቢኾን፡ እንድጽፍ ያስገደደኝ መንሥኤና ምክንያት ምን እንደኾነ፡ እናንተ፡ እውነታውን፡ በትክክል ለማስተዋል ስለተሣናችሁ እንጂ፡ በደብዳቤው ላይ፡ በግልጽ ሠፍሮ ይነበባል፤ ያም፡ እርሳቸው፡ ስሜን በማንሣትና ተልእኮዬን በመዝለፍ፥ በተለይም፡ መለኮታዊ የኾነውን፡ መላውን የእግዚአብሔርን ሥራ ከመንቀፍ ጋር፡ በቀጥታ ለማፍረስ የሚሞክር ኃይለ ቃልን፡ በመጽሓፍ ጽፈው በማውጣታቸውና ይኸው ጽሑፋቸው፡ ታትሞና ተሠራጭቶ፡ ለእኔም በመድረሱ፡ "ለዚያ፡ መልስ መስጠት የሚገባኝ በመኾኑ ነው!" ተብሎ፡ እዚያው ላይ፡ በሚበቃ ተብራርቷል። ይህ አድራጎቴ፡ በራሴ ተነሣሥቼ የፈጸምሁት አይደለም።

እዚህ ላይ፡ ሊነሣ የሚገባው፡ አንድ የሚገርምና ግራ የሚያጋባ እንቆቅልሽ አለ፤ ይኸውም፡ አለቃ አያሌው ታምሩም ኾኑ፡ እናንተ (በእርግጥ፡ የርሳቸው፡ ታማኞች ወገኖች ከኾናችሁ)፡ እንዲህ፡ ሽንጣችሁን ገትራችሁ፡ "በኢትዮጵያ፡ የግብፅ Orthodox ቤተ ክርስቲያን"፡ ስለተባለችው፡ ስለዚች ቤተ ክህነት፡ ጥብቅና ቆማችሁ፡ መናገራችሁ ነው፤ እርሳቸው፡ በሕይወተ ሥጋ ሣሉ፡ ይህችኑ ቤተ ክርስቲያን፡ አላወገዟትምን? እርሷስ፡ እርሳቸውን፡ አላወገዘቻቸውምን? እንዲህ፡ እርስ በርሳቸው ስለተወጋገዙ፡ በውግዘት ተለያይተዋል ማለት ነው። ይህም መለያየት፡ በቀብራቸው ጊዜ በተግባር ተፈጽሞ፡ እውነታው ተረጋግጧልና፡ ማስተባበል ከቶ አይቻልም።

ከላይ፡ ቀደም ብሎ እንደተገለጸው፡ እኛ፡ የቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያ ልጆች፡ በአኹኑ ጊዜ፡ በመላው ፍጥረተ ዓለም፥ "ኢትዮጵያ" ተብላ በተከለለችው ምድር ጭምር ላይ የሰፈነችው፡ የእግዚአብሔር መንግሥት የኾነችው፡ የኢትዮጵያ፡ ማለትም፡ የቅድስት ድንግል ማርያም ልጆችና አገልጋዮች፥ ዜጎችና ሕዝብ ነን። እንደProtestantቶቹ፥ ወይም፡ በአኹኑ ጊዜ፡ በዓለም ላይ ተበትነው፡ እናንተንና እናንተን በመሰሉ የጊዜ ሰዎች የማሰነችው፡ የኢትዮጵያ Orthodox ቤተ ክርስቲያን ካህናትና ምእመናን፡ እርስ በርሳቸው እየተለያዩና እየተካሰሱ፥ እየተወጋገዙና እየተጣሉ፡ በሚያደርጉት መልክ፡ በአገር ውስጥም ኾነ፥ በባዕዳን የውጭ አህጉር፡ የግል ቤተ ክርስቲያንና ድርጅት እያቋቋምንና እየከፈትን የምንሠራ አይደለንም።

አታውቁምን? "ሀገረ እግዚአብሔር" በኾነችው፡ በአገር ውስጥም ኾነ በዓለም አቀፏ ኢትዮጵያ ያሉት አብያተ ክርስቲያናት ኹሉ፡ የማን ኾኑና ነው፡ እኛ፡ ሌላ፡ የግል ቤተ ክርስቲያን የምንሠራው!? ኹሉስ፡ የእኛው አይደሉምን? በአኹኑ ጊዜ፡ ለእኛ፡ በማናቸውም ቦታ፡ የገጠር ሰበካ፥ የከተማ ደብርና የገዳም ማኅበራዊ ቤተ ክርስቲያን አያስፈልጉንም፤ ያሉት ይበቁናል።

በኢትዮጵያ ያለችው፡ የግብፅ Orthodox ቤተ ክርስቲያናችሁ ቀኖና፡ ምንጊዜም፡ በመኖሪያ ቤታችሁ፡ የቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ጸሎት እንዳይፈጸም ይከለክል ይኾናል። በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ሥርዓት ግን፡ እንዲህ አይደለም። በዘመናችን ደርሶ እንደሚታየው፡ እንደዛሬው ጊዜ ኹሉ፡ በእውነተኞች አማኞች ላይ፡ የሃይማኖት ስደትና መከራ፥ እሥራትና ዓፀባ፡ ማለትም፡ የካህናትና የአምልኮ ቦታ የማጣት ችግር ሲደርስ፡ "በእውነትና በመንፈስ መመለክን የሚወድደውና የሚፈልገው" ፈጣሪያችን፡ ይህን በሚመለከት፡ መልካም መመሪያን ስለሰጠን፡ ለእኛ፡ ለቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያ ልጆች፡ በዚያ መለኮታዊ መመሪያ መሠረት፡ የአምልኮ ምግባራችንንና የጸሎት ሥርዓታችንን፡ በየመኖሪያ ቤታችን፥ ወይም፡ በጥምቀት በዓላችን ጊዜ እንደሚደረገው፡ በድንኳን ውስጥ፡ በማቅረብ እንዳንፈጽም የሚከለክለን ገደብ የለም።

መሪያችንና መምህራችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ የመጀመሪያውን የአዲስ ኪዳን ሥርዓተ ቅዳሴ ፈጽሞ፡ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን፡ ለቅዱሳን ሓዋርያቱ ያቀበላቸው፡ "እገሌ" ተብሎ፡ ስሙ ባልታወቀ፡ በአንድ ግለሰብ መኖሪያ ቤት ውስጥ እንደነበረ፡ አራቱም፡ የምሥራቹ ተናጋሪዎች፡ በየመጽሓፋቸው መዝግበውት፡ ሲነበብ ይኖራል።

ግድ አስፈላጊ ኾኖ ስለተገኘ፡ ከሰባት ዓመታት በላይ፡ በቆየሁበት የደርግ እሥር ቤት ውስጥም፡ የቅዱስ ቊርባኑን ሥርዓተ ቅዳሴ፡ ከቤተ ክህነቱ እጨጌ ጋር የፈጸምነው፡ መለኮታዊውን መመሪያ ከሚከተለው፡ ከዚሁ፡ ከኢትዮጵያዊው ሥርዓት የተነሣ እንደነበረ ሊታወቅ ያስፈልጋል።

ለመኾኑ፡ አለቃ አያሌው ታምሩ፡ ቤተ ክህነትንና ምእመናንን አውግዘው፥ ራሳቸውም፡ በቤተ ክህነት ተወግዘው ሳሉ፡ እርሳቸውና ተከታዮቻቸው፡ በየመኖሪያ ቤታቸው ውስጥ እንዲወስኑ በተገደዱ ጊዜ፡ ኹሉም፡ ሥጋ ወደሙ ይቀበሉ የነበረው የት ነበር? ወይስ፡ የOrthodoxሶቹ ቀኖና ስለሚከለክል፥ ወይም፡ "ይህን የመሰለው ሥርዓት፡ የProtestantቶቹ ስለኾነ፡ ሊደረግ አይገባም!" በሚል ምክንያት፡ ሳይቀበሉ ኖሩ?

ይህን መለኮታዊ ምሥጢር በሚመለከት፡ እናንተ ባጥላላችኋቸው መጻሕፍቴና በዚህ ጎዋ ሰሌዳችን ላይ የሚበቃ ማብራሪያ የተሰጠ ቢኾንም፡ ያን፡ የእግዚአብሔርን መልእክት፡ በብሩህ ልቦናና በቅን ኅሊና የመቀበሉ፡ መንፈሳዊ አቋምና ዓቅም የሌላችሁ በመኾናችሁ፡ ሊገባችሁና ልትረዱት ስላልቻላችሁ፡ ለሌሎች አስተዋይ አድማጮችና ተመልካቾች ይበጅ ዘንድ፡ እዚህ ላይ፡ አጭር መግለጫን ላቀርብበት እወድዳለሁ፤ ይህም፡ እንዲህ በሚል ዐረፍተ ነገር ሊጠቃለል ይችላል፡-

ፍጥረተ ዓለሙ በሚገኝበት፥ እኛም አኹን ባለንበት፡ በዚህ፡ በመጨረሻው፡ የኪዳነ መንፈስ ቅዱስ ዘመነ ምሕረት፡ እግዚአብሔር፡ ለፍጥረቱ፡ የቸርነት ሥራውን የሚሠራው፡ በቅድስት ድንግል ማርያም፡ የአምላክ እናትነትና እግዚአብሔር ወልድ በኾነው፡ በልጇ በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት፡ በተገኘው የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ መኾኑ፡ የዛሬ፡ ፳፻፪ (ኹለት ሽህ ኹለት) ዓመት፡ ተገልጦና ታውቆ፥ እውን ኾኖና ተፈጽሞ ታይቷል፤ ተረጋግጧልም።

"እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ መመለክ የሚፈልገው፥ የሚወድደውና ደስ የሚያስሰኘውም አምልኮ፡ በእውነትና በመንፈስ የሚቀርብለትን ነው!" የተባለለት ፈጣሪያችን፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ፥ ከዚያም በፊት፡ በትንቢት፡ ሲነግረን የኖረ፡ አንድ የምሥራች መለኮታዊ የአዋጅ ቃል አለው። ያም ምሥራች የተገኘው፡ "ፈጣሪ፡ ጥንቱኑ፡ በፍጥረት መጀመሪያ አድርጎት የነበረው፥ ኋላም፡ ሰብአዊ ፍጡሩ፡ ባሳየው የክፋት ዝንባሌ፡ ከክፉው መንፈስ ጋር በመተባበር፡ ያን መልካም ኹኔታ ቢያበላሸውም፡ እርሱው እግዚአብሔር፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም፡ በፍጹም ሰውነት በመወለድ፡ ወደዚህ ዓለም መጥቶ፡ ያን ጥፋት፡ በራሱ መሥዋዕትነት በመደምሰሱና ወደቀደመ መልካምነቱ በመመለሱ ነው። (ዮሐ. ፬፥ ፳፫-፳፬።)

"ምሥራች!" የተባለው፡ ይኸው መለኮታዊው የአዋጅ ቃል፡ ምን መሰላችሁ?! ከቅዱሳት መጻሕፍት የተውጣጡት፡ የዚሁ ቃል ጥቅሶች፡ በብዙ ቦታና ምክንያት ተደጋግመው የተጻፉ ስለኾኑ፡ እዚህ ላይ፡ እንደገና ማውጣቱ አግባብ ስላልመሰለኝ፡ እጅግ ሰፊና ጥልቅ የኾነውን፡ ይህን፡ የእግዚአብሔርን ታላቅ ቸርነት፡ እንዲህ በሚል፡ አጭር ቃል ጨምቄ ላቅርብላችሁ፦

"እግዚአብሔር አብ፡ ከኢትዮጵያዊቷ ቅድስት ድንግል ማርያም በተወለደውና 'ኢየሱስ ክርስቶስ' በተባለው ልጁ፡ በእግዚአብሔር ወልድ ቤዛነት ባስገኘው የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ጸጋ፡ ዳግመኛ ለወለዳቸው ልጆቹ፡ እንዲህ አለ፦ ‹እንግዴህ ወዲህ፡ በቅዱሱ ኪዳን፡ እውነተኛውና ዘለዓለማዊው የመኖሪያዬ ጽላትና ታቦት፥ መንበሬና መቅደሴ፥ ቤተ ክርስቲያኔና ቤተ መንግሥቴ፡ እናንተ፡ ቃሌን፡ በሃይማኖት ተቀብላችሁና በምግባር ፈጽማችሁ፥ በእውነተኛው የመንፈስ ቅዱስ አምልኳችሁም፡ ሕይወት አድርጋችሁት የምትኖሩትና የምታገለግሉት ናችሁ!›" የሚለው ነው።

በዚህ አንጻር ደግሞ፡ ይህን መለኮታዊ የምሥራች መመሪያና ሥርዓት የሚቃረን፥ በባዕዳኑም ተፅዕኖ የተጠናከረ፥ እናንተና እናንተን የመሰሉ ወገኖች፡ አምናችሁ የተቀበላችሁትና ተከትላችሁ የምትኖሩበት፡ ሰብአዊ መመሪያና ሥርዓት አለ። ይህም፡ እንዲህ የሚል ነው፦

"አንድ ባለሙያ ጠቢብ፡ ጠራቢም ኾነ፥ ወይም፡ ቀራጭ፡ ከተመረጠ እንጨት፥ ወይም፡ ከዕብነ በረድ ፈልፍሎ፡ ባወጣው፡ ባለ፬ ማዕዘን ትንሽ ሰሌዳ ላይ፡ ዓሠርቱ ቃላትን እንደያዘችው፡ እንደጽላተ ሙሴ ሳይኾን፡ የክርስትና ምሥሎችንና ምልክቶችን፥ ስሞችንም ቀርፆበት፡ በቤቱ ያበጀውንና በዋጋ የሚሸጠውን የእጅ ሥራ፡ (እኛ፡ 'ሊቀ ካህናት' የምንለው፥ እናንተም፡ በባዕዳኑ ቋንቋ፡ 'ጳጳስ'፥ ወይም፡ 'ኤጲስ ቆጶስ' የምትሉት) የቤተ ክህነት ተጠሪ፡ ባርኮ የሚሰጠው፥ ወይም፡ ማንኛውም ካህን፥ ወይም፡ ምእመን፡ ወንድ ኾነ ሴት፡ ከየትም ከየት ያገኘው፥ ብቻ፡ 'ነው!' ብሎ የሚያመጣው፡ ጽላት (ጽሌ፥ ወይም፡ እርሱን በሚይዘው ሣጥን፡ በግእዝ፡ 'ታቦት' የሚባለው) ከሌለ፥ ይህም ባለጽላት ታቦት፡ 'ቤተ ክርስቲያን' ተብሎ በተሰየመ፡ በተለየ ሕንፃ ውስጥ እንዲቀመጥ ካልተደረገ በስተቀር፡ ምንም ዓይነት ችግር (የዘመናችንን የመሰለውም ጭምር) ቢደርስም እንኳ፡ አምልኮተ እግዚአብሔር፡ ማለትም፡ ቅዱስ ቊርባን የሚዘጋጅበት ሥርዓተ ቅዳሴ፥ ሌላውም ጸሎትና የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ሊፈጸም አይቻልም!" የሚለው ነው።

ታዲያ! እኛ፡ እውነተኞቹ፡ የቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያ ልጆች፡ የትኛውን ሰምተን፡ በሃይማኖት እንቀበል!? እስኪ፡ እናንተው ፍረዱ! ራሱ፡ ሰው ኾኖ ወደዚህ ዓለም መጥቶ፡ በገዛ አንደበቱ፡ እንዲያ ብሎ የነገረንን፥ ዛሬም፡ በቅዱስ መንፈሱ፡ ለእያንዳንዳችን እያረጋገጠ የሚነግረንን፡ የእግዚአብሔርን ቃል እንስማ!? እንቀበል!? ወይስ፡ ያን የእግዚአብሔሩን ቃል ሽረን፡ ይህን፡ የሰዎችን ንግግር እንስማ!? እንቀበልም!?

እኛ፡ "የእግዚአብሔር ቃል" የምንለው ደግሞ፡ በእኛው ዘንድ ተጠብቆ ቆይቶ፡ የኋላ ኋላ፥ በአኹኑ ጊዜም፡ ዓለም በተቀበለው፥ እኛ፡ አብዝተን፡ "ቅዱሳት መጻሕፍት" በምንላቸው፥ ሌላው ግን፡ "መጽሐፍ ቅዱስ" በሚለው፡ በምሥራቹ መዝገብ ውስጥ ተጽፎ ያለውን ነው። እኛ፡ "የእግዚአብሔር" ብለን የምንጠቅሰው "ቃል"፡ ከሌላ ሳይኾን፡ ከእነዚሁ ቅዱሳት መጻሕፍት ብቻ ስለኾነ፡ ያንን ጥቅሳችንንና በዚያ፡ በጠቀስነው የእግዚአብሔር ቃል መሠረት ያደረግነውን ኹሉ፡ "ይኼማ፡ Protestantነት ነው! ነገር ግን፡ ይኼ ቀርቶ፡ ልትጠቅሱ የሚገባችሁ፡ ሰዎች ከጻፏቸውና ከደነገጓቸው፡ 'የሊቃውንትና የሥርዓት (የቀኖና) መጻሕፍት ብቻ ነው፤ ልታደርጉና ልትኖሩም የሚገባችሁ፡ እነዚህኑ ብቻ መርህ በማድረግ ነው!" የምትሉ ከኾነ፡ ክርስቲያንነቱስ፥ ኢትዮጵያዊነቱስ፡ እንግዴህ፡ በእናንተ ዘንድ፡ ወዴት አለ? የለም ማለት ነው።

እኛስ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት፡ እውነተኞች ተከታዮችና ታማኞች አገልጋዮች ኾነው እንደተገኙት፡ እንደሐዋርያት፡ ሰምተን የምናምነውና የምንቀበለው፥ የምንከተለውና የምንፈጽመውም፥ ሕይወት አድርገን የምንኖረውና የምናገለግለውም፡ የእግዚአብሔርን ቃል መኾኑን፡ እናንተም፥ እናንተን የመሰለውም ኹሉ እወቁት! እነርሱም፡ "እግዚአብሔርን ከመስማት ይልቅ፡ እናንተን እንሰማ ዘንድ፡ በእግዚአብሔር ፊት የሚገባ እንደኾነ ቊረጡ! እኛስ፡ ያየነውንና የሰማነውን ከመናገር፡ ዝም ማለት አንችልም!" ብለው፡ ለተቃዋሚዎቻቸው፡ ለአይሁድ የቤተ ክህነት ሊቃውንት፡ መልስ የሰጡት፡ ቅዱሳን ሐዋርያት ናቸው። (የሐዋ. ፬፥ ፲፰-፳፩።)

በዚህ ረገድ፡ በእናንተና እናንተን በመሰሉት በኩል፡ በአኹኑ ጊዜ፡ በእኛ ላይ እየተፈጸመ ያለው ጥቃትና ግፍ፡ ምንን እንደሚመስል፥ እናንተና እኛም፡ እነማንን እንደምንመስል፡ ከኢትዮጵያዊቷ ድንግል፡ ከቅድስት ማርያም በተወለደው በኢየሱስ ክርስቶስ የትስብእት ደም ለለመለመው፡ ለቅዱሱ ኪዳን፡ ቀዳሚው ተጋዳይና ምስክር ኾኖ በተሠዋው፡ በቅዱስ እስጢፋኖስ አንደበት፡ በመጨረሻ የተነገረው፡ እንዲህ የሚለው፡ የእግዚአብሔር ቃል፡ በትክክል ያመለክተናል፦

"ዳዊት፡ በእግዚአብሔር ፊት፡ ባለሟልነትን አግኝቶ፡ ለያዕቆብ አምላክ፡ማደሪያን ያገኝ ዘንድ ለመነ። ሰሎሞንም፡ ቤትን ሠራለት። ነገር ግን፡ ልዑል፡ የሰው እጅ በሠራው ቤት የሚኖር አይደለም።

"ነቢይ፡ እንዲህ ብሏልና፦ 'እግዚአብሔር፡ እንዲህ ይላል፦ ‹ሰማይ፡ ዙፋኔ ነው፤ ምድርም፡ የእግሬ መረገጫ ናት፤ ለእኔ፡ ምን ዓይነት ቤትን ትሠሩልኛላችሁ? የማርፍበት ቦታስ፡ ምን ዓይነት ቦታ ነው? ይህን ኹሉ፡ እጆቼ የሠሩት አይደለምን?›

"እናንተ አንገተ ደንዳኖች! ልባችሁ የተደፈነ! ጆሮዋችሁም የደነቈረ! እንደአባቶቻችሁ፡ መንፈስ ቅዱስን፡ ዘወትር ትቃወማላችሁ። አባቶቻችሁ፡ ከነቢያት፡ ያላሳደዱት ማን አለ? ዛሬም፡ እናንተ አሳልፋችሁ የሰጣችሁትንና የገደላችሁትን፡ የጻድቁን መምጣት አስቀድመው የተናገሩትን፡ ገደላችኋቸው። በመላእክትም ሥርዓት፡ ኦሪትን ተቀብላችሁ፡ አልጠበቃችሁትም።" (የሐዋ. ፯፥ ፵፮-፶፫።)

ለነገሩማ፡ ቀደም ብሎና በየአግባቡ ቦታ እንደተገለጠው፡ በዘመናችን በደረሰው ችግር ምክንያት፡ እኛ፡ እየቤታችንን ቤተ ክርስቲያን አድርገን፡ አምልኮተ እግዚአብሔርን፡ በየቤታችን እንድንፈጽም ብንገደድም፡ የዛሬዋ ቤተ ክህነት ካህናትና ምእመናን፡ በያለበት፥ እርስ በርሳቸው በመወጋገዝ፡ በተለይም፡ በውጭዎቹ አህጉራት፡ ከዛሬዪቷ የኢትዮጵያ ቤተ ክህነት ሥርዓት ውጪ፡ የጽላቱን ታቦት፡ ከሕጋዊቷ የቤተ ክህነት ተጠሪዎች ሳያገኙ፡ እንዲያው፡ ከየትም የቃረሙትን የጽላት ታቦት እየያዙ፥ ያልኾነውንም፡ "ነው!" እያሉ በማቅረብ፡ ባስፈለጋቸው ቦታና ጊዜ፡ እንደፈለጋቸው፡ በሥርዓተ አልበኝነት፡ ክህነታዊዉን አገልግሎት እያካኼዱ አይደለምን?

እኛስ፡ እንዲህ አላደረግንም፤ እውነተኛውን፡ ኢትዮጵያዊ፡ የቤተ ክህነት ሥርዓታችንን በመጠበቅና በማክበር ረገድ ያለብንን ኃላፊነት በማጽናት፡ እኛ ያልነውና እያደረግንም ያለነው፡ “ይህ የዘመናችን ስደትና መከራ፥ ፈተናና ችግር እስኪያልፍ ድረስ፡ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስና በቅድስት እናቱ ድንግል ማርያም ኪዳነ ምሕረትነት ባገኘነው፡ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ እየተጠቀምን፡ ‘በእውነትና በመንፈስ እንድንፈጽመው፡ በፈጣሪያችን የተሰጠንን መመሪያ ተከትለን፡ አምልኮተ እግዚአብሔራችንን፡ በየቤታችን እያደረግን እንቆይ!” ነው።

በዛሬው የኢትዮጵያ ትውልድ ላይ እየደረሰ ያለውን፡ ይህን፡ የዘመናችንን ስደትና መከራ፥ ፈተናና ችግር፡ ያመጣው ጠንቀኛ ምክንያት፡ ምን እንደኾነ፡ ለማንም፥ ለኹሉም፡ ግልጽ ስለኾነ፡ እናንተም፥ ሌላውም ያወቃችሁት ይመስለኛል፤ ካላወቃችሁት፥ ወይም፡ ለማወቅ ባትፈልጉም፡ እገልጥላችሁ ዘንድ፡ ግድ ይኾንብኛል። ያ ምክንያት፡ መለኮታዊና የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ሃይማኖታችንን የነካ በመኾኑ፡ ታላቅ ቢኾንም፡ ባጭር ቃል ሲገለጽ፡ እንዲህ በሚል፡ አንድ ዐረፍተ ነገር ይጠቃለላል፡-

የእግዚአብሔር መንግሥት አካል የነበሩት፡ የዛሬዎቹ፡ የኢትዮጵያ ቤተ ሕዝብ፥ ቤተ ክህነትና ቤተ ምልክና፡ ኹሉም፡ በቅዱሱ ኪዳን ላይ፡ ታላቁን፡ የክህደት፥ የዓመፅና የአምልኮ አመንዝራነት ኃጢአትን፡ በድፍረትና በገሃድ ስለፈጸሙ፥ ከዚህ የተነሣም፡ ኹሉም፡ በእውነተኛ ንስሓ እስከተመለሱ ድረስ፡ በመለኮት ውግዘት ታግደውና ተለይተው፡ በጽኑ ፍዳና ሥቃይ ላይ ስለሚገኙ ነው።

የቅዱሱ ኪዳን አካል ከኾኑት፡ ከሰባቱ ቅዱሳት ኪዳናት መካከል፡ አንዱና አምስተኛው የኾነው፡ የጽላትና የታቦት ሥርዓታችንንማ፡ ለመጠበቅና ለማስጠበቅ፡ ባለቤቶቹና ባለአደራዎቹ እኛ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልጋዮች የኾንነው፡ የቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያ ልጆች አይደለንምን? አዎን! በእርግጥም እኛ ነን። አምልኳችን፡ “በእውነትና በመንፈስ” እንዲኾን፡ ከፈጣሪያችን የተሰጠንን ጥብቅ መመሪያ፡ በጥንቃቄና በታማኝነት በመፈጸም፡ የባለጽላት ታቦታችንን ቅርስና ሥርዓት የምንጠብቀው፡ ስለሦስት መሠረታውያንና ቀዋምያን ምክንያቶች መኾኑን እንዳንዘነጋ፡ ያን፡ ዓቢይ ቍም ነገር፡ እዚህ ላይ ማውሳቱ አግባብ ይኾንብኛል። እነዚህ ምክንያቶች፡ ተጠቃልለው የሚገኙበት ሓተታ፡ ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

በግእዝ፡ “ጽሌ”፡ በነጠላው፡ “ሰሌዳ” ማለት ሲኾን፡ በኹለትና ከዚያ በላይ ሲበዛ፡ “ጽላት” ይባላል፤ “ታቦት”፡ ጽላቱ የሚቀመጥበት፡ “ሣጥን” ማለት ነው:: ሙሴ፡ በደብረ ሲና፡ ከእግዚአብሔር የተቀበላቸውን፡ ኹለቱን ጽላት የያዘው፡ የቃል ኪዳኑ ታቦት፡ አንድ ብቻ ነበር፤ ይህም ታቦት፡ በብሉዩ ኪዳን ዘመነ ኦሪት፡ ለእግዚአብሔር አምልኮ፡ የተቀደሰ ማዕከል ኾኖ ሲያገለግል ቆየ::

በእነዚያ ጽላት ላይ በተጻፉት ዐሥሩ ቃላት የተገለጸው፡ ያ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ተብሎ፡ ከአማናዊቷ ታቦት፡ ከድንግል ማርያም፡ በሰውነት ከተወለደ በኋላ ግን፡ አንድ ጽሌ ብቻ የያዘ፡ ሌላ ተመሳሳይ ታቦት፡ በክርስትና እምነት መሠረት ተዘጋጀ፡፡

የአዲስ ኪዳኑን ጽሌ (ጽላት) የያዘው ይህ ታቦት፡ በየቤተ ክርስቲያኑ መቅደስ ውስጥ ባለው መንበር መካከል ተቀምጦ፡ በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ፡ ወደመለኮት ሥጋና ደምነት ይለወጥ ዘንድ፡ ኅብስቱ፡ በጻሕል፥ ወይኑ፡ በጽዋ ኾኖ ለሚቀርበው፡ ለአዲስ ኪዳኑ ቅዱስ ቍርባን በመሠዊያነት ያገለግላል፡፡

ኹለቱን፡ የብሉዩን ኪዳን ጽላት ተክቶ፡ በአዲሱ ታቦት (ሣጥን) ውስጥ የተቀመጠው፡ የአዲስ ኪዳኑ ጽሌ (ጽላት)፡ ከኹለት ሥንዝር ያልበለጠ ስፋት ያለው፡ ጠፍጣፋና አራት ማዕዘን ኾኖ፡ ከማይነቅዝ እንጨት ተፈልፍሎ፡ ወይም፡ ከዕብነ በረድ ተጠርቦ የወጣ፡ ነጠላ ሰሌዳ ሲኾን፡ በላዩ ተቀርጾ የሚታየው ጽሑፍ፡ <u>እንደቀደሙት ጽላት፡ ዐሥሩን ትእዛዛት የያዘው፡ የእግዚአብሔር ቃል ሳይኾን፡</u> ያ ቃል፡ በድንግል ማርያም ማሕፀን፡ ሰው መኾኑን ለማሳየት፡ ከላይ፡ የቅድስት ሥላሴ ስም እና/ወይም ሥዕል፥ በመኻል፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ሥነ ስቅለት ኾኖ፡ በቀኝ፡ የድንግል ማርያም፥ በግራ፡ የወንጌላዊው ዮሐንስ ሥዕሎች፥ ዙርያውንም፡ የእግዚአብሔር፡ የአምላክነቱ ስሞች ተጽፈውና ተሥለው የሚታዩበት ነው፡፡ ያ፡ ታቦት የሚገኝበት ቤተ መቅደስ፡ በጌታ ወይም በእመቤታችን ስም እንደኾነ፡ ስማቸው፥ አለዚያ፡ መታሰቢያነቱ፡ ለነቢይ፥ ለሓዋርያ፥ ለጻድቅ፥ ለሰማዕት ወይም ለመልአክ ከኾነ፡ የዚያ ቅዱስ ስም፡ "ዝ ጽላት፡ ዘቅዱስ እከሌ" ተብሎ፡ ዘመኑ ጭምር፡ ከጀርባው ይቀረጽበታል፡፡

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ፡ በዚያ፡ በመጀመሪያው የአዲስ ኪዳኑ ጽሌ ዓይነት፡ ነገር ግን አራት ማዕዘን ኾኖ፡ በዕብነ በረድ፡ ወይም በማይነቅዝ የእንጨት ዓይነት፡ በተለያየ ቅጽና ቅርጽ እየተዘጋጀ፥ እየተራባና በተገቢው ሥርዓተ ጸሎት እየተባረከ፥ ታቦት በተባለውም፡ የእንጨት ሣጥን ውስጥ በክብር እንዲቀመጥ እየተደረገ፡ ሲሠራበት ኖርዋል፡፡ ይህን የመሰለውን ጽላትና ታቦት ነው፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከድንግል ማርያም ተወልዶ፡ ለሰው ልጆች ባስገኘው ዘለዓለማዊ ትድግናው አማካይነት፡ የሚወርዱትን የመንፈስ ቅዱስ ጸጋዎች፡ ወደምእመናን ለማስተላለፍ የሚያስችሉት ምሥጢራትና ሥርዓታት በሚፈጸሙበት፡ በእያንዳንዱ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መቅደስ ባለው መንበር ውስጥ እያኖሩ የሚቀድሱበት፡፡ ይህ ሥርዓት፡ የእኛ የኢትዮጵያውያን ብቸኛ ቅርሳችን መኾኑን፡ ሃይማኖታዊው የዓለሙ ወገን ኹሉ ያውቀዋል።

በብሉዩ ኪዳን እንደነበረው ኹሉ፡ የአዲስ ኪዳኑም ጽሌ፡ ወይም በልማድ እንደሚባለው፡ ጽላቱ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ፥ ታቦቱ ደግሞ፡ የቅድስት እናቱ፡ የድንግል ማርያም ምሳሌ የመኾኑ ምሥጢር፡ ሳይቃወስ ቀጥሏል፡፡

እንዲህ ኾኖ፡ የአዲስ ኪዳኑን እምነት በመከተል ያልተቋረጠው፡ ይህ፡ የጽላትና የታቦት ዝግጅትና ሥርዓት፡ እስከዛሬ፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ሥር በተቋቋሙት አብያተ ክርስቲያን ዘንድ ሲካኼድ የኖረው፡ ለምን እንደኾነ፡ ከዚህ የሚከተሉት ሦስት ምክንያቶች በሚበቃ ያስረዳሉ፦

፩. ማናቸውም የቤተ ሕዝቡ ሰበካ ጉባኤ፡ ማለትም፡ ገጠር፥ ደብር ወይም ገዳም፡ በማኅበር ተቋቁሞና በቤተ ክርስቲያንነት ተደራጅቶ መገልገል ሲፈልግ፡ ጽላቱ፡ ከሌላ ከማንም ምእመን፥ ካህን ወይም ሊቀ ካህናት (ጳጳስ) ሳይኾን፡ ሕጋዊው ሥልጣን ካላት፡ ከኢትዮጵያ ቤተ ክህነት፡ በዘመኑ እጨጌ አማካይነት ብቻ፡ ለዚያ ሃይማኖታዊ አቋምና መንፈሳዊ ድርጅት፡ የመሠረቱ ድንጋይ፥ ሕጋዊው ፈቃድና መለኮታዊው ማኅተም ኾኖ ይሰጣል።

፪. ካህናቱ፡ በእውነተኛው ሃይማኖታዊ አምልኮ ኾነው፡ በቅዳሴ ጊዜ በሚያከናውኑት ሥርዓት ጸሎት፡ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋና ኃይል በዚያ ተገኝቶ፡ ወደኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም ይለውጠው ዘንድ፡ ኅብስተ አኰቴቱን፡ በጻሕል፥ ወይኑ በረከቱን፡ በጽዋ አድርገው፡ ለሚያቀርቡት ቅዱስ ቊርባን፡ በመንበሩ መካከል ጽላቱን ይዞ የሚገኘው ታቦት፡ መሠዊያ ኾኖ፡ ተልእኳቸው ይፈጸምበታል።

፫. በኪዳነ ልቦና፡ ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ እስከኢትዮጵያዊው መልከ ጼዴቅ፥ ከዚያም በኢትዮጵያዊው ካህን ዮቶር በኩል፡ እስከ ንግሥተ ሳባ ዘመን፡ ተያይዞ የደረሰው፡ የኅብስተ አኰቴትና የጽዋዐ በረከት አምልኮተ እግዚአብሔር፡ በኪዳነ ኦሪቱ ተጠናክሮ ከኖረ በኋላ፡ "የአዲስ ኪዳኑ አቤሜሌክ" በተባለው፡ በኢትዮጵያዊው ጃንደረባ፡ የክርስትና ጥምቀት ጸድቆ እንዲቀጥል በተደረገ ጊዜ፡ የጽላቱና የታቦቱ ሥርዓት፡ ሽግግሩን እንዴት እንዳሠመረው በማዘከር፡ ይህን ቅርስ ጠብቃ የኖረች፡ ኢትዮጵያ ብቻ መኾኗን ለማረጋገጥ፡ የአዲስ ኪዳኑን ጽላት የያዘው፡ ይኸው ታቦት፡ የዚህ ትውፊት፡ አማናዊ ድልድይና ቋሚ ማስረጃ ኾኖ፡ ለትውልደ ትውልድ ይተላለፍበታል።

ይህን፡ የብሉይ ኪዳኑን የአምልኮተ እግዚአብሔር ሥርዓት፡ እንዲህ፡ በአዲስ ኪዳኑ ምሥጢራት አድሶና አስተካክሎ በመተካት፡ የቀድሞው ቅርስ ተጠብቆና ሕያው ኾኖ እንዲቀጥል የማድረጉ ችሎታና ብቅዓት የተገኘው፡ በኢትዮጵያውያን ዘንድ ብቻ መኾኑ ይታወቃል። ይኹን እንጂ፡ ኢትዮጵያውያን፡ አምላካቸውን፡ እግዚአብሔርን የሚያመልኩበት፡ ይኸው አዲሱ የክርስትና ሥርዓት፡ ጥንትም ኾነ ኋላ፥ ምንጊዜም፦ "**እግዚአብሔር፡ መንፈስ ነው፤ የሚያመልኩትም፡ በመንፈስና በእውነት ሊያመልኩት ያስፈልጋቸዋል።**" በሚለው፡ በአምላካችን በኢየሱስ ክርስቶስ ቃል ላይ የተመሠረተና ያን የተከተለ መኾኑ ሊዘነጋ አይገባም።

ይህን የመሰለው፡ በቅዱሱ ኪዳን ላይ የተመሠረተው፡ የአምልኮተ እግዚአብሔር ባህል፡ ባንድ ወገን፡ የቃል ኪዳኑ ታቦት፡ ወደኢትዮጵያ መጥቶ፡ እስከመጨረሻው፡ በዚችው ምድር ለመቆየቱ፡ ተጨባጭ ማስረጃና ሕያው ምስክር ሲኾን፥ በሌላው ወገን ደግሞ፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን፡ በመላዋ ምድር ላይ በሚገኙት፡ በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ መካከል፡ ከኹሉ የተለየች ብርቅና ከኹሉ የቀደመች አረጋዊት ለመኾኗ፡ ዓቢዩ መለያ ምልክት ኾኖ ይኖራል። ("ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ!" በን.እ. ኤርምያስ ከበደ ወ/ኢየሱስ፤ ፲፱፻፺፫ ዓ. ም.፤ ገጽ ፸፯-፩፻፫። ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት- ፪ኛ መጽሐፍ" ፲፱፻፺፯ ዓ. ም.፤ በንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ-ኢየሱስ፤ ገጽ ፪፻፴፩-፪፻፴፫።)

በመሠረቱ፡ እናንተና እናንተን የመሰሉት ኹሉ፡ "ኢትዮጵያዊነት"፥ እርሱም፡ "እውነተኛው"፥ ያም፡ "የእግዚአብሔሩ"፡ ምን እንደኾነ፡ በትክክል ያወቃችሁትና የተረዳችሁት አልመሰለኝም። ምናልባት፡ የእናንተ "ኢትዮጵያዊነት"፡ እኛ ከምናውቀውና ከምናምንበት፥ ከምንኖረውና ከምንጋደልለት "ኢትዮጵያዊነት" የተለየ ከኾነ፡ ያንንም ኾነ፥ ሌላ ካለ፡ ኹሉንም፡ እኛ አናውቃቸውም፤ እውቅናም አንሰጣቸውም።

"ኢትዮጵያዊነት"፡ ቅዱሱ ኪዳን ነው፤ ቅዱሱ ኪዳንም፡ "ኢትዮጵያዊነት" ነው። ስለዚህ፡ "ኢትዮጵያዊነት" የኾነው ቅዱሱ ኪዳን፡ ፈጣሬ ፍጥረታት እግዚአብሔር፡ በአዳምና ሔዋን ጀምሮት፥ በኖኅ፥ በመልከ ጼዴቅ፥ በአብርሃም፥ በሙሴና በዳዊት አማካይነትም ቀጥሎት፥ በኢየሱስ ክርስቶስና በድንግል ማርያምም የፈጸመውን፥ ለሰው ልጆች የገባቸውን ሰባቱን ቅዱሳት ኪዳናት አጠቃልሎ የያዘው፡ ታላቁ፡ የእግዚአብሔር የሕይወት መዝገብ ነው።

ከዚህ የተነሣ፡ "ኢትዮጵያዊነት"፡ ጠባብና ውሱን ከኾኑት፡ "በክርስትና እምነት ውስጥ ነን!" ከሚሉት፡ ከግሪክና ከግብፅ Orthodoxነት፥ ከሮማ Catholicነትና ከምዕራባውያን Protestantነት፥ ከቀሩትም የተለያዩ የዓለም ሃይማኖቶች ጋር፡ ራሱን አያነጻጽርም፤ አያወዳድርም፤ አያመዛዝንም፤ አያስተካክልም፤ አያልቅም፤ አያሳንስም። ነገር ግን፡ ይኸው ኢትዮጵያዊነት፡ የቅዱሱ ኪዳን አካልና ባሕርይ ተጠቃልለው የተመደቡባቸውን፡ ሦስቱን ታላላቅ ክፍላተ ዘመናት፡ ማለትም፡ ዘመነ ኪዳነ ልቦናን፥ ዘመነ ኪዳነ ኦሪትንና ዘመነ ኪዳነ መንፈስ ቅዱስን፥ ወይም፡ ዘመነ ኪዳነ ምሕረትን፥ እነዚህም ኹሉ፡ ተዘርዝረው የተገለጹባቸውን ሰባቱን ኪዳናት የያዘ ነው።

ስለዚህ፡ ይኸው ኢትዮጵያዊነት፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ሊቀ ካህናትነትና ንጉሠ ነገሥትነት፥ በድንግል ማርያምም፡ መቅደስ አገርነትና እናት ንግሥትነት በምትመርራው፡ በእግዚአብሔር መንግሥት አማካይነት፡ በፍጥረተ ዓለሙ ላይ፡ በሉዓላዊነት ሰፍኖ ይኖራል።

መመሪያውም፡ ቅዱሱ ኪዳን ባስገኛቸው፡ በኢትዮጵያውያንና በኢትዮጵያውያት ልቦና ላይ የተጻፉትና በአንደበታቸው የተነገሩት፡ የእግዚአብሔር ቃላት ኾነው፡ እኒሁ የኢትዮጵያ ልጆች ያገለግሉታል።

በዚህ ምክንያት፡ ለዚሁ፡ ለ"ቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት"፡ መሠረቱና ምሰሶው፣ ጒልላቱም፡ የእግዚአብሔር ቃል ብቻ ስለኾነ፡ እናንተ፡ Orthodox እና/ወይም፡ Protestant እያላችሁ፡ ደጋግማችሁ ያነሣሣችኋቸው መጠሪያ ስሞች፡ በቃልነታቸውም ኾነ በስምነታቸው፥ በሃይማኖትነታቸውም ኾነ በድርጅትነታቸው፡ ለዚሁ፡ የእኛ ማንነት መታወቂያ ለኾነው፡ ለ"ቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት"፡ ምኑም አለመኾናቸውን ልታውቁት ይገባል።

በዚህ ዓለም፡ በሥጋ የሚኖር የፍጥረት ወገን ኹሉ፡ ምድራዊ ህልውናውን በመልካም አሳልፎ፡ ለመልካሙ ዘለዓለማዊ ሕይወት የሚበቃው፥ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት እንጂ፡ በOrthodoxነት፥ ወይም፡ በProtestantነት ስላልኾነ፥ በመጨረሻውም የመለኮት ፍርድ ላይ የሚቀርበው ጥያቄ፡ አንተ/አንቺ፡ "Orthodox፥ Protestant ነህወይ? ነሽወይ?" የሚል ሳይኾን፡ በዚሁ፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታችን "ምን ሃይማኖታዊ የምግባር ፍሬን አስገኛችሁ?" የሚል በመኾኑ፡ በእነዚህ የባዕዳን ስሞችና እምነቶች ነገር፡ ይህን ያህል ተጨንቃችሁ፡ ውትወታ ልታበዙበትና ልታጠናክሩበት የሚያስፈልግ አይመስለኝም።

ይህም እውነታ፡ እንዲህ በሚለው፡ በራሱ፡ በመምህራችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቃል፡ ተገልጦ ተነግሮናል፦ "በሰማያት ያለውን፡ የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ፡ 'ጌታ ሆይ! ጌታ ሆይ! የሚለኝ ኹሉ፡ ወደእግዚአብሔር መንግሥት የሚገባ አይደለም። በዚያን ቀን፡ ብዙዎች፡ 'አቤቱ! አቤቱ! በስምህ፡ ትንቢት አልተናገርንምን? በስምህስ፡ አጋንንትን አላወጣንምን? በስምህስ፡ብዙ ተአምራትን አላደረግንምን?' ይሉኛል። የዚያን ጊዜም፡ 'ከቶ አላውቃችሁም! እናንተ፡ ዐመፅን የምታደርጉ! ከእኔ ራቁ!' እላቸዋለሁ።" (ማቴ. ፯፥ ፳፩-፳፫።)

እዚህ ላይ ግን፡ ከዚህ ጋር የተዛመደ አንድ ቁም ነገርን ማውሳቱ፡ አስፈላጊ ይመስለኛል፤ ይኸውም፡ Protestantነትን በሚመለከት፡ በእኔ ላይ ይህን ያህል ክስና ውቅስ ስታቀርቡብኝ፡ በአለቃ አያሌው ታምሩ በኩል ያለውን፡ እንደምን ዘነጋችሁት? አውቃችሁ ነው? ወይስ ሳታውቁ? እኔ፡ ስላልተማርሁትና ስላልኖርሁበት፥ ስለእርሱም፡ በሚበቃ እንኳ ስላላነበብሁ፡ ስለProtestantነት፡ ይህን ያህል የማውቀው ነገር የለኝም።

በተለይ፡ ሊቃችሁ፡ አለቃ አያሌው ታምሩ ግን፡ ስለኖሩበት፥ ስለእርሱና ከእርሱም፡ በቂ ትምህርትን ስላገኙ፡ እርሳቸው፡ ስለProtestantነት፡ በቂ እውቀት እንዳላቸውና ሊጠየቁበትም እንደሚገባ፡ እርግጥ ነው። ይህን እውነታ፡ እናንተስ ታውቁ የለምን? ታዲያ! እንዴት ከእርሳቸው ለመማርና ለማወቅ አልሞከራችሁም?

አለቃ አያሌው ታምሩ፡ ወደእነርሱ፡ ወደProtestantቶች ተጠግተው፥ ዐብረውም በመኖር፥ በትምህርት ቤታቸውም ገብተው፡ በደቀ መዝሙርነት፡ ከእነርሱ፡ ብዙ ትምህርትን እንደቀሰሙ፡ ድብቅ፥ ወይም፡ ምሥጢር ሳይኾን፡ በአደባባይ የሚታወቅና እርሳቸውም፡ በይፋ የመሰከሩት እውነታ ነው። ምናልባትም፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በመስቀል ላይ ኾኖ፡ ነፍሱን፡ ለጊዜው፡ ከሥጋው ከመለየቱ በፊት፡ "እነኋት እናትህ!" ብሎ፡ እናቱን፡ ለደቀ መዝሙሩ፡ ለዮሓንስ፡ አደራ በሰጠበት ጊዜ፡ እናቱን ግን፡ ለዚሁ ደቀ መዝሙሩ፡ አደራ የሰጠው፡ "ሴትዮ! እነሆ ልጅሽ!" ብሎ ነው በማለት፡ በእመቤታችን ላይ፡ ያን የመሰለውን፡ "ሴትዮ!" የሚለውን ቃል ሰጥተው፡ በድፍረትና በንቀት የተረጐሙት፡ ፀረ-ማርያምነት ዓላማ ካለው፡ ከዚሁ፡ ከProtestantነት የተነሣ ሊኾን ይችላል ብሎ መገመቱ ያስኬዳል።

ደግሞስ፡ ይህንኑ ታላቅ በደል ለመሸፈን ሲሉ፡ በዚያ፡ ወደእርሳቸው ለጻፍሁት ደብዳቤ መነሻ በኾነውና ስለእመቤታችን በጻፉት መጽሓፋቸው ውስጥ፡ ስለዚሁ፡ "ሴትዮ!" ስለሚለው ቃል፡ አንዳችም ማብራሪያን ሳያክሉ፥ ወይም፡ ስለፈጸሙት በደል፡ ምንም ዓይነት የመጸጸትና የንስሓ ፍንጭን ሳይሰጡ ማለፋቸው፡ በዚሁ ከProtestantቶቹ ባገኙት አቋማቸው መጽናታቸውን አያመላክትምን?

፳ኛ. Obviously the letter is written by some one who do not have any decency and respect to out Ethiopian tradition **ላላችሁት፦**

የዚሁ ደብዳቤዬ አጻጻፍ፡ ጨዋነትና አክብሮት ከተመላበት ኢትዮጵያዊው ባህል ውጭ እንደኾነ አድርጋችሁ የሠነዘራችሁት፡ ይህን የመሰለው ነቀፌታ ስላለ፡ ለዚህም ኃይለ ቃላችሁ፡ ተገቢውን ማብራሪያ ሳልሰጥ እንዳላልፍ፡ ኃላፊነቴ ያስገድደኛል። እንዲህ ከኾነ፡ እናንተ፡ "ኢትዮጵያዊ" ስትሉ ያሞካሻችሁት "ባህል"፡ የትኛውን ማለታችሁ እንደኾነ፡ እስኪ ለይታችሁ እንድትገልጡልኝ፡ በቅድሚያ ልጠይቃችሁ?!

እናንተ፡ "ኢትዮጵያዊ ባህል" የምትሉት፡ ይህን፡ አኹን፡ እናንተ፡ "ከእግዚአብሔር ቃልና ሥራ ይልቅ፡ የአለቃ አያሌው ቃልና አድራጎት ይበልጣል! ይከብርማል!" የሚለውን ነውን? ከዚህ የተነሣም፡ "መለኮታዊዉን ቃልና ሥራ የተቃረነው፡ ይኸው ሰብአዊው ቃልና አድራጎት ለምን ተነካ? ለምንስ ተተቸ?" ብሎ በማማረር፡ እናንተን የመሰለው ኹሉ፡ በማናለብኝነት፡ የቁጣ ድምፁን እንዲያስሰማ የሚፈቅደውን ነውን፡ እናንተ፡ "ኢትዮጵያዊ ባህል" የምትሉት? "ያን፡ በመንፈስ ቅዱስ ላይ የተሠነዘረውን፡ የአለቃ አያሌው ታምሩን፡ የድፍረት ኃይለ ቃል ለማረም፡ የእግዚአብሔር መንግሥት የኾነችውን ኢትዮጵያን እንዳገለግላት፡ በይፋ፡ ቃል ኪዳን ከገባሁት፡ ከእኔ፡ ለምን ተሠነዘረ?" ብሎ የሚነቅፈውን፡ ይህን፡ የእናንተን የመሰለ፡ የወቀሳ አጻጻፍ ያፈለቀውን ነውን፡ እናንተ፡ "ኢትዮጵያዊ ባህል" የምትሉት?

ይህማ፡ እውነተኛውና ትክክለኛው “ኢትዮጵያዊ ባህል” አይደለም! እርሱማ፡ እውነተኛውንና ትክክለኛውን “ኢትዮጵያዊ ባህል”፡ አማናዊ ማንነቱን በመበረዝ፡ የዛሬ “፫ሺህ” ዓመትና “በ፲ኛው ምዕት ዓመተ ምሕረት”፡ በረቂቅ መንገድ ሠርጎ የገባው፥ እነሆም፡ ሥር ሰድዶ፡ ኢትዮጵያን፡ ከመልካሙ እግዚአብሔራዊ ሥርዓቷ ጋር አጥፍቶ፡ ራሱን ሊተካ እየሞከረ የቀጠለው፡ “የባዕዳኑ፡ የአይሁድና የግብፃውያኑ ባህል” እንጂ፡ እውነተኛውና ትክክለኛው “ኢትዮጵያዊ ባህል” አይደለም። የባዕዳኑ ባህል ደግሞ፡ በምንም መልኩና ይዘቱ፡ “የኢትዮጵያ ባህል” ሊባል ከቶ አይችልም።

ልብ አድርጋችሁ፡ በማስተዋል የምትሰሙኝ ከኾነ፡ እውነተኛውና ትክክለኛው “ኢትዮጵያዊ ባህል”፡ ማንና ምን እንደኾነ፣ ማለትም፡ ማንነቱንና ምንነቱን ላስታውቃችሁ! እርሱም፡ ኢትዮጵያ፡ ከፍጥረት፡ ማለትም፡ ከአዳምና ሔዋን ጀምራ እስካኹን፥ አኹንና ወደፊትም፥ ለዘለዓለም፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መኾኗን አምነው፥ ይህንም እምነት፡ የቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖታቸውና ምግባራቸው፥ ሥርዓታቸውና ሕይወታቸው አድርገው በኖሩት፥ ዛሬም፡ የመጀመሪያው የመንፈስ ትንሣኤ ዕድምተኞች ኾነው በሚኖሩት ልጆቿ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ዘንድ ተጠብቆና ተከብሮ፥ ጸንቶም የቀጠለው ነው፤ እርሱም፡ እውነተኛውና ትክክለኛው “ኢትዮጵያዊ ባህል” መኾኑ ታውቆ፡ እኒሁ፡ የቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያ ልጆች፡ በመንፈስ ቅዱስ መሪነትና አነቃቂነት፡ ከሰው ይልቅ፡ የእግዚአብሔር የኾነውን ሲያስቀድሙና ሲያስበልጡ፥ ሲወድዱና ሲያገለግሉ፡ የኖሩበት መለኮታዊው ባህል ነው።

ከዚህ የተነሣ፥ ደግሞም፡ እግዚአብሔር ራሱ፥ ሥራውም፡ ብርሃን ስለኾነ፡ እኒሁ የቅዱስ ኪዳኗ፡ የኢትዮጵያ ልጆች፡ ማናቸውንም፡ ሃይማኖታዊ ምግባራቸውን ኹሉ፡ እንደአስፈላጊነቱና እንደተገቢነቱ የሚፈጽሙት፡ በብርሃን እንጂ፡ በጨለማ አይደለም። ለዚህም፡ ከፈጣሪያቸው ከተቀበሉት፡ ከሕያዉ መመሪያቸው መካከል፡ እንዲህ የሚሉት ይገኙባቸዋል፡-

“መልካሙን ሥራችሁን አይተው፡ በሰማያት ያለውን አባታችሁን ያመሰግኑት ዘንድ፡ ብርሃናችሁ በሰው ፊት ይብራ!” ደግሞም፡ “[የእግዚአብሔር] ፍርዱ፡ ይህ ነው፤ ብርሃን፡ ወደዓለም መጥቷልና፤ ሰውም፡ ሥራው፡ ክፉ ስለኾነ፡ ከብርሃን ይልቅ፡ ጨለማን መርጧልና። ሥራው፡ ክፉ የኾነ ኹሉ፡ ብርሃንን ይጠላልና፤ ክፉም ስለኾነ፡ ሥራው እንዳይገለጥበት፡ ወደብርሃን አይወጣም። እውነትን የሚሠራ ግን፡ ሥራው ይገለጥ ዘንድ፡ ወደብርሃን ይመጣል፤ ስለእግዚአብሔር ብሎ ይሠራልና።” (ማቴ. ፭፥ ፲፮። ዮሐ. ፫፥ ፲፱-፳፩።)

ስለዚህ፡ ከእግዚአብሔር ይልቅ፡ ሰው እየተፈራ፥ ከእግዚአብሔር ይሉኝታ ይልቅ፡ የሰው ይሉኝታ የላቀ ክብርና ማዕርግ እየተሰጠው፥ በጨለማና በሓሜት እያሾከሾኩ፡ ደጉን ወገን፡ በተንኮል ፍላጻ፡ ከጀርባው መውጋት እንጂ፡ ፊት ለፊት ተገናኝቶና ተገላልጦ መነጋገር፡ እንደጭራቅ ተፈርቶና እንደእርም ተቆጥሮ፡ ፈጽሞ የተወገደበትን፡ ይህን የመሰለውን፡ እናንተ የምታሞካሹትን ክፉና ጥፉ፡ የባዕዳን ባህል፡ እኛ፡ የቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያ ልጆች፡ እንኳንስ፡ "ኢትዮጵያዊ" ብለን ሰይመን፡ ልንቀበለውና ልንከተለው ይቅርና፡ ልናውቀውና ልናስበውም አንሻም።

በዛሬው የኢትዮጵያ ትውልድ መካከል፡ ለቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖታቸው፡ እውነተኞችና ታማኞች የኾኑ ጀግኖች የኢትዮጵያ ልጆች ካሉ፡ የዲያብሎስ ሠራዊትና መሣሪያዎች የኾኑ ሰዎችና አጋንንት፡ ይህን ትውልድ ሊያማስኑት ከጫኑበት፡ ከማናቸውም ዓይነት፡ ጠንቀኛና ጎጂ ልማድ፡ ራሱን፡ በንስሓ እንዲያጠዳ በማድረግ፡ ይህን ክፉና ጥፉ ልማድ፡ ሊያስወግዱለት ይገባቸዋል። ይህን የተቀደሰና የሚጠበቅ ተልእኮ፡ ከግብ ለማድረስ፡ የእነርሱን መሥዋዕትነትና ሰማዕትነትም እንኳ የሚጠይቅ ኹኔታ ቢፈጠር፡ ያን ለማቅረብና ግዳጃቸውን ለመፈጸም፡ ዝግጁ ኾነው መገኘትም ይኖርባቸዋል።

**፯ኛ.** The last thing I want to mention is your books. They are poison covered with honey. And the honey is stolen from Aleqa Ayalew Tameru's books. But it's no use because you have added poison in it. So, your books are simply crap and serve no purpose other than wasting your own time as well as the readers' time and taking up space in the bookshelf. **ላላችሁት፡-**

መንፈስ ቅዱስ ባደረባቸው ሰዎች ኾነ፡ በቅዱሳት መጻሕፍት አማካይነት፡ እግዚአብሔር፡ ለዓለሙ ኹሉ፡ በልዩ ልዩ ቋንቋዎች እየገለጸ ያስተላለፋቸው፥ ያናገራቸውና ያስጻፋቸው መልእክቶቹ ኹሉ አንድ ዓይነት ናቸው።

ሰው ኾኖ ወደዓለም መጥቶ፡ በአንደበቱ ያስሰማቸውና በምግባር የፈጸማቸው፥ የእርሱ ታማኞች አገልጋዮችም፡ እስከዛሬ ሲያስሰሙና ሲጽፉ የኖሩትና ዛሬ እያስሰሙና እየጻፉ ያሉት፥ ወደፊትም፡ የሚያስሰሙትና የሚጽፉት፡ ያው፡ አንዱን የእግዚአብሔር ቃል፥ አንዲቱን የእግዚአብሔር እውነት ነው። ማናቸውም ንግግርና ጽሑፍ፡ ያ እስከኾነ ድረስ፡ ማለትም፡ ከዚያ፡ ከአንዱ፡ ከእግዚአብሔር ቃል፥ ከአንዲቱም ከእግዚአብሔር እውነት ውጪ እስካልኾነ ድረስ፡ ያን ንግግር፡ ማንም ማ ይናገረው፥ መጽሐፉንም፡ ማንም ማ ይጻፈው፡ ምንም ዓይነት ልዩነት የለውም።

እኔ፡ በመጽሓፎቼ ጽፌ ያወጣሁት፡ ያንኑ፡ እግዚአብሔር፡ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያ ልጆች ልቦና ላይ (በእኔ ጭምር) ጽፎትና በእነርሱ ዘንድ ተቀባይነት ባላቸው፡ በታወቁት ቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ያሉትን ነው።

ይህን ሥርዓት በተከተለ መልክና ይዘት እስከኾነ ድረስ፡ አለቃ አያሌው ታምሩ ያዘጋጁቸውም ኾኑ፥ በእኔ በተዘጋጁት መጻሕፍት ውስጥ የሠፈሩት የእውነት ቃላት፡ የእግዚአብሔር እስከኾኑ ድረስ፡ እኔ፡ ከእርሳቸው፥ እርሳቸው፡ ከእኔ መጻሕፍት፡ እንዲህ እንዲህ ባለው ቃል ላይ የመወሳሰድ ዘረፋ ተፈጽሟል የሚያስሰኝ ምክንያት ሊኖር አይችልም።

ለነገሩ፡ በእኔ በኩል፡ በዚህ ረገድ፡ የፈጸምኩት አንዳችም ድርጊት፡ ማለትም፡ ከአለቃ አያሌው ታምሩ መጻሕፍት የጠቀስሁት አንድም ቃል እንደሌለ ማረጋገጡ አያዳግተኝም፤ ቢኖር ኖሮ፡ ድርጊቱን፡ አግባብነት ባለው በየመጻሕፍቱ ክፍል፡ በተጠቃሽነት ባመለከትሁት ነበር። መጽሓፎቼ ኹሉ፡ የእግዚአብሔርን መልእክት የያዙ በመኾናቸው፥ የእግዚአብሔሩን መልእክታት ደግሞ፡ በሰዎች ሥራ ዋቢነት ማስመስከሩና ማረጋገጡ፡ ፈጽሞ አግባብነትና ተገቢነት የሌለው፡ ክፉ ድርጊት በመኾኑ፥ ይህን የመሰለውን አሠራር፡ የማላምንበትና ላደርገው የማልሞክረው በመኾኑም፡ እንኳንስ ልተገብረው ይቅርና፡ አስቤውም እንኳ እንዳልነበረ፡ መግለጽ እወድዳለሁ።

የእግዚአብሔርን መልእክት በሚመለከት፡ ካገር ውስጥ ወገኖችም ኾነ፥ ከባዕዳኑ የ"ሊቃውንት" መጻሕፍት መጠቃቀሱን ያልፈለግሁበት፡ አንዱ ምክንያት፡ እምነት ሊጣልባቸው የማይቻል በመኾኑ ነው፤ ይኸው፡ አኹን፡ በአለቃ አያሌው ታምሩ አድራጎት እንደተረጋገጠው ማለት ነው፤ ከእርሳቸው መጻሕፍት ውስጥ፡ ጠቅሼ ቢኾን ኖሮ፡ ይህን የመሰለውን ታላቅ ስሕተት፡ በምን መልክ ልጠግነው እችል ነበር? ከእኔ ዝግጅት ይልቅ፡ የእግዚአብሔር መልእክት መበከሉ፡ ምን ያህል ባሳዘነኝ ነበር።

በእናንተ የመጽሓፍ ትች ፈሊጥና ሚዛን፡ ይህን የመሰለው፡ የእርሳቸው ሥራ፡ "ማር"፥ የእኔ ደግሞ፡ "መርዝ" ከተባለ፥ ከዚያም አልፎ፡ ከላይ እንደጠቀስሁት፡ "crap" የሚለውና ወደኢትዮጵያኛ ልተረጉመው የሚሠቀቀኝ፡ እጅግ ጸያፍ የኾነው የርኵሰት ቃል፡ ለሙላዎቼ መጻሕፍቶቼ ከተሰጠ፡ የእርሳቸውን ማርነት የሚያሳየውን ነጥብ ማሳየት ባያስፈልጋችሁ እንኳ፡ የእኔዎቹን መርዝነት፥ እና/ወይም" crapነት የሚያጋልጡትን ቃሎች፥ ወይም፡ ዐረፍተ ነገሮች፥ ወይም፡ ክፍሎች፡ ለምን ለይታችሁ፡ አላወጣችሁም? አልገለጻችሁምም?

መጻሕፍቶቼ ኹሉ፡ በእግዚአብሔር ስምና ቃላት፥ ደግሞም፡ አለቃ አያሌው ታምሩ ባዋረዷቸውና በዘለፏቸው፡ የቅዱሱ ኪዳን አካል በኾኑት፡ በእነዚያ፡ በሰባቱ ቅዱሳት ቃል ኪዳናት፥ እንዲሁም፡ ራሷ ኢትዮጵያ በኾነችው፡ በቅድስት ድንግል ማርያምና በልጇ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስሞችና ዝክረ ነገሮች የተመሉ ሲኾኑ፡ በመርዝነት እና/ወይም፡ በcrapነት የሚፈረጅ፡ እስኪ፡ ለአብነት እንኳ የሚኾን፡ አንዲት ቃልን፥ ወይም፡ አንዲት ሆሄን ቀርቶ፡ አንዲት ነቍጥን፥ ወይም፡ ነጥብን፡ አውጥታችሁና ለይታችሁ ጠቁሙኝ!?

እንዲያው በደፈናው፡ ስም ማጥፋትማ፡ እንኳንስ፡ የመንፈስ ቅዱስ በኾነው ይቅርና፡ በደካሞች የሰው ወገኖች በኾነው ሥራ ላይ እንኳ አግባብነት የለውም።

፯ኛ፡ Let's come back to your "letter". It seems to me that you have a huge hatred towards Aleqa. Why? Let me guess? He refused to collaborate with you in printing those crap books of yours. Am I right? And besides at that time you were fresh out of prison, delusional, and his refusal was like a death sentence to you. That's so sad. But what was he supposed to do as he were the chairman of the council of the Theologians of the church.

"Was he supposed to give you the green light? I suppose not. Because his sole job was to protect the faith and teachings of the church from false and fictitious craps like your books and the like. So he did the right thing? Don't you think so Nibure-Id?" ላላችሁት፡-

"የእግዚአብሔር መንግሥት የኾነችው የኢትዮጵያ"፡ ማለትም፡ "የኢየሱስ ክርስቶስና የድንግል ማርያም አገልጋይ ነኝ!" ብሎ፡ በይፋ የተናገረና በዚሁ ቃሉ ጸንቶ፡ ይህንኑ ተልእኮውን እያካኼደ የሚገኝ፡ እንደእኔ ያለ ሰው፡ አለቃ አያሌው ታምሩን ኾነ፡ ሌላውን ሰብአዊ ፍጡር፡ እንዴት አድርጎ ሊጠላ ይችላል? ለምንስ ይጠላል? "ኹሉም፡ከእግዚአብሔር ዘንድ የተማሩ ይኾናሉ!" በሚለው የእግዚአብሔር ቃል መሠረት፡ "የተማርኩት፡ ከሰው ሳይኾን፡ ከእግዚአብሔር ነው! ከዚህም የተነሣ፡ ተልእኮዬ፡ በመንፈስ ቅዱስ የሚመራ ነው!" እያልሁ፡ እንዴት፡ ሰውን ልጠላ እችላለሁ? በጥላቻ ኾኜስ፡ እንዴት፡ በሰዎች ላይ እጽፋለሁ?

እንግዲያ፡ "ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ!" በሚለውና የእግዚአብሔርን መልእክት በያዘው መጽሓፌ ውስጥ፡ ራሷ ኢትዮጵያ የኾነችው፡ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም፡ በፈጣሪዋ ፊት፡ ስማቸውን በመጥቀስ የተፋረደቻቸው ልጆቿ፡ አለቃ አያሌው ታምሩ ብቻ ሳይኾኑ፡ ዛሬ፡ በሕይወተ ሥጋ ያሉትና በሞተ ሥጋ የተለዩት ሰዎች ጭምር ስለኾኑ፡ እንኪያ፡ የእነዚያን ኹሉ ስም አንሥቼ በመጻፌ፡ "በእነርሱ ላይ ሳይቀር፡ ጥላቻ አለብኝ!" ማለት ነውን? አይደለም።

በዚህ መጽሓፍ ኾነ፡ በሌሎቹም መጻሕፍቴ፡ እኔ፡ በመልእክተኛነት፥ ወይም፡ በተላላኪነት ያገለገልሁ ከመኾኔ በቀር፡ ሌላ፡ ከዚህ ያለፈ፡ ተልእኮ እንደሌለኝ፥ የመልእክቱ ባለቤትና ላኪው ማን እንደኾነም፡ "ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ!" የሚለው፡ ራሱ፡ የመጽሓፉ ስያሜና በውስጡ የሠፈረው መልእክት፡ በሚበቃ ያስረዳሉ።

ይኸውም፡ “ንግሥተ አዜብ [የደቡብ ንግሥት=ኢትዮጵያ] በፍርድ ቀን ተነሥታ፡ ከዚች ትውልድ ጋር ትፋረዳለች፤ የሰሎሞንን ጥበብ ትሰማ ዘንድ፡ ከምድር ዳርቻ መጥታለችና፤ እነሆ፡ ከሰሎሞን የሚበልጥ፡ በዚህ አለ።” ብሎ፡ ከዛሬ ኹለት ሺህ ዓመታት በፊት፡ ልጇ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ በተናገረላት ቃል መሠረት፡ እነሆ፡ ይህችው ኢትዮጵያ፡ ድንግል ማርያም፡ ለእያንዳንዳቸው፡ በቃል ኪዳን ሹመት የሰጠቻቸውን የአገልግሎት አደራና ኃላፊነት፡ “ምነው፡ በታማኝነት ሳትፈጽሙ ቀራችሁ!?” እያለች፡ እኒህኑ፡ በሕይወተ ሥጋና በሕይወተ ነፍስ የሚገኙትን ልጆቿን፡ በዚሁ ፈጣሪዋ ፊት እየተፋረደቻቸው ያለች መኾኗን ነው። (ማቴ. ፲፪፥ ፵፪።)

ደግሞስ፡ ያን፡ በደርግ እሥር ቤት ኾኜ ያዘጋጀሁትንና በአጠቃላይ ስያሜው፡ “አዳምና ሔዋን፡ በኢትዮጵያ!” የተባለውን፥ በውስጡ ግን፡ ሦስት ጥራዞችን የያዘውን መጽሓፍ፡ የትና መቼ አያችሁትና ነው፡ crap የሚለውን፡ ያንኑ፡ ለሌሎቹ መጻሕፍቴ የሰጣችሁትን፡ የባዕዳኑን አስጸያፊ የርኵሰት ቃል፡ በዚህም ላይ የለደፋችሁበት? ወይስ፡ አለቃ አያሌው ታምሩ፡ እንደለመዱት፡ “አሉባልታ ነው!” ብለው፡ ስለዚሁ መጽሓፍ የነገሩዋችሁ ነገር ኖርዋል?

ይህን የመሰለው ሓሜት፡ እንደገና፡ የየራሳችሁን ጥፉና ክፉ ማንነት አግዝፎና አጉልቶ የሚያሳይ ከመኾኑ በቀር፡ ሌላ ረብኅ የለውም።

በእናንተ ጭንቅላት፡ ይህን ለመሰለ የነቀፌታ ትችት ወደተዳረገው፡ ወደዚሁ መጽሓፍ፡ “ገባ ብላችሁ፡ በውስጡ ያገኛችሁት አንዳች እንከን ካለ፡ እስኪ፡ እባካችሁ ጠቁሙኝ!” ብትባሉ፡ መልሳችሁ፡ ምን ይኾናል? መልስማ የላችሁም፤ ሊኖራችሁም አትችሉም፤ እንደአለቃችሁ አነጋገር፡ የምትኖሩት፡ “በአሉባልታ” ነውና። ይህንም እውነታ፡ ያው፡ በየቦታው፡ በጽሑፍ እንደተብራራው፡ የራሳቸው፡ የአለቃ አያሌው ታምሩ፡ የቀደመ ድርጊት፡ አረጋግጦ ገልጾታል።

ያም ድርጊት፡ እንደሚከተለው፡ ባጭር፡ ሊገለጥ ይቻላል፡- እርሳቸው፡ በሰብሳቢነት ይመሩት ለነበረው፡ ለቤተ ክህነቱ የሊቃውንት ጉባኤ፡ እንኳንስ፡ በከፍተኛ ደረጃ፡ ማለትም፡ በጊዜው፡ የቤተ ክህነቱ መሪና ተጠሪ በኾኑት፡ በእጨጌው ቃልና በቤተ ክህነቱ ጠቅላይ ሥራ አስኪያሃጅ እጅ፡ እኔ ራሴ ጭምር ባለሁበት፡ በአደራ የተሰጠው፡ ከላይ የተጠቀሰው ድርሰቴ ይቅርና፡ ማንም ተራ ሰው፡ በግሉ ያቀረበው ድርሰት እንኳ፡ ይህን የመሰለው በደል “ይፈጸምበታል!” ተብሎ ሊታሰብ ከቶ አይቻልም፤ ይኸውም፡ ከተለመደው የጉባኤ ሥርዓት ውጪ፡ ድርሰቱ፡ ፈጽሞ የሚነቀፍ ቢኾንም እንኳ፡ እንዴት፡ የድርሰቱ ባለቤት፡ ለአንዲት ጊዜ እንኳ፡ ተጠርቶ ሳይጠየቅ፥ ወይም፡ በቃል፥ ወይም፡ በጽሑፍ የተገለጸ ምክንያት፡ ለደራሲው ሳይደርሰው፡ ድርሰቱ፡ ከአያሌ ወራት በኋላ፡ ዝም ብሎ ሊመለስለት የማይገባ መኾኑ ነው።

ይህ የኾነው፡ ወይም፡ እርሳቸው፡ ይህን ያደረጉት፡ ለምንድር ነው? ደራሲውን ጠርተውና በግንባር ለማነጋገር በመፍራት፥ የድርሰቱን እውነተኛነት ለማሳመን፡ የሚያቀርባቸውን ማስረጃዎችና መከላከያዎችም ተቋቁመው ለመመከት እንደማይችሉ በመሥጋት አይደለምን? ፊት ለፊት፡ ተገናኝቶ መነጋገሩ ቀርቶ፡ ይኸው የድርሰቱ ባለቤት፡ በጽሑፍ መልስ ሊሰጥ የሚችልበት መንገድ እንኳ እንዳይኖር፡ ለደራሲው፡ የጻፉት፡ አንዳችም የይፋ ደብዳቤ አልነበረም። ወይም፡ እኔን ጠርተው፡ በቃል ማነጋገሩን ቢፈሩ እንኳ፡ “በመጽሓፉ ውስጥ ያገኘነው ስሕተት፥ ወይም፡ ጉድለት፡ ይህ ነውና፡ እርሱን አስተካክል! ወይም፡ ድርሰቱ፡ በዚህ ምክንያት፡ በእኛ ዘንድ ተቀባይነት የሌለው ስለኾነ፡ መልሰነዋል!” ተብሎ፡ እንዴት አይገለጽልኝም።

እንግዴህ፡ ይኼን ዓይነቱን አሠራር ነው፡ እናንተ፡ እነፍርደ ገምድሎች፡ ትክክል ነው ብላችሁ የምትሟገቱ? እኔን፡ እንደአጥፊ፥ እርሳቸውን፡ አለቃ አያሌው ታምሩንም፡ እንደአልሚ ቆጥራችሁ፡ በእኔ ላይ የሞት ፍርድን የምታስወስኑ? እርሳቸውንም፡ ከበደል ነጻ የምታደርጉ? ኹላችንም፡ ልንፈራ የሚገባን ግን፡ እውነተኛውን ዳኛ፡ ኃያሉን እግዚአብሔርን እንጂ፡ ስሑቱንና ደካማውን ሰብአዊዉን ፍጡር አልነበረም።

ደግሞስ፡ ያን መጽሓፌን፡ በሊቃውንት ጉባኤ ሊቀ መንበርነታቸው ያልተቀበሉት፡ “የቤተ ክርስቲያንን እምነትና ትምህርት፡ ከሓሰትና ከልብወለድ ተረት ለመጠበቅ፡ ሲሉ ነው!” ብላችሁ የሠነዘራችሁትን ሙግት፡ ከየት አገኛችሁት? እናንተ፡ መጽሓፉን ካዩት፡ ከእርሳቸውና ከጉባኤው አባሎች መካከል ስላልነበራችሁ፡ መጽሓፉ፡ ለዚያ መሥፈርት የተዳረገ መኾኑን፡ እንዴት አወቃችሁ?

ለመኾኑ አለቃ አያሌው፡ በሊቃውንት ጉባኤ ሊቀ መንበርነታቸው የጠበቁት፡ የቤተ ክርስቲያን እምነትና ትምህርት ምንድር ነው? የዛሬዪቱ ኢትዮጵያና ሕዝቧ፡ የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን አገርና መንግሥት መኾናቸው፡ በይፋ ሲሻርና በእነርሱ ላይ የክርስቶስ ተቃዋሚ የኾነው የዲያብሎስ አገዛዝ በአዋጅ ተተክቶ ሲሰፍን፥ ምን አሰቡ? አስበውስ፡ ምን ተናገሩ? ምንስ አደረጉ? እንደቅዱስ እስጢፋኖስ፡ ለሰማዕትነቱ፡ ፊታውራሪ ኾነው፡ ስለመለኮታዊው የኢትዮጵያ ሥርዓተ መንግሥት፡ በቀዳሚነት በመመስከር፡ ሌሎቹ፡ ቤተ ሕዝቡና ቤተ ምልክናው “እምቢ!” ቢሉ እንኳ፡ እርሳቸው፡ ቤተ ክህነታቸውን ማዳን ይገባቸው አልነበረምን?

ነገር ግን፡ ያ ቀርቶ፡ የኾነው፡ ሌላ ኾኖ ተገኘ። ያም፡ ከቤተ ምልክናውና ከቤተ ሕዝቡ ጋር ተስማምተው፡ በግብረ አበርነት፡ በቅዱሱ ኪዳን ላይ፡ ያን የመሰለውን፡ የክህደት፥ የዓመፅና የአምልኮ ምንዝርና ኃጢአታቸውን፡ በገሃድ ፈጸሙ፤ በዚያ አቋማቸውም፡ እስከመጨረሻው ከመቀጠል በቀር፡ በኃላፊነታቸው፡ ያሰቡት፥ የተናገሩትና ያደረጉት፡ አንዳችም፡ የቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖታዊና ምግባራዊ በጎ ሥራ አልነበረም።

ደግሞስ፡ ሊጠበቅ የሚገባው ሃይማኖትና ትምህርት፥ ሥርዓትና አምልኮ፡ የትኛው ነው? ኢትዮጵያና ልጆቿ፡ ከአዳምና ሔዋን ጀምረው እንደሓረግ ተያይዞ፡ በኖኅ፥ በመልከጼዴቅ፥ በአብርሃም፥ በሙሴና በዳዊት በቀጠለው፥ በመጨረሻም፡ በድንግል ማርያምና በልጇ በኢየሱስ ክርስቶስ በታተመው፡ በቅዱሱ ኪዳን አማካይነት፡ ከእግዚአብሔር፡ በቀጥታ ተቀብለው፡ እስከዛሬ ያቆዩት የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት፥ እርሱም፡ በተዋሕዶነት የከበረው አይደለምን? ወይስ፡ ያ ቀርቶ፡ እርሳቸውና እናንተ፡ ዛሬ እያስተጋባችሁት ያላችሁት፡ የግብፅ orthodoxሳዊነት?

ግብፃውያን ኾኑ፡ ሌሎቹ ባዕዳን፡ ከረዥም ጊዜ ጀምሮ እንዲጠፋ የጣሩበት፥ አኹንም፡ ያለ፡ የሌለ ኃይላቸውን፡ በበለጠ በማጠናከር፡ በዚሁ ጥረታቸው የቀጠሉበት፥ እርሱ ግን፡ የእግዚአብሔር ሥራ በመኾኑ፡ ሊጠፋላቸው ያልቻለው፡ እውነተኛው ኢትዮጵያዊ ማንነታችን፡ በሰዎች አስተሳሰብ ሳይበከል፡ ንጹሕ ከኾነው ሃይማኖታዊና ምግባራዊ፥ ሥርዓታዊና አምልኳዊ ትውፊቱ ጋር እንዲቀጥል ለማድረግ፡ የሰማዕትነት ተልእኳችንን በማካኼድ ላይ የምንገኘውን፡ እኔንና እኔን የመሰሉትን መቃወም፡ የቤተ ክርስቲያንን እምነትና ትምህርት መጠበቅ አይደለም፤ የባዕዳኑ አጋርና መሣሪያ በመኾን፡ የእነርሱን ዓላማ በበለጠ ማራመድ እንጂ።

እዚህ ላይ፡ ይህን ርእስ በሚመለከት፡ ስንቱ፡ ተዘርዝሮ ያልቃል? ብዙው፡ በመጻሕፍቴ ተብራርቶ ተገልጿል። እነዚህ መጻሕፍቴ የያዟቸው፡ የእግዚአብሔር መልእክታት ደግሞ፡ በአለቃችሁ ዘንድ፡ "አሉባልታዎች!"፥ በእናንተም ዘንድ፡ crap ተብለው ስለተመደቡ፡ "እነርሱን ተመልከቷቸው!" ብዬ ላሳስባችሁ አይቻለኝም።

እውነታው ይህ ከኾነ፡ ራሳቸው አለቃ አያሌው፡ ከሰው ሳይኾን፡ በይበልጥ፡ ከእግዚአብሔርና ከቅድስት እናቱ፡ በተቀበሉት መለኮታዊ አደራና ኃላፊነት፡ ዋና ግዳጃቸው የኾነውን፡ የጉባኤውን ሥርዓት መፈጸምና ማስፈጸም፡ ከቶ ያስፈራቸው ምንድር ነገር ነበር? ያ ጊዜ እንኳ፡ በደርግ ምክንያት፡ የእርሳቸው ሥልጣን ሳይቀር፡ የገነነበት ዘመን ነበር። እንደእውነቱ ከኾነ፡ በዚያን ቀውጢ ወቅት፡ ለሕይወቴ ጭምር መፍራት ይገባኝ የነበርሁት፡ እኔ እንጂ፡ እርሳቸው አልነበሩም። ምክንያቱም፡ "አብዮቱን ያደናቅፋሉ!" በማለት፡ በጦር ኃይሎች ተይዤና ከደርግ የሞት ፍርድ፡ በእግዚአብሔር ቸርነት ተርፌ፡ ከእሥር የተለቀቅሁ እኔ ስለነበርሁ፥ ድርሰቴም፡ ያን የመሰለውን፡ የደርግን እግዚአብሔር አልባ ርእዮተ ዓለም የሚቃወም በመኾኑ ነው።

ታዲያ! እኔ፡ እንደዚያ ደፍሬ፡ ያን የመሰለውን ድርሰት፡ በይፋ ሳቀርብላቸው፡ እነርሱን፡ ከቶ ምን አስፈራቸው? የፍርኀታቸው መንሥኤ፡ ምናልባት፡ የእኔን ድርሰት ቢያሳልፉ፡ ያ ሰበብ ኾኖ፡ በእነርሱ፡ ማለትም፡ በእርሳቸው፡ በአለቃ አያሌው ታምሩና በሊቃውንቱ ጉባኤ ላይ ብቻ ሳይኾን፡ በጠቅላላ፡ በቤተ ክህነቱም ላይ ጭምር፡ የደርግን፡ የጭካኔ በትር፥ ወይም፡ ሠይፍ እንዳያስከትልባቸው በመሥጋት እንደኾነ አላውቅም።

በእርግጥ፡ ምክንያታቸው፡ ይህ ከኾነ ደግሞ፡ ይኸው ነገር፡ በቤተ ክህነት ላይ፡ ሌላ የባሰ ትችትን የሚጋብዝ ይኾናል፤ ይኸውም፡ “እንግዲያውማ፡ ቤተ ክህነት ልትቆም የሚገባት፡ ለእግዚአብሔር እውነት እንጂ፡ እንዲህ፡ ለዲያብሎስ ሐሰት ከኾነ፡ መኖርዋ ምን ይጠቅማል? ይህን የመሰለና የክርስቶስ ተቃዋሚ ከኾነ አገዛዝ ጋር ተባባሪ ከኾነች፡ በመለኮት ውግዘት ተለይታ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት በኾነችው፡ በኢትዮጵያ ቤተ ሕዝብ ፊት፡ በጊዜው፡ “ለፍርድ መቅረብ አለባት!” ያስሰኛል።

ያ መጽሓፌ፡ በዚያን ጊዜ ሳይታተምና ለሕዝብ ሳይሠራጭ ቢቆይም፡ ከዚያ በኋላ፡ ለዘመኑ ካላቸው አስፈላጊነት የተነሣ፡ በእግዚአብሔር ፈቃድና ቸርነት፡ ቅድሚያ ተሰጥቷቸው፡ የተዘጋጁትንና ለሕዝብ የተሠራጩትን ሌሎቹን፡ ቁጥራቸው አነስተኛ ያልኾነውን መጻሕፍቴን፡ እናንተም እንዳወቃችኋቸው ለመረዳት ችያለሁ። ታዲያ! ይህ ኹኔታ፡ ምንን ያስታውሳችኋል? ያመለክታችኋልም? አለቃ አያሌው ታምሩ፡ ነፍሳቸውን ይማርና! ያን መጽሓፌን እንዳይታተም፡ የፈጸሙት ደባ፡ “በአንተ ላይ፡ ተወስኖ እንደተፈጸመ የሞት ፍርድ ነበር!” ብላችሁ የጻፋችሁት ኃይለ ቃል፡ ደርግ፡ በእኔ ላይ ወስኖት፡ በእግዚአብሔር ኃይል የተሻረልኝ፡ ያ የሞት ፍርድ፡ እናንተንና መሪያችሁን፡ ከፉኛ ያስቆጫችሁ መኾኑን ማረጋገጣችሁ አይደለምን?

ይኹን እንጂ፡ ለእናትና ልጁ ምስጋናዬ ይድረሳቸውና፡ ያ ኹሉ፡ ፍጹም የጥላቻ አስተሳሰባችሁ፡ ይኸው፡ ከንቱ ኾኖ፡ እኔ፡ ምድራዊ ህልውናዬን፡ በሕይወተ ሥጋ ቀጥዬ፡ እነሆ፡ ከዚያ፡ በደርግ እሥር ቤት ውስጥ፡ ካዘጋጀሁት መጽሓፌ መልእክት ጋር ተመሳሳይነት ያላቸውን፡ እነዚህን፡ በርካታ መጻሕፍት ለማፍራትና ለማበርከት ችዬ፡ ተልእኮዬን በመቀጠል ላይ እገኛለሁ።አኹንስ፡ እናንተ፡ በእውነት፡ የእግዚአብሔር አማኞች ብትኾኑ ኖሮ፡ ይህ በመኾኑ፥ በዚህ፡ በመንፈስ ቅዱስ ድንቅ ሥራ፡ ሊሰማችሁ የሚገባ ምን ይኾን ነበር? ምስጋናና ደስታ እንጂ፡ ይህን የመሰለ በቀል አልነበረም። አዎን! ሊታዘንላችሁና ሊጸለይላችሁ የሚገባ ፍጡሮች ናችሁ።

ይህንም ኾነ፡ የቀሩትን መጻሕፍቴን፡ አለቃችሁም ኾኑ፡ እናንተ፡ በደፈናው ከመንቀፍና ከመዝለፍ በቀር፡ “ስሕተቱና ጉድለቱ ይህ ነው!” ብላችሁ፡ አለቃ አያሌው ታምሩ በሕይወተ ሥጋ እያሉም ኾነ፡ ዛሬ፡ እናንተ፡ በሕይወተ ሥጋ እያላችሁ፡ የምትናገሩበት አንደበት፥ ወይም፡ የምታቀርቡት ነጥብ ስለሌለ፡ በያላችሁበት፡ ዐርፋችሁ መቀመጥ በተገባችሁ ነበር፤ ዳሩ ግን፡ ሚቹም፥ እናንተም፡ በእግዚአብሔር ላይ፡ በሥውርና በምሥጢር ስትፈጽሙት የኖራችሁት ደባ፡ ይኸው ተከሥቶ፡ ለኹሉ፡ በብርሃን ይገለጥ ዘንድ፡ መንፈስ ቅዱስ፡ “ፊታችሁን ጸፍቶ!” አለቃ አያሌው ታምሩንም፡ በመጽሓፍ እንዲጽፉ፥ እናንተም፡ በጎዋ ሰሌዳችን አማካይነት፡ እ-ጦማሮቻችሁን እንድትልኩልኝ አስገድዶ፡ ያው፡ የመጀመሪያውን ደብዳቤዬን፡ ለመሪያችሁ፡ ለአለቃ አያሌው ታምሩ፥ ይህን ኹለተኛውንም፡ ለእናንተ እንድጽፍ አደረገኝ። ለመንፈስ ቅዱስ፡ ምስጋናዬ ይድረሰውና!

፰ኛ፡ So, I think his strong belief and character still haunts you..till this day. I am sorry for you. ...In the other hand I fill sorry for you, your letter clearly shows how much you suffer by complex in comparing your self with the great man Like-Likawent Aleka Ayalew Tamiru and how much your are hunted by his clean spirit. Poor guy!! **ላላችሁት፡-**

**የአለቃ አያሌው ታምሩ አክራሪ አማኞችና ተከታዮች መኾናችሁ፡ በእ-ጦማሮቻችሁ ይዘት፡ በቀላሉ ይታወቃል፤ ከዚህ አንድነታችሁና ፍቅራችሁ የተነሣ፡ ከእርሳቸው ጋር ያላችሁን፡ የአሳብም ኾነ፥ የመንፈስ ግንኙነታችሁን የቀጠላችሁ፡ ምናልባት፡ እናንተ ስለኾናችሁ፡ ምትሓታቸውም እየተመላለሰ የሚኀበኘው እዚያው እናንተኑ ነው። ስሜን አንሥተው፥ የእግዚአብሔርን ሥራ በመቃወም፥ በመንፈስ ቅዱስና በአምላክ እናትም ላይ የኑፋቄ ቃልን በመሠንዘር፡ በመጽሓፍ ያወጡት ትችት ደርሶኝ እስካየሁትና መልሱን በዚያ ደብዳቤዬ እስከሰጠኋቸው ድረስ፡ ስለእርሳቸው ያሰብኩት ምንም ነገር አልነበረም፤ እንዳስብ የሚያደርገኝ፡ አንዳችም ምክንያት የለምና።**

**ከእኔ ጋርማ፡ ከዚህ ቀደም እንደገለጽሁት፡ ከዘመኑ የቤተ ክህነት እጨጌ በታዘዘው መሠረት፡ መጽሓፌን፡ በሊቃውንት ጉባኤ ሊቀ መንበርነታቸው በተረከቡባት፡ በዚያች ጥቂት አፍታ፡ ካልኾነ በቀር፡ ከዚያ በፊት፡ ለብዙ ዓመታት፥ ከዚያ በኋላም፡ ለዘለዓለሙ አልተገናኘንም።**

፱ኛ፡ Let me finish my message by giving you a simple advice. It was the advice the great Liq gave you when he was alive. "Kezih kifu Alem raswon'na betesebwon yadnu." **ላላችሁት፡-**

**የእግዚአብሔር የኾነውንና ለቅድስት እናቱ የተሰጠውን ከምታስተሓቅሩ፥ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትም ከማታምኑ፥ በዚህ ኹሉ አድራጎታችሁ፡ መንፈስ ቅዱስን ከምትቃወሙ፡ አለቃ አያሌው ታምሩንና እናንተን ከመሰሉ ሰዎች፡ ምን ዓይነት ምክር የሚሰጥ ኾኖ ነው፡ ምክራችሁ የሚፈለገው? በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያ ልጆች ዘንድ፡ ይህን ምክራችሁን የሚሻው፡ ማንም የለምና፥ አይኖርምምና፤ ይልቅስ፡ የሚስማማውና የሚገባው፥ የሚያስፈልጋችሁና የሚጠቅማችሁ፡ እዚያው፡ ለእናንተውና ለመሰሎቻችሁ ስለኾነ፡ እዚያው፡ ለእየራሳችሁ አውሉት!**

፲ኛ፡- ከመካከላችሁ አንዱ፡ ለእ-ጦማርዎ፡ Shame on you! ማለትም፡ በአቅራቢያና በመለስተኛ ትርጉሙ፡ "ማፈሪያ!" ወይም፡ "አቤት ቅሌት!" ሊባል የሚችል ርእስን የሰጡት፥ ራስዎንም፡ ለእኔ ሲያስተዋውቁ፡ With a surprising coincidence I got a chance to see you in the office of the late Like-Likawent Aleka Ayalew in the then Yelekawent Gubae office right after you went out from the prison of Derg ያሉት፥ ከዚህም ጋር፡ First of all I haven't enough words to express my sadness and the shame I feel about what you did ሲሉ የጻፉት ሰው፡ "ስሜ፡ 'ቀሪን ገረመው በላቸው' ነው!" ብለዋል።

የማንነትዎና የስም አጠራርዎ፥ የጽሑፍ አቀራረብዎም ነገር፡ እንቆቅልሽ እንደኾነብኝ ልሸሽገው ያዳግተኛል። ምክንያቱም፡ እኔ፡ በደርግ እሥር ቤት ሣለሁ፡ በእጄ ጽፌ ያዘጋጀሁትን፡ "አዳም እና ሔዋን፡ በኢትዮጵያ!" የሚለውን መጽሓፍ፡ በዘመኑ የቤተ ክህነት መሪ፡ በእጨጌ ተክለ ሃይማኖት ጥያቄና ፈቃድ፡ በሊቃውንቱ ጉባኤ ታይቶ እንዲታተም በመታዘዙ፡ መጽሓፉን፡ ለጉባኤው እንዲያስረክቡ ከተላኩት፡ ከጊዜው፡ የቤተ ክህነቱ ጠቅላይ ሥራ አስኪያሃጅ፡ ከሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው ጋር ዐብሬ እንድኼድ ስለተጋበዝሁ፡ እዚያ በተገኘሁባት ሰዓት፡ ከጉባኤው ሰብሳቢ፡ ከአለቃ አያሌው ታምሩና ከአባሎቹ በስተቀር፡ ሌላ የውጭ፡ ማንም ሰው ስላልነበረና፥ በዚያን ጊዜ ኾነ፡ ከዚያ በፊት፡ እኔ፡ በዚህ ስም የማውቀው ሰው ባለመኖሩ ነው።

ይኸው ስምዎ፡ እውነተኛ፥ ወይም፡ የብዕር ስም ይኹን፥ ወይም፡ አይኹን፡ ወደፊት፡ ጊዜ የሚገልጠውን፡ ይህን እንቆቅልሽ፡ ለጊዜው እንተወውና፡ ለዚሁ እ-ጦማራችሁ፡ Shame on you! ብላችሁ፡ የሰጣችሁት አርእስት፡ መቼም፡ በቀጥታ ለእኔ መኾኑ ግልጽ ስለኾነ፡ እስኪ፡ እናንተኑ መልሼ ልጠይቃችሁ! ይኸውም፡ "ይህ፡ በቃለ አጋኖ ታጅቦ የቀረበ፡ የማዋረጃ ቅጽል ስም፡ ሊሰጥ የሚገባው፡ ለማንኛችን ነው? የእግዚአብሔርን ቃል መሠረት በማድረግ፡ የእርሱ የኾኑትን፡ እውነቱንና መንግሥቱን፥ የኢትዮጵያና የኢትዮጵያዊነት ሕያዋን መገለጫዎችና መታወቂያዎች የኾኑትን፡ ሰባቱን ቅዱሳት ኪዳናት፥ የአምላክ እናት የኾነችውንም፡ የእመቤታችንን ማንነት በሚመለከት የጻፍሁት እኔ? ወይስ፡ እኒህን፡ የመንፈስ ቅዱስ የኾኑትን ሥራዎች፡ በግልጽ በመንቀፍና በመቃወም መልስ የሰጣችሁ እናንተ?

ሰብኣዊ ኅሊና ኖርዋችሁ፡ የምትሠሩበት ከኾነ፡ ይኸው ኅሊናችሁ፡ እያረጋገጠ የሚነግራችሁ፡ ያለጥርጥርና ውልውል፡ Shame on you! የሚለው፡ የራሳችሁ ምርጫ የኾነው ርእስ፡ የሚስማማውና የሚገባው፡ ለእናንተ መኾኑን ነው። በዚህ ድርጊታችሁ፡ በቃላት ሊገለጽ የማይቻል፡ እጅግ የረቀቀና እስከአጥንት ጠልቆ የሚወጋ ኀፍረት ሊሰማችሁ እንደሚገባ፡ አዎን! ከእየራሳችሁ ኅሊና የበለጠ ሊነግራችሁ የሚችል ፍጥረታዊ ኃይል አይኖርም።

**፲፩ኛ፡** Do you really believe in the values of Ethiopiawenet? I doubt! If you would have had a true belief in Ethiopiawenet what you did is just to the contrary of decency, Christianity and humanity. **ላላችሁት፡-**

*የኀፍረት ነገር ከተነሣ ዘንድ፡ የሚያስገርመው፡ እናንተ፡ ስለኢትዮጵያዊነትና በእርሱ፡ በእውነት ስለማመን፥ ስለክርስቲያናዊነትና ስለሰብአዊነት፥ ስለጨዋነትም ለመናገር መድፈራችሁና ስትናገሩም አለማፈራችሁ ነው። ለመኾኑ፡ እነዚህን እውነታዎች ስትዘረዝሩ፡ የትኞቹን ዓይነት ኢትዮጵያዊነትና ክርስቲያናዊነት፥ ሰብአዊነትና ጨዋነት ማለታችሁ ነው? የእናንተዎቹን ማለታችሁ አይደለምን? እነዚያ፡ የእናንተዎቹማ፡ ከላይ፡ ቀደም ብሎ እንደተብራራው፡ እውነተኞቹ ሳይኾኑ፡ ሓሳውያኑና አሳሳቾቹ ናቸው።*

*ብታውቁትም፡ ባታውቁትም፥ ብትቀበሉትም፡ ባትቀበሉትም፡ ያለቅዱሱ ኪዳን፥ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት የሉም፤ ሊኖሩም አይቻልም። ቅዱሱ ኪዳንም፡ ሰባቱን ቅዱሳት ኪዳናት አዋሕዶ የያዘው ነው፤ አዎን! ያለእነዚህ፡ ያለሰባቱ ቅዱሳት ኪዳናት፡ ኢትዮጵያዊው ተዋሕዶ ሃይማኖት ኾነ ክርስቲያናዊነት፥ ሰብአዊነትና ጨዋነት የሉም።*

*ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ያስገኙትን፥ የቅዱሱ ኪዳን አካል የኾኑትን፡ ሰባቱን ኪዳናት፡ <u>አሉባልታዎችና ስሕተት</u>፥ ያደረጋችኋቸው፥ ኢትዮጵያ፡ ድንግል ማርያም ናት! ማለትንም፡ <u>የሚነዛ ወሬ</u> ያደረጋችሁ፡ እናንተ እና አለቃችሁ፡ እንዴት፡ ስለኢትዮጵያዊነትና በእርሱ፡ በእውነት ስለማመን፥ ስለክርስቲያናዊነትና ስለሰብአዊነት፥ ስለጨዋነትም መናገር ትችላላችሁ? አለቃችሁና እናንተ፡ ስለእነዚህ የቊም ነገር ባሕርያት ስትናገሩ እኮ፡ የምትናገሩት፡ የሰውኛውን፡ ማለትም፡ ሓሰተኛውንና አስመሳዩን፥ ጊዜያዊዉንና ሰው-ሠራሹን ኢትዮጵያዊነትና ክርስቲያናዊነት፥ ሰብአዊነትና ጨዋነት እንጂ፡ ስለእውነተኞቹና ስለመለኮታውያኑ ሊኾን፡ ከቶ አይችልም።*

*እኛ ግን የምንናገረው፡ የእግዚአብሔር ሥራ በኾነውና በመንፈስ ቅዱስ በሚመራው፡ በእውነተኛው የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነትና ከእርሱ፥ ለእርሱና በእርሱ በተገኙት፡ በእውነተኛዪቱ የኢትዮጵያ ተዋሕዶ ሃይማኖት፥ በእውነተኛው ኢትዮጵያዊ ጨዋነትና ሰብአዊነት ነው። መሠረታዊ ልዩነታችን እዚህ ላይ ነው፤ የእኛ፡ የእግዚአብሔሩና እውነተኛው ሲኾን፡ የእናንተ ደግሞ፡ ሰብአዊውና ሓሳዊው ነው። ማናቸውም፡ የእግዚአብሔር የኾነው ኹሉ ደግሞ፡ ከሰውኛው እንደሚበልጥ፡ እናንተ እና አለቃችሁ ጭምር ተስማምታችሁ የምትቀበሉት እውነታ ነው።*

*ስለዚህ፡ እኛ፡ ስለኢትዮጵያዊነት፥ ወይም፡ ስለሃይማኖት፥ ወይም፡ ስለሰብአዊነት፥ ወይም፡ ስለጨዋነት ስናስብ፥ ስንናገርና ስናደርግ፡ የእግዚአብሔር ስለኾኑት፡ ስለእውነተኞቹና ስለመልካሞቹ መኾኑን ልታውቁት ይገባል።*

አለቃ አያሌው ታምሩ፡ በመንፈስ ቅዱስ ላይ ስለፈጸሙት ታላቅ ኃጢአት፡ እኔ፡ ተገቢውን በማተት የጻፍኩት ደብዳቤ፡ በእናንተ ዘንድ፡ ከኢትዮጵያዊነት እሴቶችና እምነት፥ ከጨዋነትና ከሰብአዊነት ውጪ እንደኾነ አድርጋችሁ የቆጠራችሁት፡ ከዚሁ ልዩነታችን የተነሣ መኾኑን እንድትገነዘቡት ያስፈልጋል።

ስለኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት፡ በሦስት ተከታታይ ጥራዞች አዘጋጅቼና አሳትሜ፡ ለሥርጭት ያበቃኋቸውንና የእግዚአብሔር መልእክታት የኾኑትን መጻሕፍት፡ እናንተና አለቃችሁ ልትቀበሏቸው ያልቻላችሁት፥ እንዲያውም፡ crap የሚለውን፡ ጸያፍ የርኵሰት ቅጽልን የሰጣችኋቸው በዚሁ ምክንያት ስለኾነ አያስደንቅም።

፲፪ኛ፡ Pls. don’t make your self a cause of insults to the name of the Almighty God and to our holy church. Whether you are bad or good you are the product of this church. ላላችሁት፡-

ቅዱሱን የእግዚአብሔርን ነገር በማወናበድ አታምታቱት! ስለዚህ ርእሰ ነገር፡ ቀደም ብዬ፡ በሚበቃ አብራርቻለሁ። “ይህች” ብላችሁ፡ እኔን ያፈራችኝን ቤተ ክርስቲያን፡ እንደገና ልታስተዋውቁኝ ሞክራችኋል፤ ይህን ስታደርጉ፡ የየትኛዋ ቤተ ክርስቲያን ልጅ መኾኔን፡ ለምን ለይታችሁ አልተናገራችሁም?

እኔኮ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት የኾነችው ኢትዮጵያ፡ ካፈራቻቸውና ከሚያገለግሏት ታማኞች ልጇ መካከል አንዱ ነኝ። እርሷም፡ የአቋሚ ግንድ ከኾነው ከቤተ ሕዝቡ፡ በአንድ ወገን፡ "የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን" በሚል አጠራር የምትታወቀውንና የመንፈሳዊው አገልግሎት ዘርፏ የኾነችውን፡ ኢትዮጵያዊቷን ቤተ ክህነት፥ በኹለተኛው ወገን ደግሞ፡ የሥጋዊው አገልግሎት ዘርፏ የኾነውን ኢትዮጵያዊዉን ቤተ ምልክና፡ ከራሷ አሥርፃ ያስገኘች ናት።

ይህችው ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ከአዳምና ሔዋን አንሥታ፡ በቅዱሱ ኪዳን፡ ከፈጣሪዋና ከቅድስት እናቱ ጋር የተጋባችውን ቃል ኪዳኗን፡ አክብራና ጠብቃ፥ አጽንታም፡ እነሆ፡ ለ፯ሺ፭፻፪ ዓመታት በፍጹም ነጻነት የኖረችውና አኹንም እየኖረች ያለችው ናት። እኔም፡ የዚች መንግሥት አካል የኾነችው፡ የእውነተኛዋ የኢትዮጵያ ቤተ ክህነት ልጅና አገልጋይ፥ ተጠያቂና ተጠሪ ነኝ።

መሪያችሁ አለቃ አያሌው ታምሩና እናንተ ግን፡ በኢትዮጵያ፡ የግብፅ Orthodox ቤተ ክርስቲያንነቷን ተቀብላና አምና፥ በሕግና በአዋጅም አጽንታ የኖረችው፥ የዛሬዪቱ ቤተ ክህነት (ቤተ ክርስቲያን) ልጆችና አገልጋዮች፥ ተጠያቂዎችና ተጠሪዎችም ናችሁ።

እርሷም፡ በቅዱሱ ኪዳን፡ ከፈጣሪዋና ከቅድስት እናቱ ጋር የተጋባችውን ቃል ኪዳኗን፡ በክህደት፥ በዓመፅና በአምልኮ አመንዝራነት በማፍረስ፡ በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመን፡ በኅቡዕ፥ በምሥጢርና በረቂቅ የሰዎች ፈሊጥ፥ ከዚያ ቀጥሎና ከደርግ ጊዜ ጀምሮ እስከዛሬም፡ በገሃድና በአደባባይ፥ በይፋና በአዋጅ፡ ራሷን፡ ከኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አካልነቷ ለይታ፥ በመጨረሻ፡ "እግዚአብሔር የለም!" ካለና ከሚል፡ ፀረ ክርስቶስ ከኾነ፥ የሰዎች መንግሥት ጋር አባሪና ተባባሪ፥ ተገዢና አገልጋይ ኾና፡ በዚህ አቋሟ፡ ህልውናዋን የቀጠለችው ናት።

ታውቃላችሁ? እናንተን የመሰላችሁት እኮ ናችሁ፡ እናንተን ወልዳና አጥብታ፥ አንከባክባና አሳድጋም፥ ባገር ውስጥ ብቻ ሳይኾን፡ ወደባሕር ማዶ አህጉር ጭምር ልካ አስተምራ፡ ለቍም ነገርና ለወግ ለማዕርግ ያበቃቻችሁን፡ ይህችኑ ቤተ ክርስቲያናችሁን እኮ ነው፡ እናንተ፡ "የለም! አንቺን አናገለግልም! አንረዳም! አንንካባከብም! አንጦርም!" ብላችሁ፡ ዕርቃኗን ጥላችኋትና ለጨካኝ የዱር ዐውሬ አሳልፈችሁ ሰጥታችኋት፡ የኼዳችሁት!

እንዲህ አድርጋችኋት ስትኼዱም፡ በችግር ተዳክማና ተንጋልላ ከወደቀችበት፡ እጆቿን ወደእናንተ ዘርግታ፥ በደበዘዙና ዕንባን ባቀረሩ ዓይኖቿ እያየቻችሁ፡ "ኧረ ልጆቼ! እባካችሁ ትታችሁኝ አትኺዱ! አስጥሉኝ!" እያለች ስትማፀናችሁ፡ ዞር ብላችሁ እንኳ፡ ሳትሰናበቷት፡ በጭካኔ በደነደነ ልባችሁ፡ ጥላችኋትና ትታችኋት ሸሻችሁ። ከዚያም፡ ያለኀፍረትና ያለይሉኝታ፡ "ዓይናችሁን፡ በጨው ታጥባችሁ"፡ ወደእግዚአብሔር አልባው ሰይጣናዊ ርእዮተ ዓለምና ወደአገዛዙ ጎራ፡ ሰተት ብላችሁ ገብታችሁ፡ ደርግን፡ በባርነት ስታገለግሉትና፡ በዚችው "እናት ቤተ ክህነታችሁ" ላይ ሳይቀር እየተሿሿማችሁ፥ ስትሣለቁባትና ስታቆስሏት ኖራችሁ።

ይህን ኹሉ ግፍ፡ ያኔም፣ ዛሬም፡ እየፈጸማችሁባት ያላችሁት እኮ፡ እናንተ ናችሁ!!! እኔ አይደለሁም።

፲፫ኛ፡ When I read this letter all my memory went back to that unique event where I saw you at that office. It is surprising to me. Let me draw back your memory to that date if you have a left over healthy memory .

You were fresh out of prison, hungry, delusional, bitter and pleading the great man Like-Likawent Aleka Ayalew Tamiru to give you the green light to get your books printed. Like-Likawent Aleka Ayalew decline to your request was like a death sentence to you. I remember how much you were frustrated and helpless in front of Aleka. At that time I was in hurry to go back to Europe in the same night and I didn't got time to discuss the matter concerning you and your book with Like- Likawent Aleka Ayalew. ላላችሁት፡-

ምናልባትም፡ ያን፡ የደርግ እሥር ቤት ያፈራውን፡ "አዳም እና ሔዋን፡ በኢትዮጵያ!" የሚለውን መጽሓፌን፡ ለቤተ ክህነቱ የሊቃውንት ጉባኤ ለማስረከብ፡ በዚያ በተገኘሁ ጊዜ፡ "እኔም በዚያ ነበርሁ!" ያሉትና ከእናንተ አንዱ የኾኑት፡ እርስዎ፡ ቀሪን ገረመው በላቸው፡ ከእነዚሁ የደርግ ተሿሚዎች መካከል አንዱ የቤተ ክህነት ባለሥልጣን ሳይኾኑ የሚቀሩ አልመሰለኝም።

ምክንያቱም፡ እኔ፡ እዚያ፡ በጉባኤው ላይ በተገኘሁ ጊዜ፡ እርስዎስ፡ ምን ሊፈጥሩ፡ እዚያ ዐብረውኝ እንዲገኙ ተደረገ? *"በዚያኑ ዕለት ማታም፡ ወደአውሮጳ ለመኼድ ተቻኩዬ ነበርና፡ ስለመጽሓፉ፡ ከሊቃውንቱ ጉባኤ ሰብሳቢ፡ ከአለቃ አያሌው ታምሩ ጋር በጽሙና ለመነጋገር በቂ ጊዜ አልነበረኝም ነበር!"* ማለትዎ፡ አንዱ፡ የደርግ ተሿሚ መኾንዎን የሚያመለክት ፍንጭ ነው።

አለዚያ፡ በቤተ ክህነቱ ውስጥ፡ የደርግ ባለሥልጣን ባይኾኑ ኖሮ፡ "ምንድር ነኝ!" ብለው ነው፡ ስለእኔ መጽሓፍ፡ ከሊቃውንቱ ጉባኤ ሊቀ መንበር ጋር የሚነጋገሩት? በሊቃውንቱ ጉባኤ ዘንድ፡ የመጽሓፌ የመጨረሻ ዕድል ፈንታ፡ እንደዚያ ሊኾን የበቃው፡ እርስዎ፡ ከአውሮጳ የደርግ ተልእኮዎ ከተመለሱ በኋላ፡ ተነጋግራችሁበት የተወሰነ ለመኾኑ፡ ይህ አገላለጽዎ፡ ሌላው ጠቋሚ ማስረጃ ይኾናል። በዚያን፡ በደርግ የጭቆና ዘመን፡ ወደውጭ አገር እንደልብ የመመላለሱ ፈቃድና ችሎታ የነበረው፡ ለደርግ ባለሥልጣኖች ብቻ ስለነበረ፡ በዚህ ረገድ የገለጹት ኹኔታ፡ እርስዎ፡ የቤተ ክህነት ሰው ኾነው፡ የደርግ ተሿሚነትዎን የሚያረጋግጥ እውነታ ነው።

እኔ፡ ከደርግ እሥር ተፈትቼ፡ በዚያ መጽሓፍ ምክንያት፡ በቤተ ክህነት የሊቃውንት ጉባኤ ዘንድ በተገኘሁ ጊዜ፡ የነበርሁበትን የሰውነት ገጽታ፡ አንኳስሳችሁና አጕሏቍላችሁ ለማሳየት ሞክራችኋል። ይህን ማድረጋችሁ ለምን እንደኾነ ባይገባኝም፡ የኾነውንና የነበረውን እውነተኛ ኹኔታ፡ በእኔ በኩል መግለጽ የሚገባ ይመስለኛል።

በመጀመሪያ ነገር፡ ያ እሥር ቤት፡ ለእኔ፡ በሕፃንነት ዕድሜዬ የጀመርሁትንና እስከዚያ ያደረስሁትን፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ተልእኮዬን፡ በነፍስ፥ በሥጋና በመንፈስ፡ ለራሴም ኾነ ለሌሎች፡ እጅግ በተሳካና ፍሬያማ በኾነ ይዘት፡ ያለአንዳች ችግር ያካኼድሁበት ምቹ መድረክ እንጂ፡ ለእናንተ እንደመሰላችሁ፡ በጕሥቍልና ቆይቼ፡ በጕሥቍልና የወጣሁበት አልነበረም፤ ያ ጊዜ፡ የኹለንተና ጤንነቴ፥ እስከዛሬ የቀጠለው፡ የማስታወስ ኃይሌ ጭምር፡ የበለጠ ተሟልቶ የተገኘበት ነበር።

አዎን! ያ ጊዜ፡ እናንተና አለቃችሁ፡ መሰሎቻችሁም፥ መላዋ፡ የዛሬዪቱ ቤተ ክህነት ጭምር፡ ከደርግ ጋር በቃል ኪዳንና በአደባባይ የፈጸማችሁት ጊዜያዊ ጋብቻ፡ ያስገኘላችሁን የጫጉላ ሰይጣናዊ ዓለም የምትቀጩበት፡ “ያሥረሽ ምቺው!” ዘመን ሥላቃችሁ ነበር።

እኔ ግን፡ የደርግ የሞት ፍርድ የሚያስከትለውን የፍርድ አስፈጻሚዎችን ቅጽበታዊ ጥሪ ለመቀበል፡ ከሰባት ዓመታት በላይ ለኾነ ዘመን፡ በዝግጁነት በመጠባበቅ፡ በእሥር ቤቱ ውስጥ የነበሩትን እሥረኞች ወገኖቼን እንዳገለግል፡ ከእውነተኛዋና ከጥንታዊቷ የኢትዮጵያ ቤተ ክህነት የተሰጠኝን የተልእኮ ግዳጅ ያከናወንሁበት ነበር። ይህን እውነታ፡ ለእሥር ቤቱ ኅብረተሰብ አበረክተው ከነበረው ልዩ ልዩ ክህነታዊና ማኅበራዊ አገልግሎት ጋር፡ የ“አዳም እና ሔዋን፡ በኢትዮጵያ!” ድርሰቴ፡ በቂ ማስረጃዎች ናቸው።

በኹለተኛ ነገር፡ እኔ፡ እዚያ የቤተ ክህነት ጉባኤ ዘንድ የተገኘሁት፡ ሰብሳቢውን፡ አለቃ አያሌውንና የጉባኤውን አባሎች፡ ለመጎብኘት፥ ወይም፡ ስለመጽሐፌ፡ ደጅ ለመጥናት አልነበረም፤ እዚያ የተገኘሁበት ምክንያት፡ ባጭሩ፡ እንዲህ ነበር፡-

በእግዚአብሔር ቸርነት፡ ከደርግ እሥር ቤት ወጥቼ፡ እቤቴ ተቀምጬ ሳለሁ፡ ስማቸውን እላይ የጠቀስሁት፡ የቤተ ክህነቱ እጩጌ፡ በደግ አሳቢነታቸው፡ ስማቸውን ከላይ የጠቀስሁትን፡ የቤተ ክህነቱን ጠቅላይ ሥራ አስኪያኄጅ፡ እመኖሪያ ቤቴ ድረስ ልከው፡ በቤተ ክህነቱ አስተዳደር ውስጥ በምክርም ቢኾን ገብቼ እንዳገለግል በመጋበዝ፡ “ምን ልናደርግልህ ትወድዳለህ?” ብለው አስጠየቁኝ። እኔም፡ “በእሥር ሳለሁ ያዘጋጀሁት መጽሐፍ አለኝ፤ እርሱ ታትሞ፡ ለሕዝብ ቢሠራጭ፡ ቤተ ክህነትም፥ ትውልዱም፡ ዛሬ ለሚገኙበት ኹኔታ ይረዳል፤ ፈቃድዎ ቢኾን፡ ይህን እንዲያደርጉልኝ ነው፡ የእኔ ፍላጎት!” የሚል መልስ ላክሁባቸው።

እርሳቸውም፡ ይኸው፡ “አዳም እና ሔዋን፡ በኢትዮጵያ!” የሚለው መጽሐፌ መጥቶ፡ በሊቃውንቱ ጉባኤ እንዲታይ ስላዘዙና መጽሐፉን፡ ከጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ ጋር እንዳስረክብ ስለጋበዙኝ፡ እዚያ ተገኘሁ። እዚያ፡ በተገኘሁበትም ጊዜ፡ የሊቃውንቱ ጉባኤ ሰብሳቢና አባሎቹ፡ የልቦናቸውን የሚያውቀው እግዚአብሔር ኾኖ፡ በእንዴት ያለ አክብሮትና ፍቅር ተቀብለውኝ እንደነበረ፥ አለቃ አያሌውም፡ የእኔን፡ ያለፈና የእሥር ቤት ሙያ ጭምር በማድነቅ፡ የተለየ ንግግር ማድረጋቸውን፡ ቀሪን ገረመው፡ በእርግጥ፡ እዚያ ተገኝተው ከኾነ፡ ይህን እውነታ ሳያወሱ ማለፉቸው፥ እንዲያውም፡ አጣመውና ወደሐሰት ለውጠው ማቅረባቸው ያስተዛዝባል።

የእኔ በዚያ የመገኘቴ ኹኔታ፡ እውነተኛና ትክክለኛ ገጽታው፡ ይህን የመሰለ ሲኾን፡ እናንተ ግን፡ በዚያ የተሳሳተ መልክ ማቅረባችሁ፡ ለምን እንደኾነ አልገባኝም፤ ምናልባት፡ የአለቃ አያሌው ታምሩን፡ የሌለ ጥቃት ለመወጣት የሚረዳችሁ መስሏችሁ፡ የእኔን ስሜት ለመጉዳት ከኾነ፡ ገና አላዋቂዎች ናችሁ ማለት ነው።

ይኸውም፡ ይህና ሌሎቹ፡ በየእ-ጦማሮቻችሁ የሠነዘራችኋቸው፡ የበቀል ሙከራዎቻችሁ፡ እናንተን፡ ለመለኮታዊው ፍዳ የሚዳርጉ ሲኾኑ፡ ለእኔ ግን፡ ለተልእኮዬ መጠናከር፡ የቱን ያህል ጠቀሜታነት እንዳላቸው አለመረዳታችሁ ነው።

ይህ አላዋቂነታችሁ፡ ይህን ያህል የደደረ ኾኖ፡ እስከዚህ ሊያስጽፋችሁ የደረሰው እኮ፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት መኖር፡ ምን እንደኾነ ለመረዳት፡ ፈጽሞ የተሳናችሁና የጨለመባችሁ ድኩማን በመኾናችሁ ነውና፡ እስኪ፡ ዓቅም አግኝታችሁ፡ ሊገባችሁ የሚችል ከኾነ፡ እየራሳችሁን በመጠየቅ፡ እንድትረዱት ላድርግ!

ለመኾኑ ስታስቡት፡ የቅዱሱ ኪዳን አካል የኾኑትን፡ ሰባቱን ሕያዋን መለኮታውያን ኪዳናት፡ በሃይማኖትና በምግባር፡ ሕይወት አድርጎ የሚኖር ኢትዮጵያዊው ሰውነት፡ በዚህ፡ በግዙፉ ዓለም፡ ያለው፡ *ሥጋዊውና* ነፍሳዊው፥ መንፈሳዊውም ህልውናው፡ "ምን ዓይነት ይኾናል!" ብላችሁ ነው፡ የምታስቡት? ይህ ኢትዮጵያዊው ሰውነት፡ በመጀመሪያው የትንሣኤ ሕይወት፡ ዕድል ፋንታ ያለው ኾኖ፡ ለብፅዕና ህልውና የታደለ፥ የሚያጣውና የሚፈልገው፡ አንዳችም ነገር የሌለ፥ ኹሉ፡ የእርሱ ኾኖ የሚኖር አይደለምን? ይህን እውነታ፡ ከምትገኙበት ሃይማኖታችሁ እንኳ ማወቅ አልተቻላችሁምን?

በደርግ የጭካኔ ፍርድ የተወሰነብኝን ሞት ሳልፈራ፡ ተልእኮዬን፡ እዚያው፡ የደርግ እሥር ቤት ውስጥ፡ ያለአንዳች ችግር፡ በግልጽ ለማካኼድና አኹን ደግሞ እናንተ፡ *"በአለቃ አያሌው ታምሩ ተፈርዶብህ ነበር!" ብላችሁ ያረዳችሁኝን የሞት ፍርድ፡* ይኸው፡ ዛሬ፡ እናንተም እንደምታረጋግጡት፡ ሳልፈራ፡ ያንኑ ተልእኮዬን በመቀጠል፡ አያሌ መጻሕፍትን ለማበርከት የቻልሁት፡ ከቶ፡ በምን ምክንያት ይመስላችኋል? በዚሁ፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነቴ እኮ ነው? ሌላ ምንም የተደበቀ ምሥጢራዊ ዘዴ የለም።

፲፬ኛ፡ You were fresh out of prison, hungry, delusional, bitter. Lately I heard that you left the country and still lives in confusion and bitterness in Maryland፡ the land of your freedom and madness where you are living with your fantasy. **ላላችሁት፡-**

እናንተ ግን፡ ፈጽማችሁ ሥጋውያንና ምድራውያን፥ ዓለማውያንና የመናፍስት ወገኖች ስለኾናችሁ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነትንና ህልውናውን፡ ፈጽሞ ልትረረዱት ከቶ አልቻላችሁም፤ አይቻላችሁምም፤ እርሱም ሊገባችሁ አይችልም።

ታዲያ! ለዚህ አይደለም ወይ፡ እኔ፡ ከደርግ እሥር ቤት በወጣሁበት ጊዜ፥ ደግሞም፡ ያንኑ የእሥር ቤት ተልእኮዬን፡ በውጪዎቹ አህጉራት ለሚገኙት ወገኖቼ ለመቀጠል፡ በፈቃዴ፡ ከአገሬ ወጥቼ፡ በስደቱ ዓለም በምዘዋወርበት ጊዜ፡ ከዚህ በላይ የተጠቀሰውን ሥዕላዊ ባሕርይና ገጽታ ያላበሳችሁኝ?

እናንተ፡ ማንኛውንም ሰብአዊ ፍጡር፡ የምትመለከቱትና የምትገምቱት፥ የምታከብሩትና የምትንቁት፥ የምትሽቆጠቆጡለትና የምታዋርዱት፥ የምትፈሩትና የምትደፍሩት፡ በሥጋዊ ውበቱና አለባበሱ፥ ሥልጣኑና ብልጽግናው፥ ክብርና ማዕርጉ፥ ትምህርቱና ሙያው ብቻ ነው። ታዲያ! እንዲህ ስለኾነ አይደለም ወይ፡ እናንተ በምትጓጉለትና ዛሬም፡ በምትጋደሉለት ኹኔታ በነበርሁ ጊዜ፡ ለእኔ የነበራችሁን ያን አስተያየት፡ ዛሬ ለውጣችሁ፡ በእኔ ላይ፡ ይህን የመሰለውን፡ ተራ የስንፍና ቃል የሠነዘራችሁት? ይህም አያስገርምም።

ለመኾኑ፡ እናንተ፡ የማን ልጆች ናችሁና ነው፡ ከእናንተ፡ ሌላ ደግ ነገር የሚጠበቀው? **"እናንተ የእፉኝት ልጆች! ከሚመጣው ቍጣ እንድትሸሹ ማን አመለከታችሁ? እንግዴህ፡ ለንስሓ የሚገባ ፍሬን አድርጉ!"** ብሎ፡ አዋጅ ነጋሪው ያጋለጣቸው፡ የእነዚያ ግብዞችና የክርስቶስ ባላጋራዎች ወገኖች አይደላችሁምን? (ማቴ. ፫፥ ፯።)

እኔስ፡ ለቸሩ እግዚአብሔርና ለቅድስት እናቱ፡ የማያቋርጠው ምስጋናዬ ይድረሳቸውና፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነቱ፡ እናንተ ልታስቡትና ልታዩት፥ ልትኾኑትም በማይቻላችሁ፡ በሥጋዬና በነፍሴ፥ በመንፈሴም፡ ፍጹም በኾነው ነጻነትና የትንሣኤ ሕይወት ከብሬና ተሸልሜ፡ በመላው ዓለም በሰፈነችው፡ በኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር መንግሥትና በመላው ፍጥረተ ዓለምነቷ፡ አህጉራትን ባቀፈችው፡ በኢትዮጵያዋ ድንግል ማርያም፡ ምድር ኹሉ፡ አገሬ ኾኖ፡ እነሆ፡ በገነቲቱ ብሔረ ሙላዴና ወገኖቼ በሚገኙባት፡ በአመሪካ ሀገረ ማርያም እየተመላለስኩ፥ ወደሌሎች አገሮችም፡ እንደልቤ እየተዘዋወርሁ፡ ለወገኖቼና ለአገሬ፥ ለፍጥረተ ዓለሙም ደኅንነት በመጸለይ፥ እኒህም ኹሉ፡ በንስሓ እንዲመለሱ በማሳሰብ፡ ከነቤተሰቤ፡ በቅዱሱ ኪዳን ሰላምና ደስታ፥ ጤንነትና ዕረፍት እኖራለሁ።

እኛ የቅዱስ ኪዳኗ ኢትዮጵያ ልጆች፡ ስለምንኖረው የህልውና ዓይነት ለማወቅ፡ በኀዋ ሰሌዳችን፡ ዋና ገጽ ላይ የሠፈረውን <u>**"ምሥራች!"**</u> የሚለውን መልእክት፥ እንዲሁም፡ <u>**"ምሥራች! ከእናት ኢትዮጵያ፤ ለኢትዮጵያ ልጆች፤ ስለኢትዮጵያዊነት።"**</u> የሚለውንም፡ አዲሱን መጽሓፌን (እንደሌሎቹ መጻሕፍቴ፡ crap ልትሉት የምትችሉትን) ለመመልከት አልታደላችሁም እንጂ፡ እነዚህን፡ አንብባችኋቸው፥ ወይም፡ የምታነብቧቸው ቢኾን ኖሮ፡ እኔና እኔን የመሰሉት ኹሉ፡ እንዴት ባለው እግዚአብሔራዊ ሕይወት ውስጥ እንደምንገኝ ተገንዝባችሁ፡ የቅንነቱ ዝንባሌ ካላችሁ፡ መንፈሳውዊ ቅንዓት ሊያድርባችሁ ችሎ፡ እየራሳችሁን፡ ለዚያ፡ የእግዚአብሔር ጸጋ ለማብቃት በተነሣሣችሁ ነበር።

ተጠናውቷችሁ የሚመራችሁ፡ ምትሓታዊው የክፋት ኃይል፡ ለእናንተ፡ አግዝፎና አጉልቶ የሚያሳያችሁ፡ የእኔን፡ ተራ ሽማ አጣፍቶ፡ በባዶ እግር መኼድን፡ እንደጕሥቍልናና እንደእብደት እንጂ፡ ከላይ የገለጽሁትን እውነታ አይደለም። ይህ ዓይነቱ አስተያየታችሁ ደግሞ፡ እንግዳ ነገር ኾኖ፡ ከቶ፡ ሊያስደንቅ አይችልም፤ መምህራችን፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ራሱ ፈጽሞት፡ ተከታዮቹንም፡ "ለእግራችሁም፡ ጫማ አይኑራችሁ!" ያለውን የመሰለው ቃሉ፡ ለዲያብሎስ ጭፍሮች፡ ነደ እሳት ኾኖ ስለሚያቃጥላቸው፡ ይጠሉታልና።

ይኼው የክፋት ኃይል፡ ለእናንተም የሚያሳያችሁ፡ ከደርግ እሥር ቤት ጀምሮ፡ እስካኹን፡ እንዲህ ኾኜ መኖርን ለምን እንደመረጥሁ፡ ማወቁ ቀርቶባችሁ፡ ጠይቃችሁ እንድትረዱ እንኳ የሚያደርጋችሁን ፈለግ አይደለም። የያዛችሁ አባዜ የሚያመለክታችሁና የሚያሳያችሁ፡ በጎውን የእግዚአብሔሩን እውነት ሳይኾን፡ ክፉውን፡ የዲያብሎስን ሓሰት ብቻ ነው።

እንዲያ ባይኾንማ ኖሮ፡ በመንፈስ ቅዱስ ተነሣሥታችሁ፡ እነዚያን፡ እናንተ፡ crap ለሚለው፡ ለባዕዳኑ ጸያፍና አስነዋሪ ስያሜ የዳረጋችኋቸውን መጻሕፍቴን በማንበብ፡ ይህን ኹሉ እውነታ፡ በቀላሉ፡ ለመገንዘብ በቻላችሁ፥ ባላዋቂነትም፡ በእኔ ላይ፡ ይህን የመሰለውን በቀል፡ በጽሑፍ ቃላት ለመወጣት ባልሞከራችሁም ነበር። ሃይማኖትና ምግባር የጎደላችሁ እናንተ፡ ያ ዓይነቱ፡ የምትመኙትና የምትፈልጉት፥ የምታከብሩትና የምታደንቁት፡ የወርቅ ልብስና የወርቅ ጫማ፡ እንዴት አድርጎ፡ በእኔ ላይ፡ ለእናንተ ሊታያችሁ ከቶ ይቻላል!? አይቻልም። በአማናዊው ማንነታችን፡ እርስ በርሳችን፡ በግልጽ ለመተያየትና በግዘፍ ለመተዋወቅ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ሃይማኖትና ምግባር ያስፈልጋል።

፲፰ኛ፡ Off course I read the book your wrote and rejected by Lique Aleka Ayalew Tamiru ላላችሁት፡-

ሊያሳፍሩዋችሁ ከሚገቡ ድክመቶቻችሁ መካከል አንዱ፡ ይኸው አላዋቂነታችሁ ሲኾን፡ ከእርሱም ይልቅ የሚብሰው፡ ነገሮችን ሳታጣሩ፡ በሓሜትና በስሜት፥ በወሬና በአሉባልታ ብቻ እየተመራችሁ፡ ያንን የምታስተጋቡ መኾናችሁ ነው። ይህንንም የሚረጋገጠው፡ ከላይ የሠፈረው የቀሪን ገረመው ጽሑፍ ነው።

አለቃ አያሌው ታምሩ፡ "አልቀበልም!" ብለው ተቃውመው የመለሱት መጽሓፍና ቀሪን ገረመው፡ "አኹን፡ በቅርቡ አነበብሁት!" ያሉት መጽሓፍ የተለያየ መኾኑን አለማስተዋላችሁ፡ በእርግጥ ያሳፍራል። የቤተ ክህነቱ ሊቃውንት ጉባኤ ሰብሳቢ አለቃ አያሌው፡ ተቃውመው የመለሱት፡ ያ መጽሓፍማ፡ "ኢትዮጵያዊው፡ በእውነት ፍለጋ! ኢትዮጵያዊው፡ በእውቀት ፍለጋ! ኢትዮጵያዊው፡ በጦቢያ ፍለጋ!" የሚሉትን ሦስት ጥራዞችን የያዘው፡ "አዳም እና ሔዋን፡ በኢትዮጵያ!" የሚለው መጽሓፌ ነው፤ እርሱም፡ ገና አልታተመም።

*ቀሪን ገረመው ያነበቡት መጽሓፍ፡ ከእርሱ ወዲህ፡ ማለትም፡ ከደርግ እሥር ቤት ከወጣሁ በኋላ፡ በኢትዮጵያኛና በእንግሊዝኛ አዘጋጅቼ፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት ከታተሙትና ለሕዝብ ምንባብ ከተሠራጩት መጻሕፍቴ መካከል አንዱ መኾን ይኖርበታል።*

***፲፮ኛ፡*** I can understand that you never dare to write a single line *[እንኳንስ፡ ፳፩ ገጽ ያለውን ረዥም ደብዳቤ ልትጽፍ ይቅርና፡]* if Lique Aleka Ayalew was alive. You never did that during his life time. Because the satan who lived in you knows very well more than you how much that great person was holy and how his utter commitment as a greatest scholar was only to the truth and the purity of the teachings our religion . Sorry! For you!! **ላላችሁት፡-**

**በእናንተ ላይ፡** Shame on you! **ሊያስሰኝ የሚያስችለው ሌላው፡ አሳፋሪ ኹኔታችሁ ደግሞ፡ይህ፡ ከላይ ተጠቅሶ የሚነበበው ጽሑፋችሁ ነው። ምክንያቱ፡ እንደሚከተለው ነው፡-**

*ቀሪን ገረመው፡ "አነበብሁት!" ያሉት መጽሐፌ፡ የትኛው እንደኾነ፡ ለይቼ አላወቅሁትም እንጂ፡ ባውቀው ኖሮ፡ መልካም በኾነ ነበር። ይኹን እንጂ፡ ያነበቡት መጽሓፍ የትኛውም ይኹን አይኹን፡ የነገሩን ድምዳሜ አይለውጠውም።*

*ምናልባት፡ በእርግጥ አንብበው ከኾነ ግን፡ ያ መጽሓፍ፡ "ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ!" የሚለው አለመኾኑ፡ ይታወቃል። ምክንያቱም፡ ይህ መጽሓፍ፡ አለቃ አያሌው ታምሩ፡በሕይወተ ሥጋ እያሉ፡ በ፲፱፻፺፫ ዓ. ም. ታትሞ፡ ለሕዝብ የተሠራጨ ሲኾን፡ በዚሁ መጽሓፌ፡ በገጽ ፬፻፳-፬፻፳፺ ላይ፡ በቀጥታ ስማቸውን በመጥቀስ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ሃይማኖታችንንና ምግባራችንን፥ ሥርዓታችንንም በሚመለከት ስለፈጸሟቸው በደሎች ዘርዝሬ በመግለጽ የጻፍሁት ስላለ ነው። እርሳቸውስ፡ ያን፡ ለዚያ፡ ወደእርሳቸው ለላክሁት ደብዳቤዬ መነሻ የኾነኝን ቃል፡ በመጽሓፍ ሊጽፉ የቻሉት፡ ይህንኑ፡ እርሳቸውን ጭምር የሚነካውን መጽሓፌን ስላገኙ አይደለምን?*

*የሚያሳዝነውና እናንተንም፡ ማሳፈር ብቻ ሳይኾን፡ ብርቱ ግምት ላይ የሚጥላችሁ፡ ከላይ፡ በዚህ ጽሑፌ መግቢያ እንደተወሳው፡ መጻሕፍቴን ቀርቶ፡ ለአለቃ አያሌው የተጻፈውንና ይኸው አኹን፡ እናንተ ተቆርቁራችሁ መልስ የሰጣችሁበትን ደብዳቤ እንኳ፡ በማስተዋል አለመመልከታችሁ ነው። ያን ደብዳቤ፡ በማስተዋል ተመልክታችሁት ቢኾን ኖሮ፡ ይህን የመሰለውን የተሳሳተ ትችት፡ በእናንተ በኩል መስጠት ባላስፈለጋችሁ ነበር።*

እንደእናንተ አስተሳሰብና አጻጻፍ፡ “በቀወሰ አእምሮና በጕሥቍልና አካል፥ በመራራም ኑሮ የምናውዘው እኔ እብዱ”፡ በደርግ ውሳኔ፡ የሞት ፍርድ ተላልፎብኝ፡ ጥሪዬን፡ ከሰባት ዓመታት በላይ ለኾነ ዘመን፡ በየአፍታዋ እጠባበቅ በነበርሁበት እሥር ቤት፡ እነዚህን፡ አለቃ አያሌው ታምሩና የደርግ ተጧሚዎች የነበሩት የቤተ ክህነት ሰዎች ተቃውመው የመለሷቸውን ሦስት መጻሕፍት፥ ኋላም፡ በስደቱ ዓለም፡ እናንተ አኹን፡ crap የሚለውን አስጸያፊ የርኵሰት ባዕድ ስያሜን የሰጣችኋቸውን ሰባት ያህል መጻሕፍትን፡ አዘጋጅቼ፡ ለሕዝብ ምንባብ ለማቅረብ ከቻልሁ፡ እንደእናንተው አስተሳሰብና አጻጻፍ፡ “በተስተካከለ ጤናማ አእምሮና በተደላደለ የምቾት ሕይወት የምትኖሩት፡ እናንተ ብልሆቹ ምሁራን” ደግሞ፡ ምን ዓይነቱን የህልውና ፍሬ እንዳበረከታችሁ፡ ለእኔ ቀርቶ፡ እስኪ፡ ለራሳችሁ ወገኖች ተናገሩ!? እኔም፡ እስኪ ልስማው!?

እንግዴህ፡ በእየእ-ጦማሮቻችሁ ለሠነዘራችኋቸው አስተሳሰቦቻችሁ፡ የምሰጣችሁን ማብራሪያ፡ በዚህ እፈጽማለሁ። በእነርሱ አማካይነት ላስተላለፋችሁልኝ የተቃውሞ መልእክት፡ ይህን ያህል ካተትሁ፡ ይህንኑ ጽሑፌን፡ እንደሚከተለው አጠቃልለዋለሁ።

እስካኹን እንደተከታተላችሁት፡ በተቻለኝ መጠን፡ በቅዱሱ ኪዳን ጨዋነት ያዘጋጀሁትን፡ ይህን፡ ከላይ ያሠፈርሁትን መልስ ያቀረብሁት፡ እናንተ፡ በምግባር ባትፈጽሟቸውም እንኳ፡ ክብርን በምትሰጧቸው፡ በ“ሊቃውንት መጻሕፍት ጥቅሶች” በማጀብ አለመኾኑን አስተውላችሁት ይኾናል፤ ነገር ግን፡ ባለፈው ደብዳቤዬና በሌሎቹ ጽሑፎቼ ኹሉ እንዳደረግሁት፥ አኹንና ወደፊት፥ ምንጊዜም እንደማደርገው፥ የእግዚአብሔር ልኡካንና የመንፈስ ቅዱስ ልሳናት የኾኑት፡ ነቢያትና ሐዋርያት፥ ራሱ፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም የተናገሩዋቸውን ቃላት ብቻ በመጠቃቀስ መኾኑን፡ እንደተገነዘባችሁት አምናለሁ።

ይህን በማድረጌ፡ “ይህማ፡ ተራ ማሃይምና ያልተማረ ጨዋ የሚጠቀምበት፥ የProtestantቶቹ ይትበሃል ነው!” እያላችሁ፡ ጥቅሶቹንም፥ እኔንም እንደምታቃልሉ፡ ከየጽሑፋችሁ ቢታወቅም፥ ደግሞም፡ ከእግዚአብሔር ይልቅ፡ “ሊቃውንት ናቸው!” የሚባሉትን ከምታመልኩና ይኸው ባህል፡ በኅብረተሰቡ ዘንድ እንደሚያስከብራችሁ ተረድታችሁ፡ እየራሳችሁንም፡ “ሊቃውንት ነን!” እያላችሁ ከምታመጻድቁ፡ ከእናንተ፡ ከዚህ ሌላ፡ የሚጠበቅ ነገር ባይኖርም፡ ይኸው የእግዚአብሔር ቃል፡ በእናንተ ላይ ያደረገውን ኃይሉን፡ አኹንም ላመልክታችሁ!

ለዚያ ተልእኮ በታዘዘው ቅዱስ መልአክ እጅ፡ ለአለቃ አያሌው ታምሩ የላክሁትን ደብዳቤ፡ እናንተ ስታነብቡት፡ ሥጋዊውና ነፍሳዊው ኹለንተናችሁ፡ በእግዚአብሔር የእውነት ሠይፍ ስለተመታ፡ የደረሰባችሁን ኹኔታ፡ በየእ-ጦማሮቻችሁ የተጠቀማችሁባቸው ጥፉ ቃላትና የጽሑፎቻችሁ ተርብነት፡ ለማንም ተመልካች፡ በግልጽ ያሳያሉ።

ያም ኹኔታ፡ ኹለንተና ሰውነታችሁ፡ በጦር ተወግቶ እንደሚጮህና እንደሚወራጭ ጨካኝ የዱር ዐውሬ፡ መቁሰሉና መሠቃየቱ፥ በባዕዳን ኃይላት የተበከለው መንፈሳችሁም፡ ከመለኮታዊው ነደ እሳት የተነሣ፡ በቁጣና በብስጭት ተቃጥሎ መደፍረሱ የተጋለጠበት ነው።

ይህ የኾነው፡ እንዲያው ያለምክንያት አይደለም፤ ብታምኑበትም፥ ባታምኑበትም፡ ምክንያቱ፡ ያው፡ እናንተ የምታቃልሉትና የምትጠሉት፥ ቀንደኛው የክፋት አበጋዝም፡ ከሩቅ፡ የሚሸሸው፥ ደፍሮ፡ "ልቅረብ!" ቢልም እንኳ፡ በወላፈኑ የሚያኮማትረው፡ <u>የእግዚአብሔር ቃል፡</u> የሰውነታችሁን ኹለንተና ስላነደደውና ስላቃጠለው ነው። አኹንም፡ እኔ፡ ያንኑ የእግዚአብሔርን ቃል፡ እንዲህ እያልሁ ስጠቅስባችሁና እናንተም ስታነብቡት፡ በውስጣችሁ በሚሰማችሁና በውጫችሁ በሚደርስባችሁ፡ ለየራሳችሁ ትገነዘቡታላችሁ!

**"ቃለ እግዚአብሔር፡ ይቀጠቅጥ አርዘ! ወይቀጠቅጦ እግዚአብሔር፡ለአርዘ ሊባኖስ። ...ቃለ እግዚአብሔር፡ ይመትር ነደ እሳት! ቃለ እግዚአብሔር፡ ያድለቀልቆ ለገዳም! ወያድለቀልቆ እግዚአብሔር፡ ለሓቅለ ቃዴስ!"**

**ማለትም፡ "የእግዚአብሔር ቃል፡ ዝግባን ይሰብራል! እግዚአብሔር፡ የሊባኖስን ዝግባ ይቀጠቅጠዋል። ...የእግዚአብሔር ቃል፡ የእሳቱን ነበልባል ይመትራል! የእግዚአብሔር ቃል፡ ምድረ በዳውን ያናውጣል! እግዚአብሔር፡ የቃዴስን በረሃ ያናውጠዋል!"** (መዝ. ፳፰፥ ፭-፰።)

ያን ደብዳቤ፡ ገና፡ በመጀመሪያው፡ ስታነብቡት፡ ያን የመሰለው ክፉ ስሜት፡ በእናንተ፡ በኹለንተናችሁ ውስጥ፡ ከቶ፡ ስለምን አደረባችሁ? እንዴትስ ሊያድርባችሁ ቻለ? ለምንስ እስከዚህ ፈንድቶና ግንፍሎ በጽሑፍ እስከመግለጥ አደረሳችሁ? የዚህን ምክንያት ለማወቅ፡ በመንፈስ ቅዱስ ብቻ ለሚመሩትና ለሚኖሩት፡ ለቅዱስ ኪዳኗ የኢትዮጵያ ልጆች፡ የሚሳናቸው ይመስላችኋልን? አይምሰላችሁ!

በየእ-ጦማሮቻችሁ አማካይነት በተከሠተው፡ በዚህ ግብራችሁ፡ እናንተ፡ እውነተኞች ኢትዮጵያውያን፥ እውነተኞች ክርስቲያኖች፥ እውነተኞች ዐምሓራዎች፥ ወይም፡ እውነተኞች የእግዚአብሔር አማኞች እንዳይደላችሁ፡ ለይቶ ለማወቅ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊ መኾንን ከቶ አይጠይቅም፤ ማንኛውም አስተዋይ ሰው፡ በቀላሉ ሊያውቀው የሚቻለው፡ ግዙፍ እውነታ ነውና።

እናንተ ግን፡ "እንዴት አይደለንም! ነን እንጂ!" ካላችሁ፥ ከኾናችሁም፡ ከዚህ ቀጥሎ ለሚቀርቡላችሁ ጥያቄዎች፡ መልስ መስጠት አለባችሁ! ይህም፡ "'ነን እንጂ!' ካላችሁ፡ ታዲያ! ደብዳቤው የተጻፈበት ዓቢይ ምክንያት፥ የያዘውም ዋና መልእክት፡ ፍሬ ነገሩና ቁም ነገሩ፡ ምን እንደኾነ አላወቃችሁትም ኖርዋልን? ካወቃችሁት፡ እስኪ ንገሩኝ! ምንድር ነው?

“እርሱማ፡ ፈጣሪያችንና አምላካችን፡ በእግዚአብሔር አብነቱ፥ በእግዚአብሔር ወልድነቱና በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስነቱ ባሕርይና አካል፡ ለፍጥረቱ ያደረገውን ታላቅና ዘለዓለማዊ የቸርነት ሥራ የሚቃረን ቃልን፡ አለቃ አያሌው ታምሩ፡ በመጽሐፍ ጽፈው በመገኘታቸውና በዚህ ታላቅ ኃጢአት፡ እጅ ከፍንጅ በመያዛቸው አይደለምን?

“‘አዎን!’ ካላችሁ፡ መልካም! ይህ መኾኑን ባወቃችሁ ጊዜ፥ ወይም፡ ከዚያ በኋላ፡ በውስጥና በውጭ ያለው ሰውነታችሁ፡ ስለእግዚአብሔር ባለው የቅንዓት እሳት፡ ታዲያ! ለምን፡ ሳይቀጣጠል ቀረ?

“እንዲያውም፡ በዚያ ደብዳቤዬ፡ በገሃድ የተገለጠው፡ ብቸኛውና ዋናው ጉዳይ ይኸው መኾኑን ካረጋገጣችሁ በኋላ፡ ያለ፥ የሌለ፡ የሥጋና የነፍስ፥ የመንፈስም ኃይሎቻችሁን፡ አቅንታችሁና አተኲራችሁ ልታሰቡና ልትመሰጡ ያስፈልጋችሁ የነበረው፡ ወደዚያ፡ ወደታላቁ፡ ወደእግዚአብሔራዊ ዓላማ ሊኾን ሲገባ፡ ያን ትታችሁ፥ ወይም፡ እርሱን ወደጎን አድርጋችሁ፡ አለቃ አያሌውንና እኔን ለሚመለከተው፡ ግለሰባዊ ጉዳይ፡ እንዴት፡ ቅድሚያውንና ብልጫውን፡ ልትሰጡ ወሰናችሁ? ይኸኛው፡ ግለሰባዊው፡ ያውም፡ ያን በመሰለ ክፉ ስሜት፡ ከዚያኛው ከእግዚአብሔራዊው ጋር ሲነጻጸር፡ እንደኢምንት እንኳ ተቆጥሮ፡ ሊወሳ የማይገባው ሲኾን?” የሚሉ ናቸው።

ለእነዚህ ጥያቄዎች የሰጣችሁት መልስ፡ ምን ዓይነት እንደኾነ፡ ከላይ የሠፈሩት እ-ጦማሮቻችሁ፡ ይኸው፡ አጋልጠውና አረጋግጠው ስለመሰከሩባችሁ፥ በዚሁ ግብራችሁ፡ “ከኢትዮጵያዊው ቀርቶ፡ ከሰው ወገን፡ ምን ዓይነት ፍጡሮች ናችሁ!” ከማለት በቀር፡ እንግዴህ ወዲህ፡ ከእናንተ የሚጠበቅ፡ ሌላ ምላሽ፡ ከቶ፡ አይኖርም።

አዎን! እናንተ፡ እያንዳንዳችሁ፡ እውነተኛ ኢትዮጵያዊ፥ ወይም፡ እውነተኛ ክርስቲያን፥ ወይም፡ እውነተኛ ዐምሓራ፥ ወይም፡ እውነተኛ የእግዚአብሔር አማኝ ብትኾኑ ኖሮማ፡ ልትቈረቈሩና ልትቆጩ፥ ልትቀኑና ልትመሰክሩም፥ ጥብቅና ልትቆሙም የሚገባችሁ፡ ለማን ነበረ? ከአለቃ አያሌው ታምሩ ይልቅ፡ ለእግዚአብሔር አልነበረምን? እናንተ፡ ለአለቃ አያሌው ታምሩ፡ ልጅም፥ ቤተሰብም፥ ቤተዘመድም፥ ወዳጅም፥ ተከታይም፥ ምንም ምን ኹኑ! ለመኾኑ፡ ከፈጠራችሁ ከእግዚአብሔርና ከእርሳቸው፡ የምታምኑትና የምትከተሉት፥ የምትወድዱትና የምታገለግሉት ማንን ነው? ማንንስ ሊኾን ይገባል? እናንተ፡ እውነተኛ ኢትዮጵያዊ፥ ወይም፡ እውነተኛ ክርስቲያን፥ ወይም፡ እውነተኛ ዐምሓራ፥ ወይም፡ እውነተኛ የእግዚአብሔር አማኝ ብትኾኑ ኖሮ፡ ልታምኑና ልትከተሉ፥ ልትወድዱና ልታገለግሉ የሚገባችሁ፡ አለቃ አያሌው ታምሩን ነው? ወይስ፡ እግዚአብሔርን? አለቃ አያሌው ታምሩን ሳይኾን፡ እግዚአብሔርን ሊኾን እንደሚገባ፡ የየራሳችሁ፡ እውነተኛ ሃይማኖታዊ ኅሊና ሳይቀር ያውቀዋል፤ ይፈርዳልም።

አላስተዋላችሁትም እንጂ፡ በዚያ በንቀትና በትዕቢት ባረካከሳችሁት ደብዳቤዬ ውስጥ ተጠቅሶ ያለው የእግዚአብሔርም መመሪያ ቃል አረጋግጦ የሚያመለክተን አግጣጫ፡ ይህንኑ ነው፤ እርሱንም፡ ለማስታወስ ያህል፡ እዚህ ላይ፡ እንደገና እንድጠቅሰው እገደዳለሁ፡-

**"ለምድር፡ ሰላምን ያመጣሁ ይመስላችኋልን፧ አይደለም፤ ሰይፍን፥ መለያየትን እንጂ።" ካለ በኋላ፡"ወደእኔ የሚመጣ፥ ሊከተለኝም የሚወድድ፡ አባቱንና እናቱን፥ ሚስቱንና ልጆቹን፥ ወንድሞቹንና እኅቶቹን፥ የራሱ የኾነችውን፡ ሰውነቱን እንኳ ሳይቀር የማይጠላ፡ ደቀ መዝሙሬ ሊኾን አይችልም።" ያለው ነው።**

እናንተ፡ ለእውነተኛው ኢትዮጵያዊ ማንነት በሚያበቃው፡ በቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖታችሁ፡ ጸንታችሁ የምትገኙ ብትኾኑ ኖሮ፡ ለአለቃ አያሌው ታምሩ የተላለፈውን ደብዳቤ ስታነብቡ፡ ያድርባችሁ የነበረው ስሜት፡ የመንፈስ ቅዱስ እርካታና ደስታ እንጂ፡ የርኩሱ መንፈስ መገለጫ የኾነው ብስጭትና ቍጣ ባልነበረ ያሰኛል።

እንዲያውም፡ ከዚህ ደብዳቤ አልፋችሁ ተርፋችሁ፡ በጠቅላላ፡ መጽሓፎቼ፡ መደርደሪያ ቁም ሣጥኖችን ከማጣበብ ያለፈ ጠቀሜታ የሌላቸው መኾናቸውን፥ አንባቢዎቻቸውም፡ እነርሱን በመመልከት ያጠፉት ጊዜ ከንቱ መኾኑን፥ እኔም፡ እኒህን የመሰሉትን አገልግሎቶች በመፈጸም፡ የማሳልፈው ጊዜ፡ እንደብክነት፥ በመጨረሻም፡ “ይግረምህ!” ብላችሁ፡ በእኔ በኩል እያካኼድሁ ያለሁት ተልእኮ፡ እንደሥራ ፈት የሚያስቆጥረኝ መኾኑን ጽፋችኋል።

ታዲያ ይህ ግብራችሁ፡ ካለፈው፡ ከመሪያችሁ፡ ከአለቃ አያሌው ታምሩ በደልና ጥፋት፡ የባሰ ኾኖ፡ በመንፈስ ቅዱስ ላይ፡ የላቀ የስድብ ቃልን፡ በድፍረት መናገራችሁን፡ አረጋግጦ የሚመሰክርባችሁ፥ እንደዚያ መሪያችሁም፡ እጅ ከፍንጅ የተያዛችሁበት ማስረጃ አይደለምን? ታዲያ! ያ “በመሪያችሁ ላይ ይደርሳል!” ተብሎ የተፈራው መለኮታዊ ፍርድ፡ እርሳቸውን ብቻ ሳይኾን፡ በይበልጥ፡ በሕይወተ ሥጋ ወደኋላ የቀሩትን፡ እናንተን የመሰሉትን ተከታዮቻቸውን፡ “ወደንስሓ ይመልሳቸዋል!” ተብሎ በተስፋ በሚጠበቅበት ጊዜ፡ “በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ!” ወይም፡ “በቍስል ላይ ቍስል!” እንዲሉ፡ በየራሳችሁ ላይ፡ በሥጋም፡ በነፍስም፥ በዚህ ዓለም ኾነ፡ በሚመጣው፡ ስርየት የማይገኝለትን ታላቅ ኃጢኣት መፈጸማችሁ አይደለምን? ዓይናችሁ እያየ፡ ይህን ዓይነቱን ብያኔ፡ በየራሳችሁ ላይ ለመስጠት፡ እንዴት ጨከናችሁ!?

እናንተ ልትኾኑ ያልፈለጋችሁትንና ያልቻላችሁትን፡ ኹኖ የተገኘን ሰው፡ ማለትም፡ ከሰው ይልቅ፡ የእግዚአብሔር ለኾኑት እውነትና መንግሥት፣ ቃላትና ሥርዓት ቀናተኛ ኹኖ፡ ያለፍርሃትና ያለኀፍረት፣ ያለይሉኝታና ያለውልውል፡ በድፍረትና በብርሃን ቆሞ የሚናገረውንና የሚጽፈውን፡ የምትቃወሙና የምትወነጅሉ ስለኾናችሁ፥ ይህን የመሰለውንም ማንነታችሁን፡ እየራሳችሁ በጻፋችኋቸው እ-ጦማሮቻችሁ ስለከሠታችሁት፡ **"አድኅነኒ ወባልሃኒ እማይ ብዙኅ! ወእምእዴሆሙ ለደቂቀ ነኪር!" ማለትም፡ "አቤቱ! ከከሃዲ ሕዝብ ዓመፅና ከምንደኛ ትውልድ አገዛዝ ታደገኝ!"** ተብሎ ሊጸለይባችሁ የሚገባ መኾኑን አረጋግጣችኋል።

ስለዚህ፡ እናንተ፡ የእግዚአብሔር፥ ከእግዚአብሔር፥ በእግዚአብሔርና ለእግዚአብሔር ብቻ በኾኑት ተልእኮዬ፥ መጽሓፎቼና ደብዳቤዬ ላይ፡ እንደዚያ ያለውን፡ የተቃውሞ ጥቃታችሁን ለመፈጸም ስትሉ፡ እነዚያን በመሰሉ፡ የተለያዩ የክፋት ቃላት መጠቀማችሁ፡ በምንም መልኩ፡ ከቶ አያስደንቅም። እንዲያውም፡ እኔንና ተልእኮዬን፥ የዚሁ አገልግሎቴ ፍሬዎች የኾኑትን ሥራዎቼን፡ የቱን ያህል እንደጠቀማችሁና እንዳስከበራችሁ፡ እንዲህ የሚለው፡ የመሪያችን የኢየሱስ ክርስቶስ መመሪያ ቃል በማረጋገጥና በማጠቃለል ያስረዳችኋል፡-

**"ከመምህሩ የሚበልጥ ደቀ መዝሙር፥ ከጌታውም የሚበልጥ አገልጋይ የለም። ደቀ መዝሙር፡ እንደመምህሩ፥ አገልጋይም፡ እንደጌታው ከኾነ፡ ይበቃዋል። ባለቤቱን [እኔን]፡ 'በሰይጣናት አለቃ፡ ሰይጣናትን ያወጣል!' ካሉት፡ ቤተሰቡንማ [እናንተንማ]፡ እንደምን፡ ከዚህ አብልጠው አይናገሩዋቸው!?"** (ማቴ. ፲፥ ፳፬-፳፭።)

እንግዲህ፡ እያንዳንዳችሁ፡ "ኢትዮጵያዊ ነኝ!" ማለቱ ቀርቶባችሁ፡ "ሰብአዊ ፍጡር ነኝ!" ብላችሁ የምታምኑ ከኾናችሁ፡ ቢያንስ፥ ቢያንስ፡ "ተራው ዓይነት ኅሊና አላችሁ!" ማለት ነው፤ እንዲህ ከኾነ፡ አንዳንድ ቀላልና ግልጽ የኾኑ ነገሮችን፡ ማስተዋልና ማመዛዘን ትችላላችሁ ማለት ነው፤ እንዲህ ከኾነ ደግሞ፡ እናንተ፡ አባሎቹና የማንነቱ ተጠሪ ኾናችሁ፡ በአርአያነት የቀረባችሁለት፡ ይህ፡ የዛሬው "ኢትዮጵያዊ ነኝ!" የሚለው ትውልድ፡ ምን ዓይነት እንደኾነ፡ በእየራሳችሁ አጻጻፍ፡ ግልጽ አድርጋችሁ እንዳሳወቃችሁት፡ በትክክል ተገነዘባችሁት አይደለምን?

ለመላው ፍጥረተ ዓለም ያስተዋወቃችኋትና የእናንተ የኾነችው "የዛሬዪቱ ኢትዮጵያ" እና ትውልዷ፡ ምን ዓይነት ጉዶች እንደኾኑ፡ ማለትም፡ የእግዚአብሔር ከኾነው፡ ከቅዱሱ ኪዳን፡ እየራሳቸውን፡ በክህደትና በዓመፅ፣ በአምልኮ አመንዝራነትም በመለየታቸው፡ በዓለም ኅብረተሰብ ዘንድ፡ የቱን ያህል የተናቁና የተዋረዱ፥ የተጠሉና የተጠቁ ኾነው እንዲገኙ እንዳደረጋችኋቸው፡ አስተዋላችሁት አይደለምን?

አዎን! በምንም ዓይነት መልኩና ይዘቱ፡ “ሃይማኖትና ምግባር” ብዬ ላወሳው የማልሞክረው፡ ይህ፡ የእናንተን የመሰለው አስተሳሰብና ድርጊት ነው፡ የዛሬዪቱን ኢትዮጵያና ትውልዷን፡ በአኹኑ ጊዜ፡ በሥጋዊውና በዓለማዊው ብቻ ሳይኾን፡ በሃይማኖታዊውና በመንፈሳዊው የህልውና አቋማቸው ሳይቀር፡ እንዲህ ካለው የኍሥቍልና መቀመቅ አውርዷቸው፡ ሲማቅቁ እንዲታዩ ያደረጋቸው።

“እኔ ከሞትኩ ሥርዶ አይብቀል! አለች” እንደተባለችው እንስሳ፡ አኹንም፡ እናንተ፡ ለየግላችሁ ጊዜያዊ ፍትወትና ጥቅም፥ ክብርና ምቾት ስትሉ፡ እንዲቀጥል የምትፈልጉት፡ ይህን የመሰለውንና የክፋት ወገን የኾነውን፡ “የዛሬዪቱ ኢትዮጵያ”ን አሳዛኝና አሳፋሪ ኹኔታ አይደለምን? አዎን! ነው።

በዚህ አንጻር፡ የእኛ የቅዱሱ ኪዳኗ ኢትዮጵያ ልጆች ፍላጎትና ዓላማ፥ ጥረትና ትግል፡ ከዚህ፡ ከእናንተው፡ ፈጽሞ የተለየው፡ ተቃራኒው ነው። እርሱንም፡ እንዲህ በሚል አጭር ዐረፍተ ነገር መግለጥ ይቻላል፡- ይኸው “የዛሬዪቱ ኢትዮጵያ” አሳዛኝና አሳፋሪ ኹኔታ፡ በመንፈስ ቅዱስ የእውነት ኃይል ተወግዶና ተደምስሶ፡ እኛ እየኖርናት የቀጠልነው፡ እውነተኛዪቱ ኢትዮጵያ፡ በአማናዊውና በጠራው ማንነቷ ተመልሳ የምትገለጽበትን ጊዜ ለማምጣት፥ ደግሞም፡ ዓይኖቹ፡ በክፋት ጨለማ ታፍኖና በድንግዝግዝ የሥቃይ ኑሮ ለሚባዝነው፡ የዘመናችን የኢትዮጵያና የዓለሙ ትውልድም፡ ይህንኑ ምሥራች ለማድረስ፡ እኛ፡ የቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያ ልጆች፡በዚሁ የኢትዮጵያዊነታችን ሕይወት እየኖርን፡ በተልእኳችንና በገድላችን ሳንዝል፡ በበለጠ ጽናት ወደፊት ማካኼድ ነው።

ይህም ማለት፡ ይህችው፡ እውነተኛዪቱ ኢትዮጵያ፡ የ፯ሺ፭፻፪ ዓመታትን በሚያስቈጥረውና የዕድሜ ባለጸጋነቷን በሚያንፀባርቀው ቀዳሚነቷና ጥንታዊነቷ፥ በእግዚአብሔር ሕዝብ አገርነቷና መንግሥትነቷ፡ በጨለማ ተውጦ በጭንቀትና በሥጋት ለሚቃትተው ፍጥረተ ዓለም፡ እንደማለዳ ፀሓይ፡ እንደገና ብቅ ብላ፡ ብርሃኗን የምትፈነጥቅለትንና ከዚህ ከማሰነው አኗኗሩ መንጥቃ የምታወጣበትን ቀን ለማስገኘት ነው። ያም፡ ኢየሱስ ክርስቶስና ድንግል ማርያም፡ በዙፋናቸው ተቀምጠው፡ በፍጥረተ ዓለሙ ላይ በገሃድ የሚሰፍኑባት መንግሥታቸው የምትገለጥባት ናት።

ጽሑፌን ከመዝጋቴ በፊት፡ “ቀሪን ገረመው በላቸው” የሚለው፡ የፈጠራ ይኹን የእውነት ስያሜያችሁ፡ ዛሬ፡ እናንተና እኔ ላለንበት እውነተኛ ኹኔታ፡ እንዴት አድርጎ እንዲስማማ ኾኖ ሊተረጐም እንደሚችል፡ እዚህ ላይ፡ እንዲህ በሚሉ ዐረፍተ ነገሮች ገልጬ፡ እስኪ ላቅርብላችሁና፡ በማስተዋል ተመልከቱት!

-ይህች የዛሬዪቱ፡ የእናንተ ኢትዮጵያ፡ እናንተን የመሰሉ ልጆችን ያፈራውን፡ ይህን ትውልድ አስገኘች! ይኸው ትውልድ፡ ከሃይማኖት ጉድለቱና ከምግባር ብልሽነቱ የተነሣ፡ የፈጸመው፡ የክህደት፥ የዓመፅና የምንዝርና ታላቅ ኃጢአት፡ ለእውነተኛዪቱ ኢትዮጵያ፡ የህልውናዋ መሠረት፥ የሕይወቷ ግድግዳና የክብሩዋ ጉልላት ኾኖ፡ ከፈጣሪዋና ከቅድስት እናቱ ጋር ባስተሣሠራት፡ በቅዱሱ ኪዳን ላይ ጽኑ ቀውስን አመጣ! ያም ቀውስ፡ በቤተ ሕዝቡ፥ በቤተ ምልክናውና በቤተ ክህነቱ ላይ፡ መለኮታዊዉን የውግዘት ፍዳ አስከተለ!

-ከደርግና ከእናንተ የሞት ፍርድ ተርፌ፡ ዕድሜውን ያገኘሁትን፡ እኔን የመሰለው ኢትዮጵያዊ፡ እናንተ፡ ማንነታችሁንና ምንነታችሁን በገለጻችሁባቸው፡ በእነዚህ እ-ጦማሮቻችሁ መጽሔትነት፡ ያች፡ የሚያውቃት፡ እውነተኛዪቱና ገናናዪቱ ኢትዮጵያ፡ ዛሬ፡ በዓለሙ ኹሉ ፊት፡ እንዲህ ተዋርዳ፥ ይኸው ትውልዷም፡ በንስሓ ለመመለስ፡ እምቢ ብሎ፡ እንዲህ፡ በመከራና በፈተና እየተሠቃየ መቀጠሉን አየ! አረጋገጠ!

-ስለዚህ፡ የደርግን የሞት ፍርድ፡ ዐብረውት የተቀበሉት፡ የእሥር ቤት ጓደኞቹ፡  ፍርዱ ሲፈጸምባቸው፥ እርሱ ግን፡ ከዚያ ሠይፍ፡ ለጉድ ተርፎና ወደኋላ ቀርቶ፥ "ዕድሜ፡ መስታዋት ነው!" እንዲሉ፡ በዕድሜውም ቆይቶ፡ ይህን ኹሉ ጉድ ለመመልከት በቃ!

-በዚህ ኹኔታ፡ ምንኛ፥ የቱንስ ያህል ይገርመው! ከዚህ የተነሣ፡ "‹‹ቀሪን ገረመው በላቸው!› ብሏል!› ብለህ፡ ዛሬ ላለውና ለመጪዎቹ የኢትዮጵያ ትውልዶች ንገራቸው! ጻፍላቸውም! አለ!" ተባለ። አዎን! ያስሰኛል።

በመጨረሻ፡ "ጆሮ ያለው ይስማ!" በሚለው፡ በመለኮታዊው የአዋጅ ቃል፡ ነገሬን ለማብቃት እንዲህ እላለሁ፦

"ለብልህ አይነግሩ! ለአንበሳ አይመትሩ" የሚባለው እኮ! "በራሱ ክንድና ጥርስ ገንጣጥሎና ዘነጣጥሎ ሊበላ ለሚችለው፡ ለአራዊቱ ንጉሥ፡ ለአንበሳ፡ ራሱ ዐድኖ፡ በግድያው ያቀረበውን የሰለባ ሥጋ፡ 'እኔ፡ እየመተርሁ፡ ላጕርሥህ!' ማለት፡ በራስ ላይ ሞትን መጋበዝ ነው።

"እንዲሁ ኹሉ፡ ሰውም፡ በእግዚአብሔር መልክ በመፈጠሩ፡ በዚህ ተፈጥሮው ምክንያት፡ ብልህ ነው። ራሱ፡ ኹሉን ነገር  ስለሚያውቅ፡ ሊነገረው የሚገባ ምንም ነገር የለም። ምናልባት፡ አስፈላጊ ኾኖ ቢነገረው እንኳ፡ ጥቂት፥ ወይም፡ ለአንድ ጊዜ ብቻ ይበቃዋል።" የሚለውን መልእክት ለማስገንዘብ ነው።

የምሳሌው መልእክት በዚህ አያቆምም፤ ግቡ፡ ስለሰነፍ ለማመልከት ስለኾነ፡ መልእክቱ፡ "ለሰነፍ ግን፡ መልሰውና መላልሰው፡ አሥር ጊዜም ቢነግሩት፥ ቢወቅሩትም፡ አይሰማም፤ አይገባውምም። ስለዚህ፡ ያለው ምርጫ፡ እርሱን፡ ማነጋገሩን መቀጠል፥ ወይም፡ ማቆም ብቻ ይኾናል!" በሚል ውሳኔ ይደመደማል። ለዚህ ይትበሃል፡ "አውቆ የተኛን፡ ቢቀሰቅሱትም፡ አይነቃም!" የሚለው ምሳሌያዊ አነጋገርም፡ ይስማማዋል።

ለእናንተም፡ ለአለቃ አያሌው ታምሩ የተጻፈው ደብዳቤ ይበቃችሁ ነበር፤ ቢበዛም፡ “ተመልክተናቸዋል!” ያላችኋቸው መጻሕፍቱና በጎዋ ሰሌዳችን ላይ የወጡት መልእክቶች በበቋችሁ ነበር (ምንም እንኳ፡ በcarpነት የፈረጃችኋቸው ቢኾኑም!)። እኔም፡ ለእነዚህ ደብዳቤዎቻችሁ፡ ይህን ያህል በማተት፡ የማብራሪያ መልስ መስጠት ባላስፈለገኝ ነበር፤ ይህም ኹሉ ኾኖ፡ አኹንም፡ መልእክቱ፡ ገብቷችሁ፡ ቁም ነገሩን፡ ለመረዳት የምትችሉ ቢኾን፡ መልካም በኾነ ነበር።

አኹንም፡ ይህን መልስ የሰጠሁት፥ እንዲያውም፡ እንዲህ አብራርቼ፡ በሰፊው የጻፍሁት፡ ለእናንተ ብቻ ሳይኾን፡ በይበልጥ፡ ይህ፡ የእናንተ ተቃራኒ አስተሳሰብ፡ በቃልም ኾነ፥ በጽሑፍ ለሚደርሳቸው ኹሉ፡ በዚህ ረገድ፡ በእኔ በኩል፡ የተከሠተችውን፡ የእግዚአብሔርን እውነት፡ በትክክለኛው ግልጽነት እንዲያውቋት ለማድረግ ስል ነው።

ለእናንተማ፡ የእግዚአብሔርን እውነትና መንግሥቱን የምትሹ ብትኾኑ ኖሮ፡ ያው፡ ለአለቃ አያሌው ታምሩ የተጻፈው ደብዳቤ፡ ይበቃችሁ አልነበረምን? መልእክቱንም ተቀብላችሁ፥ በሞተ ሥጋ ለቀደሟችሁ፡ “ነፍሳቸውን ይማርልን! እኛንም፡ ይቅር ይበለን!” ብላችሁ፡ በእውነተኛ የሃይማኖትና የአምልኮ ንስሓ ተጠምዳችሁ በጸለያችሁ ነበር። ይህን የመሰለ፡ ዘለፋን ያዘለ፡ የእብሪትና የትምክህት ምላሽ በመስጠት ፋንታም፡ እውነተኞቹ ኢትዮጵያዊና ኢትዮጵያዊት፡ የ“እግዚአብሔር ሰው” ተብለው በሚታወቁበት፡ የትሕትና ምግባር ላይ በተገኛችሁ ነበር። ነገር ግን አልኾነም።

ስለዚህ፡ “የሚያደርጉትን አያውቁምና፡ ይቅር በላቸው!” ተብሎ ሊጸለይላችሁ የምትገቡ ኾናችሁ አግኝቻችኋለሁና፡ እኔም፡ ተልእኮዬ በመኾኑ፡ በዚህ ረገድ የሚገባኝን ከማድረግ፡ ወደኋላ አልልም። (ሉቃ. ፳፫፥ ፴፬። የሐዋ. ፯፥ ፷።)

እንግዴህ፡ እናንተም፥ እኔም፡ እየራሳችንን፡ በንስሓ መልሰን እያደስን፥ በሥጋ ሞት ለተለዩንም እየጸለይን፡ የእግዚአብሔር መንግሥት በኾነችው እናት አገራችን ኢትዮጵያ፡ ዛሬ፡ በዚህ ዓለም፡ በሕይወተ ሥጋ፥ ኋላም፡ በሚመጣው ዓለም፡ በሕይወተ ነፍስ፡ ኹላችንም፡ በአንድነት ለመኖር እንድንችል፡ በተሰጠን መለኮታዊ ጸጋና ዕድል እንጠቀም ዘንድ፡ አኹኑኑ፡ በዚችው፡ በመዳፋችን ይዘናት ባለችው የህልውናችን አፍታ መወሰን ይገባናል።

ይኹን እንጂ፡ አቋማችሁ፡ አኹንም፡ የዚያን፡ ለአለቃ አያሌው ታምሩ የተጻፈውን ደብዳቤ መልእክት አለመቀበል ከኾነ፥ ከዚሁ የተቃውሞ አቋማችሁም፡ በእውነተኛ ንስሓ ባለመመለስ፡ እስከመጨረሻው ጸንታችሁ መቀጠልን ከመረጣችሁ፡ የእናንተም ዕድል ፈንታና ጽዋ ተርታ፡ ያው፡ እንደጌታ ቃል፡ ለአለቃ አያሌው ታምሩ የተወሰነው ዓይነት መኾኑን፡ በጽኑ ልትገነዘቡት ይገባል።

ይህም፡ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በቀደሙ አብነቶቻችሁ፡ በአይሁድ፡ በተቀዳጀው የሾህ አክሊል መልክ፡ ዛሬ ደግሞ፡ እናንተ፡

-በመጀመሪያ፡ የእግዚአብሔርን እውነትና የእግዚአብሔርን መንግሥት፥ የእግዚአብሔርን ቃላትና የእግዚአብሔርን መልእክት ለያዙት፥ ባጠቃላይም፡ የመንፈስ ቅዱስ ለኾኑት መጻሕፍቴ፡ ወደኢትዮጵያኛ መተርጎሙ እንኳ የሚያሥቅቀውን፡ crap books የሚለውን፡ የባዕዳኑን የርኵሰት ስያሜ፥

-ቀጥሎ፡ ለደብዳቤዬ፡ ከላይ የተገለጡትን፡ የባዕዳኑን ልዩ ልዩ ጸያፍ የተጸውዖ ቅጽሎችን መስጠታችሁ፡ በቀጥታ፡ በመንፈስ ቅዱስ ላይ፡ የስድብ ቃልን መሠንዘራችሁ መኾኑን የሚያረጋግጠው፡ ከዚህ ቀደም ብሎ፡ በሰፊው የተብራራው እውነታ ነው።

ይህን እውነታ መሠረት በማድረግ፥ እውነተኛው መምህራችንና ሊቃችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ "ስለዚህ፡ እላችኋለሁ፡- ኃጢአትና ስድብ ኹሉ፡ ለሰዎች ይሰረይላቸዋል፤ ነገር ግን፡ መንፈስ ቅዱስን ለሰደበ፡ አይሰረይለትም። በሰው ልጅ ላይ፡ ቃልን የሚናገር ኹሉ፡ ይሰረይለታል፤ በመንፈስ ቅዱስ ላይ ግን፡ የሚናገር ኹሉ፡ በዚህ ዓለም ቢኾን፥ ወይም፡ በሚመጣው፡ አይሰረይለትም።" ብሎ የተናገረውን ቃሉን በማመን፡ ከአበጋዛችሁ፡ ከአለቃ አያሌው ታምሩ በደል ይልቅ ለባሰው፡ ለዚሁ፡ ለታላቁ ኃጢአታችሁ፡ የሚገባውን ፍርድ ይሰጥ ዘንድ፡ በእውነተኛው መንፈሳዊ አምልኮ፡ ሰግጄና በግንባሬ ተደፍቼ፡ ይህን፡ ግልጽ ደብዳቤዬን፡ ለባለቤቱ፡ ለመንፈስ ቅዱስ፡ እነሆ፡ በይፋ አስረክቤያለሁ።

ጥር ፳፩ ቀን፥ ፳፻፪ ዓ. ም.

ቅድስት ድንግል ማርያምና የእግዚአብሔር መንግሥት የኾነችው ኢትዮጵያ አገልጋይ፡- ቄስ (ንቡረ እድ) ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ።